# የፓትርያርክነቱ መንበር እንዴት ተገኘ ?

## እሥራ ምዕቱን (2000) ለመዘከር

ረታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት

ከዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ

መጋቢት 27 ቀን 1999 ዓ.ም.

አድራሻ
ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
☎ 011-127 16 09
011-127 44 64
091-186 01 13
091-170 87 80

ኮምፒዩተር ዲዛይን
ሠናይት መላኩ
091-130 12 99

www.ethiopianorthodox.org

## መታሰቢያነቱ

የቤተ ክርስቲያናችንን ሁለንተናዊ እድገት ሳፋጠኑ በአይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ ታላላቅ ሥራዎችን ለሠሩ፣ በዚች ቅድስት ሀገር በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን እጅ በመሾም የመጀመሪያው ፓትርያርክ ለሆኑ፣ ለሰማዕቱ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ዘደብረ ሊባኖስ ኤልያስ ጉጃም ይሁንልኝ፡፡

© የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

## አበርክቶት

ለዚህ ምስኪን ዓለም መዳን አንድ ልጁን በመላክ ለወደደን፣ የፈለገውን ነገር ሁሉ በልጁ በኩል ላከናወነ ኤፌ.1÷10፣ በስሙ ለታነፀው ለደብረ ቢና ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያንና በዚሁ ደብር ለሰ/ት/ቤት እድገት ለወንጌልመልእክት ጥሩ ዓላማ ላላቸው ዘወትር ነገረ መስቀሉን ተሸክመው ለሚኖሩ ለሰንበት ት/ቤቱ ጥቂት የዓላማ አባላት ለሆኑ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ እንዲሁም፡- ከማህፀን ጀምራ የተሸከመችኝ ሁልጊዜ የእናትነት ፍቅሯ ያልራቀኝ ላለሁበት ሕይወት አስተዋፅኦ ላደረገችልኝ ለውድ እናቴ ለወ/ሮ ሙሉ ተገኝ ይህን መጽሐፍ አበረክታለሁ፡፡

## ምስጋና

☞ ይህን አነስተኛ የሆነውን ጅምር ወደዚህ ከፍ ላለ የመ ጽሐፍ ዝግጅት እንዲደርስ ኃይል ለሆነኝ በሞቱ ላዳነኝ በደሙ ላከበረኝ ለጌታዬ ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር፣ ምስጋና፣ ውዳሴ፣ ዝማሬ፣ ስባሔ፣ እበይ፣ አምልኮ፣ ስግደት ለእርሱ ብቻ ይሁን፡፡ አሜን!

☞ መጽሐፉን አንብበው ገንቢ አስተያየታቸውን የለገሱኝ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ እያስተማሩ ላሉ መ/ር ዳንኤል ሠይፈ ሚካኤልና መ/ር አብርሃም አዱኛ፣

☞ የሽፋኑን ዲዛይን በምፈልገው ሀሳብ አሳምሮ የሠራልኝን አርቲስት እንየው ጸጋዬን፣ እንዲሁም ረቂቁን ሳትሰለች በትዕግሥት ለአንባቢ እይታ እንዲስብ አድርጋ የጻፈችልኝን ወ/ሮ ሠናይት መላኩን እጅን በጣም አድርጌ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

☞ ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ የታደሰ ሀብቴ ቅን ሀሳብ ባይታከልበት ይህ መጽሐፍ እዚህ ደረጃ አይደርስምና ባለውለታዬ ነው፡፡ ቸሩ አምላክ ዘወትር በምሕረቱ እንዲጐበኘው እመኛለሁ፡፡

☞ በመጨረሻም ዘወትር በሀሳብ በምክር ከጐኔ ያልተለዩኝ ከዚህ የበለጠ ሥርቼ ቤተ ክርስቲያንን እንዳገለግል የምታበረታታኝ መጽሐፉ እንዲወለድ በጸሎቷ ያሰበችኝ ፈትለወርቅ ፈ.ልጋሳ /አይቲን/ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርብላታለሁ፡፡

**የሽፋን ሥዕል መግለጫ**

1. በስተግራ የጥንቱ አሁን ሙዚየም የሆነው መንበረ ፓትርያርክ ሲሆን በስተቀኝ ያለው ኢትዮጵያዊ ኪነ ጥበብ የተንጸባረቀበት አዲሱ መንበረ ፓትርያርክ ነው፡፡
2. በሀገራችን በመሾም የመጀመሪያው ፓትርያርክ የዚህ መጽሐፈ አዘጋጅ የመጽሐፉን መታሰቢያነት ለእርሳቸው የሰጠው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በደቀመዝሙርነት በመምህርነት በሊቀ ሥልጣናትነት በጳጳስነት እና በፓትርያርክነት ማዕርግ ይታያሉ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ

ገጽ


✠ መቅድም ........ 1
✠ መግቢያ ........ 3


## ምዕራፍ አንድ


✠ መንፈሳዊ ነፃነት ለማግኘት የተደረገ ጥረት ........ 11
✠ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነፃነት ማግኘት ........ 15


## ምዕራፍ ሁለት


✠ በጠላት ወረራ የተቋረጠው ግንኙነት መቀጠል ........ 23
✠ መንፈሳዊ ጉባኤ ያደረገው ምርመራ ........ 28


## ምዕራፍ ሦስት


✠ የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መስማማት ........ 31
✠ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ መሾም ........ 35


## ምዕራፍ አራት


✠ ኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳስ ፓትርያርክ መሆን ........ 39
✠ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ታሪክ ........ 42
✠ በፓትርያርኩቻችን የተሾሙ ጳጳሳት ብዛት ........ 47


## ምዕራፍ አምስት


✠ በኢትዮጵያ ምድርና በኢትዮጵያውያን እጅ በመሾም
የመጀመሪያው ቅዱስ ፓትርያርክ ........ 55
✠ አቡነ ቴዎፍሎስ ለዚህ ማዕረግ መመረጥ ........ 57
✠ በሀገር ውስጥ ያከናወኗቸው ሥራዎች ........ 61
✠ በውጭ ሀገር የፈጸሟቸው ሥራዎች ........ 67
✠ ስለ ቅዱስነታቸው የተሰጡ አድናቆቶች ........ 75
✠ በዘመነ ክርስትና የነበሩ ነገሥታት ዝርዝር ........ 79
✠ እጨጌዎች ........ 87
✠ ዓቃቤ ሰዓት ........ 90
✠ ግብፃውያን ፓትርያርኮች ........ 93
✠ ከግብፅ የመጡ ጳጳሳት ........ 105
✠ ዋቢ መጻሕፍት ........ 108


በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

# መቅድም

*"... ይህ መንበር ቅዱስ በመሆኑ ያለፈውን የሚናገር የወደፊቱን ትንቢት የሚገልፅ ያዘኑትን የሚያረጋጋ የተቸገሩትን የሚረዳ፤ መንፈሣውያን አገልጋዮችን የሚመግብ፤ ከፍተኛ መንበር ነው:: ይህ መንበር የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን ለክብርና ለታሪክ ልዩ ልዩ የሃይማኖት ተከታዮች ያከብሩታል ለታሪክ ልዕልና ይከበራል:: ይህ መንበር በቀላል የተገኘ አይደለም በሥጋዊ አካልም ቢሆን ስለመንበሩ ሲባል በከፍተኛ ደረጃ አድክሟል:: እንግዲህ ይህ መንበር ለአገራችን እንደ ታላቅ በረከት ነውና የምንመለከተው..."*

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ
[ትንሣኤ ቁጥር 107]

አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከእግዚአብሔር በተለገሰው እድሜ ሊሠራቸው ከሚገባቸው ነገሮች መካከል መጭው ትውልድ በዓላማ እንዲኖር የቤተ ክርስቲያኑን ሕልውና እንዴት እዚህ ደረጃ እንደደረሰ እየመረመረ ባለው ጊዜ ማስገንዘብ ሲችል ብቻ ነው:: ለዚህ ደግሞ በችኮላ ሳይሆን ረጋ ብሎ በሞቱ ካዳነው በደሙ ካከበረው አምላኩ የተሰጠውን ሕይወት በአግባቡ ሲጠቀምበት ነው የጊዜን ጥቅም የሚረዳው:: ለዚህ ነው «ጊዜን ያስተዋለ እንጂ የቸኮለ አይጨርሰውም» የሚባለው:: እንደ እግዚአ ብሔር ፈቃድ በዚህ ዓመት ለማዘጋጀት ካቀድኩት መጻሕፍቶች መካከል ለብዙ ጊዜ ሳብላላው የቆየሁትን በኘትርክና መንበር [በሊቃነ ጳጳሳት] ዙሪያ ከግብፅ- እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለንን ግንኙነት እስከ ምን ድረስ እንደነበር ለመግለፅ አስብ ነበር:: በሁለት ክፍል ካዘጋጀሁት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት መጻሕፍት [ክፍል አንዱ ታትሟል፤ ክፍል ሁለቱ ለልቆ ሕትመት ብቻ ይጠብቃል] ይህን ጉዳይ በመጠኑ እንደ አንድ ወርቃማ ዘመን በመውሰድ አካትቼው ነበር::

ሆኖም ይህን የመሰለው ታሪክ በትንሹ ተዳስሶ ከሚታለፍ ራሱን የቻለ ርዕስ ተሰጥቶት ለንባብ ቢበቃ የበለጠ ጥሩ ነው ብለው የቅርብ ወዳጆች ምክራቸውን ስላካፈሉኝ፤ ከላይ የገለፅኩት ክፍል ሁለት የመጽሐፍ ዝግጅቴ ውስጥ ከ30 ገፅ ያላነሰ ታሪክ ይዞ ቢካተትበትም የቅርብ ባልንጀ ሮች ስላበረታቱኝ ሰፋ አድርጌ እንደውም የበለጠ ጊዜና ትኩረት በመስጠት ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ችያለሁ:: አንባብያን! የዚህ መጽሐፍ ዋናው ፍሬ ሀሳብ የፓትርያርክነት መንበር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከብዙ ልፋት በኋላ እንዴት እንደተቀዳጀች ፍፃሜውም የት እንደደረሰ እኔን መሰል ወጣት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንዲገነዘቡት ለማድረግ ብቻ ነው::

በ1951 ዓመተ ምሕረት ይህን ክብር ያገኘንበት ወርቃማ ዘመን ነው:: ይህን እድል ካገኘንበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ቤተ ክርስቲያናችን 5 ፓትርያርኮችን በመንበሯ ላይ ሰይማለች:: በዚህ የመጽሐፍ ዝግጅት እነዚህ ፓትርያርኮች በሢመት ዘመናቸው የሾሟቸው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የቀድሞና የሹመት ስም፤ ተመድበውበት የነበረው ሀገረ ስብከታቸው የዚህ መጽሐፍ ሌላው አካል ሆኖ ሰፍሯል:: በመጨረሻም ለግንዛቤ እንዲረዳን በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ውስጥ ነገሥታት፣ እጨጌዎች አቃቤ ሰዓታት ግብፃውያን ፓትርያርኮችና የላኳቸው ጳጳሳት ይዳሰሳሉ::



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ የግብፅ - እስክንድርያ ፓትርያርኮች ስም በሙሉ እና እንደዚሁም የወረሯቸው መሐመዳውያን ያደረሱባቸውን ችግሮች ጉላ ያሉትን በመካከሉ አስፍሬዋለሁ:: እነዚህ ፓትርያርኮች ለሀገራችን ሹመው የላኩልን ጳጳሳት ስም ዝርዝር ሁሉንም ባይሆን የተወሰኑትን በማን ዘመነ መንግሥት እንደመጡ ለመጠቆም ሞክሬአለሁ:: እንዲሁም በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጀመረው የእጨጌነት ስያሜ እና ብዛታቸው እንዲሁም በቤተ መንግሥት ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን ወክለው ያገለገሉ አቃቤ ሰዓታት ዝርዝር፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂዎች የነበሩት ነገሥታት በተለይ ከዘመነ ክርስትና ወዲህ የነገሡትን እንደየነገሡበት ዘመን በዝርዝር አስፍሬዋለሁ::

ይህ የመጽሐፍ ዝግጅቴ ብፁዓን አባቶችን የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን ወደፊት በሌሎች እውቅ ሊቃውንት በሕይወት ያሉትንም የሌሉትንም አጠቃላይ የሕይወት ታሪክ የያዘ መድብል ይጽፋሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: ይህ ደግሞ ፍንጮች እየታዩ ነው:: በተለይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ1996 ዓ.ም. ያዘጋጀው «ዝክረ አበው» የሚል መጽሔት ያሉትን የነበሩትን ብፁአን አበው ጳጳሳት መቼና በማን ዘመን እንደተሾሙ በፎቶ ግራፍ አስደግፎ አውጥቷል:: ጉድሏል ብሎ ያሰበውን ደግሞ ተሻሽሎ እንደሚወጣ አስገንዝቧል:: ይህ የመጽሔት ዝግጅት ቀደም ብዬ ለጠቀስኩት ሀሳብ ተስፋ ሰጭ በመሆኑ አደንቃለሁ:: በቅርቡ ደግሞ ያረፉትን ብፁዓን ኢትዮጵያውያን አበው ጳጳሳት የሕይወት ታሪክ የያዘ በዲያቆን መርሻ አለኸኝ የተዘጋጀ «ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን» የተባለው መጽሐፍ ትውልዱ እነዚህን አባቶች ከነበራቸው የቤተ ክርስቲያን ሙያ ጋር እንዲያውቃቸው በማድረጉ መጽሐፉን ሳላደንቅ አላልፍም::

እኔም ከዚህ ወጣ በማለት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛውን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ማዕርግ እንዴት እንዳገኘችና የቀድሞ ነገሥታት ይህን እጃቸው ለማስገባትና ሙሉው ሥርዓት በምድራችንና በልጆቿ እንዲካሔድ ያደረጉትን አስተዋፅኦ በመጠኑ ለመጠቆም ሞክሬአለሁ:: በወቅቱ በዚህ ዙሪያ የተዘጋጁ ወይም ይህን ታሪክ የመዘገቡ መረጃዎች እንደልብ አለማግኘት ከዚህ ከፍ ያለ ጥራዝ እንዲወጣው ባስብም፣ ፍላጐቴና ምኞቴን ገድቦታል:: ቢሆንም የአቅሜን ያህል በመድከም 30 ገፅ የሆነውን ይህን ጅምር ለዚያውም እንደ አንድ ርዕስ በሌላ የመጽሐፍ ዝግጅቴ ተካትቶ የነበረውን ወደዚህ ራሱን ወደቻለ መጽሐፍ ከፍ ስላደረኩት ለዚህ ደግሞ ጌታዬ፣ አዳኜ፣ ቤዛዬ፣ ተስፋዬ በደሙ ያጠበኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ስለሆነኝ እያመሰገንኩት! የመጽሐፉን ደካማ ጐን ለመጠቆም የሩቅና የቅርብ ወዳጆች ግንዛቤ የግድ ያስፈልጋልና ይህን እየጠበቅሁ፣ ነገር ግን ምን ለማስቀመጥ እንደሞከርኩ ትረዱኛላችሁ የሚል ፅኑ እምነት ስላለኝ ዝግጅቴን ለንባብ ሳበረክት ራሴን ዝቅ በማድረግ ነው::

አዘጋጁ



# መግቢያ

የኢትዮጵያና የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት የጀመሩት በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ነው:: የግንኙነታቸውም ምክንያት በትውልዳቸው ሶርያዊ በዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ የሆኑት የመጀመሪያው የሀገራችን ጳጳስ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ማዕርገ ጵጵስና አግኝተው የመጡት ከግብፅ እስክንድርያ ነበር:: የሾመልንም 20ኛው የመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ ነው:: አባ ሰላማ ወደ ግብፅ በመሔድ የመጡበትን ጉዳይ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ሲያመለክቱ ቅዱስ አትናቴዎስ ሌላ ግብፃዊ ሰው በማፈላለግ ጊዜውን አላባከነም:: ራሱን ፍሬምናጦስን ሹሞ ልኮልናል:: የሕዝቡን ባሕል ቋንቋ...፣ የሚያውቅ ከሱ ሌላ ማንም አልነበረምና::

ከዚህ በኋላ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት የተመሠረተው መንፈሳዊ ግንኙነት ግብፅን ከ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እየተፈራረቁ የገዟት ባለ ሥልጣኖች በቤተ ክርስቲያኒቱ ጭምር ጣልቃ በመግባት እየተቋረጠና እየቀጠለ ሄዷል:: ከቅዱስ አትናቴዎስ በኋላ የተሾሙ ጥቂት የማይባሉ የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት መንፈሳዊ ሥልጣኑን የራሳቸው ብቻ በማድረግ በሠለስቱ ምዕት /በ318/ ሊቃውንት ስም:- «ኢትዮጵያ ከተወላጆቿ መካከል ጳጳስ መሾም የለባትም» ብለው የፈጠራ ጽሑፍ በፍትሐ ነገሥት ላይ በመደንቀራቸው ለ1 ሺ 600 ዓመታት ያህል በባዕድ ተፅእኖ ስር የወደቀችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እምነቷን እንደ ልብ ለማስፋፋት ከፍተኛ የሆነ የአባቶች እጥረት የታየበት በርካታ ዓመታትን አሳልፋለች:: የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የመጠበቅና የማስጠበቅ ሂደት ትልቁን ድርሻ የተወጡት ሀገራችንን የመሩ ነገሥታት ይህን መንፈሳዊ ችግር እጃችን ለማስገባት ብዙ ጥረት አድርገዋል:: ከእነዚህም መካከል ሊጠቀሱ የሚገባቸው የላስታው ንጉሥ ሐርቤ እና አፄ ዮሐንስ 4ኛ ናቸው::

ንጉሥ ሐርቤ በንግሥናው ዘመን [1131-1145 ዓ.ም] ኢትዮጵያውያን አድካሚ ጉዞ አድርገው ወደ ግብፅ በመሔድና የግብፅን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደጅ ጠንተው ገፀ በረከት ሰጥተው በዚያ ላይ ድንበርን ለሚቆጣጠሩ የግብፅ ሡልጣን ወኪሎች መንገድ እንዲሰጧቸው ተማፅነው፣ በብዙ ችግር ይዘው የሚመጡት ጳጳስ ተሿዙሮ መስበክ ስለማይችል፣ በዚያ ላይ የቋንቋ መግባባት ችግር ስላለ የመጣው ጳጳስ የሚቀመጠውም በቤተ መንግሥት ክልል መሆኑን ከግምት በማስገባት ለየት ያለ ጥያቄ ለግብፅ ቤተ ክርስቲያን ያቀረበ ንጉሥ ነው:: ይህም እኛ ራሳችን ለዚህ ማዕርግ ይበቃል ያልነው መነኩሴ መርጠን ጳጳስ አድርጋችሁ ሹሙልን በማለት መልእክተኞችን ወደ ግብፅ ላከ:: በዘመኑ የነበሩት የእስክንድርያ ፓትርያርክ አባ ገብርኤል ሁለተኛ ሲሆኑ [70ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ናቸው] ጥያቄውን በቀና ሳይቀበሉ የላክንላችሁ ጳጳስ በቂ ነው ብለው መልእክተኞችን አሰናበቱ:: በዚህ የጨለማ ዘመን ይህን የመሰለ ጥያቄ ቅዱስ ሐርቤ ማቅረቡ የነገሩን አስፈላጊነት በሚገባ መረዳቱን ይጠቁማል::



www.ethiopianorthodox.org

ይህን የመሰለውን ጥያቄ ከ8 መቶ ዓመታት በኋላ በአፄ ዮሐንስ 4ኛ ዘመን በድጋሚ ተነሥቷል:: አፄ ዮሐንስ ከላይ የገለጥነውን መሠረታዊ ችግር ገብቷቸው የግብፅን ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊ ጳጳስ እንዲሾም ጠይቀዋል:: እንደተለመደው ጥያቄአቸው ተቀባይነትን አጣ:: ከዚህ በኋላ ኢየሩሳሌም ውስጥ በሚኖሩ መነኮሳት አማካኝነት ከሶርያ ጋር ደብዳቤ መጻጻፍ ጀምረው ነበር:: ሆኖም ሕዝቡ ያልለመደው የሌላ እህት አብያተ ክርስቲያን ጳጳስ ቢመጣ ይከፋዋል በማለት ትተውታል:: ነገር ግን ሌላ ጥያቄ በማቅረብ 4 ግብፃዊ ጳጳስ ተሹመው እንዲመጡላቸው ጠይቀው ይህ ተፈጽሞላቸዋል:: እነዚህ 4 ግብፃውያን ጳጳስ በ80 ሺ ብር ተገዝተው ነበር የመጡት::[1]

እነዚህ ሁለት ነገሥታት በዚያን ዘመን በሞኝነት የተደነቀረብንን እንቅፋት ለመንቀል ያቀረቡት ጥያቄ ዛሬ ተገቢውን መልስ ማግኘቱን ስን መለከት ዓላማቸው በዘመናቸው ሳይፈፀም ቢያልፉም የከፈቱትን ጠባብ መንገድ የኋላ ሰዎች በማስፋት ፍላጐታችን እንዲፈጸም ሀሳባቸው ታላቅ አስተዋፅኦ አድርጓል:: ለ1ሺ 600 ዓመታት ወደ ኢትዮጵያ የመጡ 110 ግብፃዊያን ጳጳሳት ሁሉም ባይሆኑ አንዳንዶች ቤተ ክርስቲያናችንን ጐድተ ዋታል:: ጥቂቶቹን ጥሩ ካልሆነው ሥራቸው ጋር እንደሚከተለው እናያለን::

በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በላስታው ንጉሥ ጃን ሥዩም ጊዜ ወደ ሀገራችን የተላኩ ግብፃዊ ጳጳስ አቡነ ሳዊሮስ ይባላሉ:: እኝህ ጳጳስ በግብፅካ ለው የመንግሥቱ መሪ ጋር በመመካከር በዚያ የሚኖሩ የእስክንድርያ ክርስቲያኖች የእስላሞች አገዛዝ እንዲቀንስላቸው በማሰብ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ፤ ከመጡበት መንፈሳዊ ዓላማ በእጅጉ በመውጣት በኢትዮጵያ ለሚ ኖሩ ጥቂት የዓረብ እስላሞች መስኪድ አሠርተው ነበር:: ሕዝቡም በነገሩ በመቆጣት ጳጳሱን ማረፊያ ቤት በማስገባት መስኪዶችን አፍርሷቸዋል:: [የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአባ ጎርጎርዮስ ገፅ 34፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጉዬ በተክለ ጻድቅ መኩሪያ]

ከላይ በጠቀስነው ንጉሥ ዘመን የመጡት የእስላሞች ወዳጅ አቡነ ሳዊሮስ ከታሠሩ ጀምሮ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ አልመጣም:: ከዚህ በኋላ የነገሠው ይምርሐነ ክርስቶስ ተላልኮ አባ ጊዮርጊስ የተባሉትን ጳጳስ አስ መጣ:: የመጡት እኒህ ጳጳስ የሕዝቡን መንፈሳዊ ጥማት በማርካት ፈንታ

1. እነዚህ ጳጳሳት ማቴዎስ፣ ጴጥሮስ፣ ሉቃስ፣ ማርቆስ ይባላሉ:: ከዋናው ጳጳስ ከአቡነ ጴጥሮስ በቀር አቡነ ማቴዎስን ለንጉሥ ምኒልክ፣ ሉቃስን ለንጉሥ ተክለሃይማኖት፣ ማርቆስን ደግሞ ለቤጌምድር ደልድለዋቸዋል:: ከእነዚህ መካከል አቡነ ሉቃስ ታህሳስ 28 ቀን 1881 ዓ.ም. ሲሞቱ፤ አፄ ምኒልክ ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ጋር ተላልከው አቡነ ዮሐንስ የተ ባሉ ጳጳስ በ1891 ዓ.ም. አምጥተዋል:: እኚህ ጳጳስ በሥራቸው ላይ ብዙም አልቆዩም አየሩ ስላልተስማማቸው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ:: ሲመለሱ ሐረር ላይ ለደጃዝማች ተፈሪ /በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ/ እና ለልጅ እምሩ /በኋላ ለራስ/ የዲቁና ማዕርግ ሰጥተዋል [አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር 10 ገፅ 103]



ስስታምና ምእመኑን ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመሰብሰብ ይልቅ በንግድ ተሠማርተው ገንዘብ መሰብሰብ ስላዘወተሩ ተመልሰው ወደ ግብፅ ተልከዋል::

ከዚሁ ክፍለ ዘመን ሳንወጣ ከእስክንድርያ ወደ ኢትዮጵያ ሊላኩ የነበሩ ጳጳስ ስም ወስዶ አብዱም የሚባል እስላም የሐሰት ደብዳቤ ይዞ አባ ቄርሎስ እባላለሁ በማለት ወደ ሀገራችን መጥቶ የጳጳስ አቀባበል ተደረገ ለት:: በኋላ ቀሳጢነቱ /አታላይነቱ/ ታውቆበት ተይዞ የገዛ ወገኖቹ በዳህላክ በኩል በመውሰድ አንገቱን በሰይፍ ቀሉት:: እንግዲህ ይህን ክፍተት ተመል ክተው አሁን የጠቀስነውን ችግር በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የፈጸሙ ሰዎች ገጥመውናል:: መንፈሳዊ ሥልጣኑን በቅንነት ጥቅማቸውን ወደጐን በማድረግ ለኢትዮጵያ ተወላጆች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ግብፃውያን ፓትርያርኮች ቢሰጡ ይህን ሁሉ አናይም ነበር::

አፄ ቴዎድሮስን ቀብተው ያነገሡ ግብፃዊ ጳጳስ አባ ሰላማ ይባላሉ:: እኝህ ጳጳስ በ10 ሺ ብር ተገዝተው ነበር የመጡት:: በባሕርያቸው ተዟዙሮ መስበክና በሌሎች ክልል የሚገኙትን ዲቁና ቅስና ለመስጠት አልሄድም የሚሉ ነበሩ:: ከዚህ የተነሣ ትንፋሻቸው በስልቻ እየተደረገ ወደ ጐንደርና ጐጃም በመላክ ክህነት ለሚቀበለው ሰው እየተቀነሰ ስለሚነፋለት የስልቻ ክህነት ይቀበል ነበር ይባላል:: [አፄ ቴዎድሮስ በጳውሎስ ኞኞ ገጽ 107]

በአፄ ዮሐንስ ዘመን ከመጡት ከ4ቱ ግብፃውያን ጳጳሳት መካከል 3ቱ በሞት ሲለዩ እስከ ንግሥት ዘውዲቱ ጃሬስ የቆዩት አቡነ ማቴዎስ ናቸው:: በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የዴር ሡልጣን የይገባኛል ጥያቄ በሽምግልና ጠቡን እንዲያበርዱ ወደ ኢየሩሳሌም ቢላኩ ለወገኖቻቸው አድ ልተው ርስቱ የግብፅ ነው በማለት ፈርደው ተመልሰዋል:: በዚህ ድርጊት የተናደዱት እቴጌ ጣይቱ በግዞት ወደ አዲስ ዓለም ማርያም አካባቢ ላኳ ቸው:: እቴጌ ጣይቱ ቀድመው ሞቱ እንጂ አቡነ ማቴዎስ ቀድመው ሞተው ቢሆን ኖሮ በኢትዮጵያ ምድር ላይ እንደማይቀበሩ ቁርጥ ሀሳባቸው ነበር::

የቋንቋ ችግር በተመለከተ ደግሞ በጐንደር ዘመነ መንግሥት መጥተው ከነበሩት ጳጳስ መካከል 22 ብር እየተቀበሉ ቅስና ይሰጡ ነበር:: አንድ ለመቀሰስ የፈለገ ይህን ያህል አልያዘምና ጓደኞቹ ቀስሰው ሲወጡ ይህ ገንዘብ የሌለው ሰው ሁለት ጣቶቹን እንደ ባላ ቀስሮ አባታችን እግዚ አብሔር ያሳይዎ አስገቢው 2 ብር ካልሰጠኸኝ አትቀስስም ብሎ ከለከለኝ እኔ ሁለት ቀርቶ 1 ብር የለኝም ደሀ ነኝ ሲል ሌባ ጣቱን ቀስሮ አሳየ:: አቡኑ ምን ይላል ብለው ቢጠይቁ ሚስቶቹ ሁለት ናቸው በአንዲት ሴት መወሰን አልችልምና በሁለቱ ቅስናይሰጠኝ ይላል አሏቸው:: ጳጳሱም ደንግጠው ቆመው አስደብድበው ከዚህ ከተማ እንዳታድር ብለው ከጓደኞቹ ነጥለው ደሙንና እንባውን እየዘራ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሄዷል:: [ገበታዋሪያ የንባብ መማሪያ ከደስታ ተክለ ወልድ 1928 ዓ.ም. ገፅ 42]

የኢጣልያ ፋሽስት መንግሥት ሀገራችንን ሲወር በ1921 ዓ.ም. ከተ ሾሙት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት መካከል አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤልን በግፈኛው የሞሶሎኒ ወታደሮች በመትረየስ ተደብድበው ሲሞቱ በወቅቱ



www.ethiopianorthodox.org

የነበረው ግብፃዊ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ መንጉቹን ለአውሬ በመተው መሳው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ለእኔ ይሰጠኝ በማለት ሹመት ለመጠየቅ ወደ ሮም ተጓዘ:: ጉዳዩ የማይፈጸምለት መሆኑን ሲያውቅ በዚያው ሀገሩ ግብፅ ገብቶ ቀረ:: ይህ ሁሉ የተመረጡለትን ዓላማ ወደ ጐን በመተው ይልቁንም ከቤተ ክርስቲያናችን ፍላጐት ይልቅ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ የሚያስቀድሙ አንዳንድ ግብፃውያን ጳጳሳት ስናስብ ያስቆጨናል::

## ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ግብፃውያን ጳጳሳት ያደረሱት ችግር አጠቃላይ በርዕስ ተከፍሎ ሲዳሰስ

### 1. በግዴለሽነት ቤተ ክርስቲያንን መጉዳታቸው፤

በ9ኛው መቶ ክፍለዘመን በሀገራችን ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ቅርሶቻችን የወደሙበት፤ ክርስቲያኖች የተሰደዱበት፤ አብያተ ክርስቲያናት የጋዩበት፤ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያው የስደት ዘመን ተብሎ የተመዘገበበት ክፍለ ዘመን ነበር:: ይኸውም በዮዲት ጉዲት አማካኝነት የደረሰ ጥፋት ነው:: የስደቱም ጊዜ 40 ዓመታት ፈጅቷል:: ነገር ግን በዚህ 40 ዘመናት የግብፅ እስክንድርያ ቤተክርስቲያን 6 ፓትርያርኮችን ስታፈራርቅ አንዳቸውም ቤተ ክርስቲያናችንን አስበው የሚያፅናና፣ የሚባርክ፣ አይዟችሁ የሚል ጳጳስ አልላኩልንም:: ከዚያ በኋላ የተላኩትም የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ያስቀደሙ ነበሩ:: ለማስመጣት የሚሔዱትንም ያጉላሏቸው ነበር:: እዚህ ላይ ብዙዎች ግብፃውያን ፓትርያርኮች ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብለው የሕይወት መስዋዕትነት ለምን አልከፈሉልንም ብለን አይደለም:: ኢትዮጵያውያን ክርስቲያናዊ ኃላፊነታቸው አስገድዷቸው መከራውን ታግሰው፣ ጊዜያቸውን ሰውተው ስቃዩን ከምንም ሳይቆጥሩ ግብፅ ደርሰው ያለምንም ውጤት የሚመልሱበት ጊዜ ስለነበር በዚህ ድርጊታቸው ይተቻሉ ይወቀሳሉም ግዴለሾች ናቸውና::

### 2. የኢኮኖሚ አቅሟን ያዳከሙ ናቸው፤

አንድ ጳጳስ ከግብፅ ለማስመጣት ቤተ ክርስቲያናችን ከሚጠበቅባት ነገር/መካከል/ ወርቅ፣ ብር መላክ ነበር:: የሚላከውም ለቤተ መንግሥቱና ለቤተ ክህነቱ ነበር:: ይህም የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወዲያው ጳጳስ እንዲልኩልን ወርቅና ብር ሲሰጣቸው፤ ተመርጦ የሚላክልን ጳጳስ ደግሞ በሰላም ወደ ኢትዮጵያ እንዲደርስ ጠረፍን /ድንበርን/ ለሚጠብቁ እስላሞች ተጨማሪ ወርቅ እንደ እጅ መንሻ ይሰጣቸው ነበር:: ለምሳሌ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን የመጡ አባ ሰላማ በ10 ሺ ብር የተገዙ ሲሆኑ፤ በአፄ ዮሐንስ ዘመን ደግሞ የመጡ 4 ጳጳሳት በ80 ሺ ብር ገዝተው ነበር ያስመጧቸው:: የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቀና መንገድ መንፈሳዊ ስልጣናቸውን ቢጠቀሙበት ኖሮ ቤተ ክርስቲያናችን ይህን ሁሉ መከራ



አታይም ነበር:: ይህም የራሷን ልጆች ጳጳስ መሾም ይችሉ ነበር:: ይህ ሁሉ ጳጳስ ለማስመጣት የምታወጣው ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያናችን ተልዕኮ ቢውል ኖሮ ብዙ ግዳጇን ትወጣበት ነበር::

### 3. ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን አስተጓጉለዋል፤

ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ጳጳሳት ተንቀሳቅሰው እንዳያስተምሩ ቋንቋችንን፣ ባሕላችንን አያውቁም:: በዚያ ላይ የሚቀመጡት በቤተ መንግሥት ክልል ስለሆነ የቤተ ክርስቲያናችን ዜጐች ተገቢውን ወንጌል እንዳያገኙ አድርገዋል:: ለምሳሌ በጃን ስዩም ዘመን በዚህ መጽሐፍ መግቢያ እንደተገለፀው የወገኖቻቸው ችግር እንዲቀል ለማድረግ በግብፅ የሚኖሩ የእስላም ባለሥልጣኖችን ለማስደሰት ብለው አቡነ ሳዊሮስ የተባሉ ጳጳስ መስጊድ አሠርተው ነበር:: እንግዲህ በእነሱ የጥቅም፣ የፍርሀት ተገዥነት ቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን በሚገባ እንዳትወጣ እንቅፋት ፈጥረውባታል::

### 4. ታሪካዊ በደል ፈፅመዋል፤

በአፄ ምኒልክ ዘመን የነበሩ ግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ [እኝህ ጳጳስ 38 ዓመት በኢትዮጵያ የኖሩ ናቸው] በኢየሩሳሌም የሚገኘው ርስታችን፤ የግብጾችን የይገባኛል ጥያቄ ጠቡን በሽምግልና እንዲያበርዱት ወደ ኢየሩሳሌም ተልከው ነበር:: ይህን ሽምግልና ደስ ያላላቸው እቴጌ ጣይቱ «የበግን ግልገል ተኩላ ታሳድገው አይባልም» በማለት ተቃውመው ነበር:: ይህም ለወገኖቻቸው ያደላሉ የሚል አስተሳሰብ ነበር እቴጌ ጣይቱ የነበራቸው:: የፈሩት አልቀረም አቡነ ማቴዎስ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዘው ቦታው የግብጾች ነው በማለት ፈርደው ተመልሰዋል:: እቴጌ ጣይቱ ከዚህ በኋላ ጳጳሱን እንደ አደገኛ የኢትዮጵያ ጠላት እየተመለከቷቸው ኖረዋል:: [የታሪክ መስታወት ልዩ እትም]

### 5. ለቤተ ክርስቲያን መደፈር በር ከፍተዋል፤

በተለይ አብደም የሚባል እስላም ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ ሊላክ የነበረ ቄርሎስ የተባለ ጳጳስ ስም ይዞ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ቄርሎስ እባላለሁ ብሎ የሀሰት ደብዳቤ ለቤተ መንግሥት ባለሥልጣናት አስረከበ:: የጳጳስ አቀባበልም ተደረገለት:: በኋላ አታላይነቱ ተነቅቶበት እንዲያዝ ተደርጐ በዳህላክ በኩል ተወስዶ የገዛ ወገኖቹ አንገቱን በሠይፍ ቀጥተውታል:: እንግዲህ በዚያን ዘመን ሌሎች እምነቶች ቤተ ክርስቲያናችንን ለመድፈር እድሉ ሰፊ እንደነበር እንረዳለን:: ይህም ከአገር ርቀትና ከመገናኛ እጦት የተነሣ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው በሐሰተኛ ጳጳስ ነኝ በማለት በተደጋጋሚ ሊመጣ የሚችልበት እድል ክፍት እንደነበር እንረዳለን::



www.ethiopianorthodox.org

## 6. በሊቃውንቶቻችን ሥነ ልቡና ላይ ተፅእኖ አሳድረዋል፤

የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንቶች በርካታ ድርሰቶችን አዘጋጅተው ቢጽፉም፤ በወቅቱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ ሲኖዶስ ስላልነበራት የቤተ ክርስቲያኒቱም ኃላፊነት በግብፃውያን ጳጳሳት ላይ ወድቆ ስለነበር:: የደረሱት መጽሐፍት ተቀባይነት እንዲኖረው ሲሉ በግብፅና በሌሎች ቅዱሳን አበው ስም ለመሰየም ይገደዱ ነበር:: ይህም ምን ያህል በሊቃውንቶቻችን ሥነ ልቡና ላይ ተፅእኖ አድርገው እንደነበር እንረዳለን [ፍንጭ ፍተሻ በዶክተር ሐዲስ የሻነው ገፅ 30]

## 7. መመዘኛውን ያሟላ ክህነት እንዳይኖር አድርገዋል፤

ትልቁ ጥለውብን የሄዱት ጠባሳ አንዱ ይህ ነው:: ምክንያቱም ገና በጨቅላ አዕምሮና አካል በእናታቸው ጀርባ ላይ ታዝለው ለሚመጡ ሕፃናት የዲቁና፣ የቅስና ማዕርግ ይሰጡ ነበር:: ምንም ከችግር አንፃር ቢሆንም መመዘኛውን ያሟላ ክህነት መስጠት ነበረባቸው:: ለህፃናት ዲቁና ይሰጡና፤ ወደፊት ዲቁና የሰጠው ጳጳስ በሞት ቢለይና ሌላ ተተኪ ጳጳስ ከግብፅ እስከሚመጣ ድረስ የሚወስደውን ጊዜ ከግምት በማስገባት ወዲያው የቅስና ማዕርግ እንዲቀበሉ ያስገድዷቸዋል:: መመዘኛ ያላሟላ በነገረ መለኮት እውቀት ያልዳበረ የክህነት ሹመት እስከ አሁን መቀጠል የዚያን ዘመን ጠባሳ ነበር:: ይህ ድርጊት በኢትዮጵያ በኩል አማራጭ ከማጣት የተነሳም ሲሆን፤ ድርጊቱን በፈፃሚው በኩል ግን መንፈሳዊ ግዴታን ከዘንጋትና በምን ቸገረኝነት ነው::

ከቦታ ርቀት የተነሣ ክህነት ለመቀበል ሲሄዱ በሚደርስባቸው ጉዳት የተማረሩ ብዙ ናቸው:: ለምሳሌ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመን ወገዳ ከሚባል ሀገር 15 ሰዎች ጐንደር ሄደው ቅስና ተቀብለው ሲመለሱ ሽፍቶች ፈንግለው ሸጧቸው:: ከ15ቱ ሦስቱ 2 ጊዜ ተሸጠው በ3ኛው ያንኮበር ነጋዴ ቢገዛቸው አምልጠው አገራቸው በገቡ ጊዜ ከ3ቱ አንደኛው የእኔ ዘር ተምሮ ቄስ ከሆነ ርጉም ይሁን ብለው ስለረገሙ ጕሽውሀ በሚባል ሀገር ልጆቻቸው ፊደል ሳይቆጥሩ ለበርካታ ዓመታት ኖረዋል:: [ገበታዋሪያ የንባብ መማሪያ ገፅ 39]

ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ስለሐዋርያዊ አገልግሎት ከፍተኛ የሆነ ትኩረት በመስጠት ያላቸውን መንፈሳዊ ኃላፊነት ብቃት ላላቸው ኢትዮጵያውያን አባቶች በማጋራት ትልቅ ግዴታ የተወጡት በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት የመጡት አቡነ ያዕቆብን ሳላነሳ አላልፍም:: ከተሰአቱ ቅዱሳን በኋላ የተቀናጀ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት የተካሄደበት በዚህ ጳጳስ ዘመን ነው:: ይህም 12 አባቶችን በመምረጥ በአንብሮተ እድ /እጅን በመጫን/ በመሾም ባርከ በመላው ኢትዮጵያ አሠማርተዋቸዋል:: [ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት 1ኛ መጽሐፍ ገጽ 126-128]



በዚህ መጽሐፍ እስከ አሁን በመጠኑ የጠቀስናቸው ችግሮች በዝርዝር ለማቅረብ ሳይሆን የመጽሐፉን ማዕከላዊ ዓላማ አንባቢ እንዲገነዘብ መንገድ ይሆንልኛል በማለት የሠፈረ ነው:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከተወላጆቿ መካከል ጳጳስ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘችው በ1921 ዓ.ም. ነው:: ከዚህጊዜ ጀምሮ መልእክተኞች ወደ ግብፅ በየጊዜው በመሄድ ጉዳዩን አጠናክሮ በመያዝ ከራሳችን አበው መካከል ጳጳስ ሊቀጳጳስ ብሎም ፓትርያርክ የማንሾምበት ምንም ምክንያት እንደሌለ አፅንኦት በመስጠት መልእክተኞች ለግብፅ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቢገልጡላቸውም እነሱም ባንፃሩ ሲያንገራግሩ በግዝት ሰበብ ሲያስፈራሩ ኖረው በ1951 ዓ.ም. የኙትርክናውን ሥልጣን በእጃችን ለማስገባት ችለናል:: በዚህ መጽሐፍ ይህ በጉልህ ተንፀባርቋል::

ሌላው ቤተ ክርስቲያናችን በመንበሯ የሾመቻቸው አምስት ፓትርያርኮች ዘመነ ሢመት እነማን በማን እንደተሾሙ ጭምር ለግንዛቤ ይረዳናል በማለት አስፍሬዋለሁ:: ይህ መጽሐፍ እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ የነበሩትን አሁን ያሉትን ጳጳሳት በሙሉ የያዘ ነው:: ከእነዚህ መካከል ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ሁለንተናዊ እድገት ያፋጡኑ ከዲቁና እስከ ኙትርክና ማዕርግ የደረሱትን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የሕይወት ታሪክ ከሥራዎቻቸው ጋር አብሮ ቀርቧል::

ያልተማሩትን እየተማሩና የተማሩትን እያስተማሩ ሰብዐዊ ሕይወታቸውን በድንግልና ወስነው በመኖር ለዲቁና፣ ለቅስና፣ ለምንኩስና፣ ለቆምስና፣ ለጵጵስና፣ ለሊቀጵጵስና ብሎም ለፓትርያርክነት ማዕርግ በቅተው በአካሄድ በአነጋገር በትምህርት አሰጣጥ፣ በስብከት አመራር በአመለካከት አንድ ታላቅ የብዙ ምዕመናን አባት ሊያደርግ የሚገባውን አጥልቆ በመከታተል ታላቅ ሐዋርያዊ ተግባር ያከናወኑ አባት በ20ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አፍርታለች:: እኝህም ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ናቸው:: የቅዱስነታቸው የሕይወት ታሪክ በሰፊው ከሠሯቸው ሥራዎች ጋር በመጽሐፉ ውስጥ እናገኛለን:: እኚህ ታላቅ አባት «ሰማዕት» የሚለውን ስያሜ ያገኙት ቤተ ክርስቲያናቸውን በደማቸው ያስከበሩ ሲሆን፤ በሐዋርያዊ ተልእኳቸው ሰፊ ድርሻ አላቸው:: በሀገረ ስብከታቸው ሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት በርካታ መንፈሳዊና ስጋዊ ተግባራትን አከናውነዋል:: ይህም ወደ ክርስትና ሕይወት የሚመለሱ የምእመናን ቁጥር እየበዛ ስለመጣ 12 አብያተ ክርስቲያናትን አሰርተዋል::

በፈፀሙት ሐዋርያዊ የወንጌል ተልእኮ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች አስተምረው ለጥምቀተ ክርስትና አብቅተዋል:: በ1949 ዓ.ም. በባሌ ጠቅላይ ግዛት ባደረጉት የአንድ ጊዜ ጉዞ ብቻ በገደብ አውራጃ:- በዶዶላ፣ በሲሮፍታ፣ በሄቤ፤ በሄቤኖ፣ በኮሶና፣ በጋጣ እየተዘዋወሩ ባደረጉት የወንጌል አገልግሎት፣ 24 ሺህ የአዋማና የልዩ ልዩ እምነት ተከታዮች በማሳመን በማጥመቅ ወደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት አባልነት መልሰዋል:: በ1958 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስር የሚካሄድ የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ድርጅት መስርተው በአዲስ አበባና በሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች እንደ አባትነታቸው እየተዘዋወሩ በአድባራቱና በገዳማትም



www.ethiopianorthodox.org

እየተገኙ ምእመናንና ቤተ ክርስቲያንን በይበልጥ ለማቀራረብ የምእመናኑ ቁጥር እንዲታወቅም ለማድረግ የስብከተ ወንጌል ድርጅት አቋቁመዋል::

ከዚህም ሌላ በመንበረ ፓትርያርኩ የወጣቶች ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት መስርተው በየደብሩ ቅርንጫፍ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር እንዲቋቋምና ወጣቶች በመንፈሳዊ ተግባር በይበልጥ የሚኅለምሱበትንና ከቤተ ክርስቲያን ጋር የሚቀራረቡ በትን መንገድ ከፍተዋል:: ቤተ ክርስቲያንም ከዘመኑ ሥልጣኔ ጋር ጎን ለጎን መራመድ ስለሚገባት ቅዱስነታቸው ዘመናውያን ሰባክያንን ቀሳውስትን ዲያቆናትን በየጊዜው እያሰለጠኑ በመንፈሳዊ መስክ እንዲሰማሩ አድርገዋል:: እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ልጆች ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ አገር እየላኩ ልዩ ልዩ እውቀት እንዲቀስሙና ጊዜው በሚፈቅደው ዘመናዊ ዘዴ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ አድርገዋል:: የውጭ ግንኙነትንም በበለጠ አሳድገዋል:: አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሊያደርግ የሚገባውን ትልቅ ሥራ በአይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ መንፈሳዊ ተግባር ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አበርክተዋል:: የመጽሐፉን ይዘት ለመግለፅ ለመግቢያ ያህል ይህን ካልኩ ቀሪውን በሰፊው ከመጽሐፉ ውስጥ እናገኛለን::

አዘጋጅ ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
1999 ዓ.ም.
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ



# ምዕራፍ አንድ
## መንፈሳዊ ነጻነት ለማግኘት የተደረገ ጥረት

በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ የነበሩት ንጉሥ ተፈሪ በኋላ (ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ) ኢትዮጵያ በሥጋዊ በኩል ያላት ነፃነት የታወቀ እንደመሆኑ መጠን በመንፈሳዊ ረገድ ሙሉ ነፃነት አግኝታ ከተወላጆቿ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ሊቀ ጳጳሳት ለመሾም እንድትችል ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ከደከሙት ነገሥታት አንዱ ናቸው:: የኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ አልጋ ወራሽ በነበሩበት ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያድግና እውቀቱንም እንዲያሰፋ ሲሉ የጽሕፈት መኪና (ማሽን) ከአውሮፓ አሥመጥተው ጋዜጦች፣ አቋቁመው የጽሑፍ ነፃነት በመስጠታቸው፤ በሕዝቡ ልቡና ውስጥ ሲወጣና ሲወርድ የነበረውን የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት በተለ ይም ከተወላጆቻችን የራሳችን ጳጳስ የማግኘት ጉዳይ ለሌላው ለማካፈል ስለተቻለ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ነፃነት ለንዲሰጣትና ከተወላጆቿ መምህራን ጳጳሳት እንዲሾሙ ብዙ ጸሐፊዎች ቁም ነገር የያዘ ሃሳባቸውን በጋዜጣ ገልጠው ነበር::

ይህን የተገለጠውን አስፈላጊ ነገር የተመለከቱ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት መአርገ ጵጵስና ለመቀበል የሚከለክለን ነገር አለመኖሩን ስለተረዱት ከአገራችን ኢትዮጵያ መምህራን እየተመረጡ አንድ ሊቀ ጳጳስና ለአውራጃው የሚሆኑ ብዙ ጳጳሳት ይሾሙልን የሚሉ እየበዙ ሔዱ:: በዚህ መሠረት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ለሊቃውንቱም የሐሳቡን እውነተኛነት በመግለጥ አስረዱ:: በዚህ መሠረት በንጉሥ ተፈሪ የቀረበው መሠረታዊ ሐሳብ በግርማዊት ንግሥት መወደድን ስላገኘ፤ በወቅቱ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ወደ ነበሩት አቡነ ቄርሎስ መልዕክት ላኩ::[1] ፓትርያርኩም

1. ከዚህ መልእክት በፊት አልጋወራሽ ተፈሪ በ1916 ዓ.ም. ግብፅንና የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን ጐብኝተዋል:: በዚያን ጊዜ የነበሩት ፓትርያርክ ቄርሎስ 5ኛ ናቸው:: አልጋ ወራሽ ተፈሪ በብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ አማካኝነት ስጦታ አበርክተውላቸዋል:: ይህም ስጦታ የወርቅ አርባዕቱ ወንጌል፤ የወርቅ መቋሚያና የእጅ መስቀል፤ የሊቀ ጵጵስና አክሊል... ያጠቃለለ ሲሆን፤ ይህ ጉብኝት ኢትዮጵያ ከተወላጆቿ መካከል ለራሷ የጳጳሳት እንዲኖራት የሚያስችላትንና ወደፊት ከቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ጋር ለመነጋገር መሠረት የተጣለበት ነበር:: [እድገትና ነፃነት ገጽ 19-27 ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ገጽ 66-67]/



www.ethiopianorthodox.org

የመላው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት የሃይማኖት ማኅበር የሚጨርሱት ጉዳይ እንጂ በእኔ ብቻ የሚያልቅ አይደለም የሚል ምላሽ ሰጥተው ነገሩን ሳይጨርሱት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: በእስክንድርያ በቅዱስ ማርቆስ መንበር የሚቀመጠው ሊቀ ጳጳሳት እስኪመረጥ አንድ ዓመት ከአምስት ወር ስለቆየ የኢትዮጵያም ጥያቄ መቆየት ግድ ሆኖ ነበር::

ከዚህ በኋላ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ወኪል የነበሩት ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ ለፓትርያርክነት ስለተመረጡ በ1921 ዓ.ም ታህሳስ 7 ቀን መሾማቸው በቴሌግራም ተሰምቶ ነበርና፣ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ያስታወቁትን ቃል መሰረት አድርገው ከኢትዮጵያ መምህራን መካከል ተመርጠው ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳሳት ሆነው እንዲሾሙ ለማድረግና ነገሩን ወደ ፍፃሜ ለማድረስ ወደ አዲሱ ፓትርያርክ ለብፁዕ አቡነ ዮሐንስ መልእክት ላኩ::

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ መልዕክት ሐሳቡን ከመቀበል በስተቀር አጥጋቢ መልስ አልሰጠችም:: ለዚህም የሚከተለውን ገለጡ:- *"ግርማዊነትዎ የላኩትን መልእክት ሰማን በማንኛውም ነገር ለቤተ ክርስቲያኗ የሚስማማ መልካም ባሕርይ ያለው አንድ ጳጳስ ለመሾም ከዚህ በፊት መፍቀዳችን እንደገና እናረጋግጣለን:: የቤተ ክርስቲያን ሕግ የሚፈቅድልን ቢሆን ኖሮ ይህንኑ ሊቀ ጳጳስ ሌሎችን ጳጳሳት ለመሾም እንዲችል አድርገን ብንሾም ደስ ይለን ነበር:: የእናንተ ጥያቄ የቤተ ክርስቲያንን ሕግ የሚያውክ ስለሆነ ጳጳስ ብለን እንድንሾማቸው አንድ እጨጌ ይላኩልን:: ከሊቀ ጳጳሱም ጋር አንድ ሆነው በየክፍለ አገሩ ላለው አገልግሎት የሚረዱ ሁለት የግብፅ ጳጳሶችን እንሾማለን ለሁለቱም ወገን ጥቅም የሚሆነው ንና ደስ የሚያሰኘ ውን ሀሳባችን መሆኑ እናረጋግጣለን:: ሐዋርያዊ ቡራኬያችን ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ለግርማዊነትዎ፣ ለቤተ ክርስቲያን ልጆቻችን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንሰጣለን"* በማለት ላኩ::

ከዚህ መልዕክት እንደምንረዳው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን "ኢትዮጵያ ከተወላጆቿ መካከል ጳጳስ እንዳይሾም" የሚል ሕግ አለ ነው የምትለው:: ይህንን ወደፊት እናየዋለን፣ በዚህ መሠረት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የመለሰችውን ይህን ሐሳብ ንጉሥ ተፈሪ በድጋሚ ከፓትርያርኩ ጋር በአካል ተገናኝተው የሚወያዩ



ሰው ልከው[2] ሐሳቡ ተቀባይነትን አግኝቶ ከእስክንድርያ ፓትርያርክ ከኢትዮጵያ 5 መምህራን ተመርጠው ጳጳስ ሆነው እንዲሾሙ ፈቅዶ የአውንታ መልስ ላኩ::

በዚህ መሠረት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የነገሩን ተቀባይነት ማግኘት ለሊቃውንቱና ለካህናቱ አስታውቀው ጳጳስ ለመሆን የሚገባቸውን በትምህርትና በምግባር የበሰሉ መምህራን እንዲ መረጡ ታዞ አስር አድርገው መረጡ ከእነዚህ መካከል 5 ብቻ እንዲመረጡ አመራረጡም በእጣ እንዲሆን ምክር ተደርጎ በእጣው ላይ 7 ቀን ሙሉ በቤተ ክርስቲያን ጸሎት እየተፀለየበትና ቅዳሴ እየተቀደሰ ቆይቶ ለአምስቱ መምህራን እጣ ወጣላቸው እነዚህም:-

1. መምህር ደስታ፣
2. መምህር ኃ/ማርያም፣
3. መምህር ወልደኪዳን፣
4. መምህር ኃ/ሚካኤል፣
5. እጨጌ ገ/መንፈስ ቅዱስ፣ ናቸው::

ከእነዚህ መካከል እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በጤና መጓደል ምክንያት ግብፅ ሳይሔዱ እዚሁ ቀሩ እኚህ አባት የንግሥት ዘውዲቱ የንስሐ አባት ነበሩ:: ሌሎቹ በግንቦት 2 ቀን 1921 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ተነስተው በባቡር ወደ ጅቡቲ ወረዱ:: ከዚያም ግንቦት 5 ቀን በመርከብ ተሣፍረው ወደ ካይሮ ሄዱ:: በካይሮ 15 ቀን ያህል ከቆዩ በኋላ ግንቦት 25 ቀን እሁድ እለት ለኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት የተመረጡት አንዱ ግብፃዊ ሊቀ ጳጳስ ተብለው ከኢትዮጵያ የሔዱት ከ4ቱ መምህራን ጳጳሳት ተብለው በቅዱስ ማርቆስ መንበር በተሾሙት በአቡነ ዮሐንስ 19ኛ:- ጴጥሮስ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ሚካኤል፣ ተብለው ተሰይመው ተሾሙ:: በሰኔ 21 ቀን 1921 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ፣ በዚህን ጊዜ ከፍተኛ አቀባበል ከቤተ መንግስትና ከቤተ ክህነት በኩል ተደርጎላቸዋል::

በኢትዮጵያና በግብፅ ቤተ ክርስተያን መካከል ያለው ስለጳጳሳት ሹመት ነገር ይህን በመሳሰለው ስምምነትና መግባባት

2. በዚህ ጊዜ ተልከው የነበሩት የትምህርት ሚኒስቴር ዳይሬክተር የነበሩት አቶ ሳህሌ ፀዳሉ ይባሉ ነበር::



www.ethiopianorthodox.org

መንገድ ወደ መልካም ፍፃሜ ደረሰ:: የእስክንድርያው ፓትርያርክ ኢትዮጵያን ጎብኝተው ተመለሱ::[3] የተሾሙት ጳጳሳትም ወደ ሀገረ ስብከታቸው እየሔዱ የመረጡትን መንፈሳዊ ተግባር በትጋትና በንቃት ሆነው ያከናውኑ ጀመር:: ሕዝቡም በፍትሐ ነገሥት "ኢትዮጵያ ከራሷ መምህራን ጳጳሳት አይሹሙ" የሚለው መጽሐፊ እዳ ተፍቆ ከተወላጆቿ ጳጳሳት በማግኘቷ እጅግ ደስ አለው::

### የጳጳሳቱ ስምና ሀገረ ስብከት የሚከተለው ነበር

| የበፊት ስማቸው | የሢመት /የጵጵስና/ ስማቸው | የተሾሙበት አገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| አባ ሲድራስ | አቡነ ቄርሎስ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ | ሸዋን አገርን ይዘው ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ |
| መምህር ደስታ | አቡነ አብርሃም | የጎጃምና የጎንደር ጳጳስ |
| መምህር ወ/ኪዳን | አቡነ ይስሐቅ | የትግሬ ጳጳስ |
| መምህር ኃ/ሚካኤል | አቡነ ጴጥሮስ | የምስራቅ ጳጳስ |
| መምህር ሐዲስ | አቡነ ሚካኤል | የኢሊባቡርና የከፋ ጳጳስ |
| እጨጌ ገ/መንፈስ ቅዱስ | አቡነ ሳዊሮስ | የደቡብ ኢትዮጳያና እጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ |

እዚህ ጋር ልናስተውለው የሚገባን ነገር ቢኖር አሁንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ያልተመለሰ መሆኑ ነው:: ምክንያቱም እንደተመለከትነው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዋናው ጥያቄዋ ጳጳሳት እንዲሾሙላት ብቻ ሳይሆን ሊቀ ጳጳስ ተሹሞላት ይህ የተሾመው ሊቀ ጳጳስ በፓትርያርክነት ማዕርግ እንዲያድግና ሌሎችን ኢትዮጵያውያንን ጳጳስ አድርጎ እንዲሾም ነው:: ግን እላይ እንደተመለከትነው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ አድርጋ የሾመቻቸው ግብፃዊ አቡነ ቄርሎስ ናቸውና::

3. የእስክንድርያው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ በታህሳስ ... ቀን 1922 ዓ.ም ኢትዮጵያን ለመጎብኘት መጥተው ነበር:: በዚሁ ...ት ጥር 1 ቀን ሐሙስ እለት በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ባህታ ...ርያም ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቀድሰው ለጵጵስና ታጭተው ከነበሩትና ወደ ግብፅ ካልሔዱት መካከል እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስን የጵጵስና ቅብአት ቀብተው ስማቸውን አቡነ ሳዊሮስ ብለው ሾመዋቸዋል::



ይህ በዚህ እንዳለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በአልጋ ወራሽነትና ባለ ሙሉ ስልጣን እንደራሴነት ላይ የንጉሥነት መአርግ ደርበው ዓመት ከመንፈቅ ያህል ትልልቅ የመንግስቱን ጉዳዮች ማከናወናቸውን ከቀጠሉ በኋላ በ1922 ዓ.ም ግንቦት 24 ቀን ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ንግሥት ዘውዲቱ ካረፉበት ቀን ጀምሮ የንጉሡ ነገሥቱን ሥራ እየሠሩ ይቆዩ እንጂ የቅብዐ መንግስቱ ሥርዓትና ዘውድ የሚቀዳጁበት ጊዜ ወደ 1923 ዓ.ም እንዲተላለፍ ተደርጎ ነበር:: ይህ የሆነበት ምክንያት ስለ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሞት የሚደረገው ኀዘን ሰፊ ወራት እንዲሰጠው ስለተደረገ ነው::

ቀደም ሲል ንጉሥ ተፈሪ ሲባሉ ቆይተው ንግሥት ዘውዲቱ ከሞቱ ከ7ወር በኋላ ጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ.ም በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ንግሥናቸውን ፈፅመው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው በቅብዐ መንግስት ተቀብተው ነገሡ:: ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ያደረጉ የሀገራችን መሪ ናቸው::

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነፃነት ማግኘት
## ከ1921 - 1951

ይህ ዘመን ለዓመታት ሲደከምበት የነበረው ኢትዮጵያ ከተወላጆቿ መካከል መምህራን ተመርጠው ከኤጲስ ቆጶስነት ወደ ጳጳስ ከዚያም ወደ ሊቀጳጳስ ብሎም ከፍተኛውን የፓትርያርክነት ሥልጣን የተገኘበት ዘመን ነው:: ባለፈው ክፍል እንደ ተመለከትነው ተሹመው የነበሩት 5ቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በየሀገረ ስብከታቸው ሲያገለግሉ ሲደክሙ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግስት ደግሞ አንድ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ተሹሞ እርሱ ሊሎች ጳጳሳትን እንዲሾም ከግብፅ ቤተክርስቲያን ጋር መደራደሩን ቀጠለ:: ይህ በዚህ እንዳለ በ1928 ዓ.ም የአድዋ ጦርነትን ለመበቀል 40 ዓመት ሙሉ ተደራጅቶ በዘመናዊ መሣሪያ ተከናንቦ በግፍ ሊወረን የመጣው የኢጣልያ ፋሽስት መንግስት ድርድሩን እንዲቋረጥ አድርጎ ነበር:: "የአገሩ ሰርዶ በአገሩ በሬ" እንደሚባለው አስቀድሞ የተጠነቀቁለት ነገር



www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ በኋላ ስለሚያገለግል የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ ጳጳሳት በየሀገረ ስብከታቸው ሆነው አገራችንን ለመውረር፣ ሃይማኖታችንን ለማጥፋት፣ ቤተ ክርስቲያንን ለማቃጠል ፋሽስት ስለተነሣ ስለተቀደሰችው ተዋህዶ ሃይማኖታችሁ ደማችሁን አፍስሱ እያሉ ለሕዝቡ ከልብ የሆነ ወገናዊ ምክራቸውን አካፈሉ::

ከ5ቱ ጳጳሳት መካከል ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም በፋሽስቶች እጅ ተይዘው በአደባባይ እንደ ወንጀለኛ የተቆጠሩት የታላቁ ሐዋርያ የቅዱስ ጴጥሮስ ልጅ አቡነ ጴጥሮስ በኔሮን[4] ልጆች በመትረየስ ተደብድበው ሞቱ:: የኢሊባቡሩ ጳጳስ የነበሩትም ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቀዳሚ ሰማዕት የሆኑትን የአቡነ ጴጥሮስን ፍለጋ በመከተል እንደዚሁ በኔሮን ልጆች (በፋሽስቶች) እጅ ተደብድበው በሰማዕትነት አረፉ::

## ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ

**ልደትና አስተዳደግ:-** ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በ1875 ዓ.ም. ሰላሌ /በፊቼ ከተማ/ ተወለዱ አባታቸው ደጃዝማች ዳርጌ ይባሉ ነበር:: ገና ህፃን ሳሉ አባታቸው ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ወስደው ከባሕታዊ ተድላ ተማሪ ቤት አስገቧቸው:: ከዚያ ለጀማሪዎች የተመደበውን የቤተ ክህነት ትምህርት እየተማሩ አደጉ የክርስትና ስማቸው ኃይለማርያም ነበር::

**በትምህርት ቤት:-** በለጋ እድሜያቸው ቅኔ ተምረው ተቀኙ:: እንደገናም ወደ ዋሸራ ሔደው ለመምህርነት የሚያበቃውን ትምህርት ፈፅመው በቅኔ አስተማሪነት ተመረቁ:: ጥቂት ዘመን በጐንደር ዜማ ቀፀሉ:: ከዚያም በኋላ ወሎ /ቦሩ ሜዳ/ ላይ ከታላቁ ሊቅ ከመምህር አካለ ወልድ ብሉያትንና ሐዲሳትን ሊቃውንትንም አደላደሉ:: በ1900 ዓ.ም. በምስካበ ቅዱሳን ገዳም /አማራ ሳይንት/ ገብተው 9 ዓመት ቅኔንና መጻሕፍትን አስተማሩ::

**ምንኩስና:-** በ1909 ዓ.ም. በደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኩሱ:: ወዲያው ማዕርገ ቅስና ተቀብለው በቤተ መቅደስ ተልዕኮ

4. ቅዱስ ጴጥሮስ በ67 ዓመተ ምሕረት በኔሮን ቄሳር በሰይፍ መገደሉን ልብ ይሏል::



ያዙ:: በ1910 ዓ.ም. ወላይታ ደብረ መንክራት ገዳም መምህር ተብለው ከደብረ ሊባኖስ ተሾሙ:: በ1917 ዓ.ም. በዝዋይ ደሴት የገዳሙ መምህር ሆኑ:: በ1919 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ላይ የመንበረ ልዑል ማርቆስ መምህርና በቤተ መንግሥት የራስ ተፈሪ /በኋላ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ/ የንስሐ አባት ሆኑ::

**ጵጵስና:-** በ1921 ዓ.ም. አራት ኢትዮጵያውያን መነኮሳት በእስክንድርያ በቅዱስ ማርቆስ መንበር ካለው ፓትርያርክ ጵጵስና እንዲሾሙ በተደረጉ ጊዜ ከተመረጡት መነኮሳት አንደኛው መምህር ኃይለ ማርያም ነበሩ:: በዚሁ ዓመተ ምህረት ግንቦት 18 ቀን የጵጵስናውን ማዕርግ ሲቀበሉ ስማቸው ጴጥሮስ ተብሎ ተሰየሙ:: ከኢትዮጵያ አውራጃዎች የደረሳቸው ሀገረ ስብከት መንዝና ወሎ ነበር::

**አርበኝነት:-** አረመኔው ፋሽስት በ1928 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ላይ የግፍ ጦርነት ባነሳ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ከጦር ሥፍራ መለየት ስላለሆነላቸው ወደ ሰሜን የጦር ግንባር ዘመቱ:: የኢጣልያ ፋሽስት ማይጨው ላይ በመርዝ ጦርነት በመጠቀሙ የተነሳ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሲበታተን ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ:: በሚያዝያ 24 ቀን ወደ ደብረ ሊባኖስ ሔደው ለሀገርና ለነፃነት መሞት ቅዱስ ተግባር መሆኑን ለሰላሌ አርበኞች ይሰብኩ ጀመር:: የሰላሌ አርበኞችም ወደ አዲስ አበባ ዘምተው ሐምሌ 21 ቀን ጠላትን ሲወጉ እሳቸውም በመካከላቸው ነበሩ::

**በጠላት እጅ:-** ጠላትን ለመውጋት ወደ አዲስ አበባ ዘምተው የነበሩት የሰላሌ አርበኞች ወደ ኋላ እንዲመለሱ የጠላት ኃይል ባስገደዳቸው ጊዜ አቡነ ጴጥሮስ ፊቴን አላዞርም ብለው በአዲስ አበባ ቀሩ:: በሐምሌ 22 ቀን ረቡዕ ወደ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ቤት ሄደው ይኸው አለሁ ብለው አስታወቁ:: የፋሽስት አለቃ ግራዚያኒ ወዲያው ሲጠይቃቸው እንዲህ ብለው መለሱለት «ሰማያዊ ንጉሤ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ምድራዊ ንጉሤም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብቻ ነው:: ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ናት» አሉት:: በዚህ ጊዜ ግራዚያኒ እንደ ሽፍታ ግደሉት ብሎ ትዕዛዝ ሰጠ::

**በሞት ፊት ቀርበው:-** ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በፋሽስት ወታደሮች ተይዘው ወደ ሚገደሉበት ሥፍራ ወደ አራዳ ገበያ



www.ethiopianorthodox.org

ተወሰዱ:: ሲገደሉ ለማሳየት ፋሽስቶች ሕዝቡን በበሰቡት አቡነ ጴጥሮስ ከሚገደሉበት ሥፍራ ሲደርሱ 4ቱን ማዕዘን በመስቀላቸው ባረኩ:: ሕዝቡም ፊት ቆመው እንዲህ አሉ *«ፋሺስት የሀገራችን አርበኞችን ሽፍታ ቢሏቸው እውነት አይምሰላችሁ ሽፍታ ማለት ያለ ሀገሩ መጥቶ የሰውን ርስት የሚቀማ አብያተ ክርስቲያናትን የሚያቃጥል የክርስቲያንን ደም የሚያፈስ ይህ በመካከላችሁ የቆመው አረመኔው የኢጣልያ ፋሽስት ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእርሱ እንዳይገዛ ውጉዝ ነው የኢትዮጵያም መሬት እንዳትቀበለው የተወገዘች ትሁን»* ብለው ተናግረው ሲጨርሱ በመትረየስ ተኩሰው ገደሏቸው::

ምንጭ:- ሐውልታቸው ሲመረቅ የወጣ በራሪ ጽሑፍ፣
አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁ. 5፣
ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን፣

## ብፁዕ አቡነ ሚካኤል

**ልደትና እድገት:-** ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የተወለዱበት ሥፍራ በጌምድር አፈረዋናት ድምበር ወረዳ ልጬ መስቀለ ክርስቶስ ከሚባል-ሀገር ነው:: የጥንት ስማቸው ኃይለ ሚካኤል ነው:: በኋላ ለጳጳስነት ተመርጠው ሲቀርቡ አቡነ ሚካኤል ተብለው በደቡብ ኢትዮጵያ ተሾሙ::

**የትምህርት ቤት ሕይወት:-** ግንድ አጠመም ቅዱስ ሚካኤል ከሚባል አገር በዚሁ በሚጠራው ቤተ ክርስቲያን ክርስትና ተነስተው በዚህ አገርም አድገው ለትምህርት በቅተው ለቁም ነገር በደረሱም ጊዜ መምህር ዋሴ ከሚባሉ አባትና እናታቸው ወስደው እንዲማሩ ሰጧቸው ፊደል ከጀመሩ አንስተው ለድጓ እስኪበቁ ድረስ አንድ ቀን እንደ ልጅ ጥፋት ሳይኖራቸው በመልካም ቁምነገረኝነት ካደጉ ወዲያ ለማዕርገ ዲቁና እንደበቁ፣ መምህራቸው መምህር ዋሴ የዜማ ትምህርት እንዲማሩ መካነ ሰማዕት ገላውዴዎስ ሀገራቸው ስለሆነ መምህር ተድላ ለሚባሉት የዜማ መምህር ሰጥተዋቸው ጸመድጓ ምዕራፍ በሚገባ አደላድለዋል::

**ለጵጵስና ማዕርግ መድረስ:-** ከግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ ዲቁና ቅስና ተቀብለው ቤተ ክርስቲያንን በንፅህና በድንግልና በጥሩ ሕይወት አገልግለዋል:: ግብፅ ወርደው በ1921 ዓ.ም.



ከ4ቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ከአቡነ ይስሐቅ ከአቡነ ጴጥሮስ ከአቡነ አብርሃም ጋር ተሹመው አቡነ ሚካኤል ተብለው ተሰይመዋል:: ግፈኛው የኢጣልያ ፋሽስት መንግሥት ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ሀገራቸውን በአጥንታቸው እሾህነት አስከብበው በደማቸው የኦርቶዶክሳዊትን ቤተ ክርስቲያን ክብር አስጠብቀዋል::

ባሉበት ሀገረ ስብከት ሕዝቡን ሰብስበው ለጠላት እንዳይገዛ በማስተባበር የቤተ ክርስቲያናቸውን ክብር እንዲጠብቁ በማደፋፈር የአርበኝነት ተግባር ሠርተዋል:: ከብዙ ሠራዊት ወንድሞቻቸው ጋር ከሀገር ወደ ሀገር በመዞር ቃለወንጌል በማስተላለፍ ሲፋጠኑ «ሰቢ» ከሚባል ጫካ ላይ ደርሰ የጠላት ጦር ከበባቸው በዚሁ ቦታ አድረው በግስቱ በጠላት ጦር ተያዙ የዚህን ጊዜ:-

**በጠላት እጅና በሞት ፊት መቅረብ:-** *«እኔ የክርስቶስ ባሪያ የሆንኩ አባ ሚካኤል የማውቀው ከላይ በሰማይ በምድር በመላ ፈጣሪዬ ንጉሤ ኢየሱስ ክርስቶስን በምድር ላይ እግዚአብሔር የቀባውን ኃይለ ሥላሴን እንጂ ሌላ ንጉሥ ከቶ አላውቅም:: ይህች ሀገር በእምነት ቅድምናዋ የተነገረላት ከጥንት ጀምራ ወልድ ዋህድ በማለት ጸንታ ፈጣሪዋን ስታመሰግን የኖረች ሀገር ናትና ለሮም ጳጳስና ንጉሥ ልትገዛ አትፈቅድም:: የሚፈቅድም ቢኖር የተወገዘ ይሁን እንኳን ቃሌ አጥንቴ አይፍታው»* ብለው ሲጨርሱ ፋሽስቶች 8 ቀን ሙሉ ሌሊት ከውርጭ ቀን ከፀሐይ አውሎ አሳድሮ አሰንብቶ በፍፃሜ ረፍታቸው ከተማሰ /ከተቆፈረ/ ጉድጓድ ሽለቆ አግብቶ በመትረየስ ደብድቦ ገደላቸው በፊቱኑ የሰማዕትነትን ክብር ይፈልጉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ኅዳር 24 ቀን 1929 ዓ.ም. ምትክ በሌላ ነፍሳቸው ፈርደው በሰማዕትነት አረፉ::

ምንጭ:- ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን፣
- አማርኛ የቤ/ክ መዝገበ ቃላት 1989/1981/ ገጽ 171-178፣

ይህ በዚህ እንዳለ ግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ በዚሁ ዓመት በሐምሌ ወር ዱቼ ሞሶሎኒ ለማየትና አንዳንድ ጉዳዮችን ለመነጋገር መንኰቻቸውን ለአውሬዎች በትነው ወደ ሮም ሔዱ:: በዚህም ጊዜ የኢትዮጵያ ጳጳስ አቡነ አብርሃም ተጠባባቂ ሊቀ ጳጳሳት እንዲሆኑ መርጠው ወኪል



www.ethiopianorthodox.org

ማድረጋቸውን ለመንግስቱና ለቤተክህነቱ ሰዎች አሳወቁ:: አቡነ ቄርሎስ ሮም የሔዱበት ምክንያት የራሳቸውን ስልጣን ለማደላደል፣ ሊቀ ጵጵስናቸውን እንዲያፀድቁላቸው ለመጠየቅ ነበር::[5]

አባ ቄርሎስ ከሮም መልስ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ለመጀመር በመርከብ ተሳፍረው ፓርትሳይድ ሲደርሱ "የእስክንድርያው ፓትርያርክ አለቃዬና አባቴ ስለሆነ አንድ ጊዜ አይቼው ልመለስ" ብለው የኢጣልያን ባለስልጣኖችን ለመኑ:: ልመናቸው ተቀባይነትን አገኘና ተፈቅዶላቸው ካይሮ ከደረሱ በኋላ እንግዲህ ወደ አዲስ አበባ አልመለስም ሲሉ ቆርጠው ተናገሩ:: በዚህን ጊዜ ከፊተኞቹ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በሕይወት የተረፉት አቡነ አብርሃምና አቡነ ይስሐቅ ብቻ ነበሩ:: ይህን ከግምት በማስገባት ኅዳር 21 ቀን በ1930 ዓ.ም የኢትዮጵያ መምህራን ሊቃውንት ተሰብስበው የሚገባውን ጸሎት ካደረሱ በኋላ አቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳስ ሆኑ:: እርሳቸውም ወዲያው በዚያው ቀን አምስት ጳጳሳትና አንድ ኤጲስ ቆጶስ ሾሙ:: እነርሱም:-

| የቀድሞ ስማቸው | የሚመት ስማቸው | የተሾመበት ሀገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| ንቡረ እድ ተክለ ሃይማኖት | አቡነ ዮሐንስ | እጨጌና የሸዋ ጳጳስ |
| መምህር ገብረ አምላክ | አቡነ ማርቆስ | የኤርትራ ጳጳስ |
| መምህር ገብረ አምላክ | አቡነ ሰላማ | የሐረር ጳጳስ |
| መምህር ገብረ መድኅን | አቡነ ማቴዎስ | የወሎ በኋላ የወላሞ ጳጳስ |
| መምህር ገብረ ኪዳን | አቡነ ገብርኤል | የጎንደር ጳጳስ |
| መምህር አካሉ | አቡነ ሉቃስ | የወለጋ ኤጲስ ቆጶስ |

5. አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙን ማርሻል ግራዚያኒ የኢጣልያ ጠላት በሆነው በእንግሊዝ መንግሥት ስር ከምትተዳደረው ግብፅ ካለችው ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ካልገነጠሉ በሊቀ ጳጳስነት ሽፋን የስለላ መረብ ሊፈጠር ስለሚችል በምንም ምክንያት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለማስተዳደር አትችሉም ስላላቸው አቤቱታ ለማቅረብ ነው ይባላል:: አባ ቄርሎስ ሮም ቢሄዱም የኢጣልያ ባለሥልጣናት የግራዚያኒን ውሳኔ በማፅናት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ካልለዩአት ቤተ ክርስቲያኒቱን በሊቀ ጵጵስና መምራት አትችሉም ብሎ ቁርጥ ያለ መልስ ሰጣቸው:: [የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ታሪክ በሉሌ መልአኩ ገጽ 170]



የአቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳስ መሆንና ጳጳሳትን የመሾማቸው ነገር በግብፅ እንደተሰማ የግብፅ ኮፕት ሲኖዶስ በዲሴምበር 28 ቀን 1937 /ታህሳስ 19 ቀን 1930 ዓ.ም/ ስብሰባ አድርጎ በአቡነ አብርሃምና በተሾሙት ጳጳሳት ላይ ውግዘት አስተላለፈ:: በ1930 ዓ.ም. በኅዳር ወር ከየገዳማቱና አድባራቱ የተሰበሰቡ መምህራንና ሊቃውንት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ለማውገዝ የተነሳችበትን የአቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳስ መሆንና ሌሎች ጳጳሳትን መሾማቸውን አግባብ መሆኑን ይህ ጉባኤ መረመረ:: ይኸውም ጉባኤው ጠላት ኢትዮጵያን ሲወር አቡነ አብርሃምን ሊቀ ጳጳስ ለማድረግና ሌሎች ጳጳሳትን እንዲሾሙ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተገደደችበትን ዋና ዋና ነገሮች የሚከተሉት መሆናቸውን አሳወቀ::

1. ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ ኢትዮጵያን ትተው ወደ አገራቸው ገብተው መቅረታቸውን በመመልከት፣
2. ከእስክንድርያ ፓትርያርክና ከግብፃውያን ጋር ለመገናኘት አለመቻሉንና መንገድ በመዘጋቱ፣
3. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ያለ ጳጳስ መኖር የማይገባት መሆኗን በመመልከት ያለ ጳጳስ የቀረች እንደሆነ የመንግስቱ ሃይማኖት ካቶሊካዊ ስብከት የሚያዳክማትና የሚያጠፋት መሆኑን በመገንዘብ፣
4. ከ5ቱ ኢትዮጵያውን ጳጳስ ሦስቱ ሞተው አሁን በሕይወት የቀሩት ሁለቱ ብቻ ስለሆኑና እነርሱ ሳሉ ጳጳሳትን ተክቶ ማቆየት አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣
5. ግብፃዊ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ወደ ሮም ሲሔዱ የሊቀ ጵጵስናው መንበር አቡነ አብርሃምን የወከሉዋቸው መሆኑን በመመልከት አቡነ አብርሃም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ሌሎች ጳጳሳትን እንዲቀቡ ጉባኤው መክሮ የመረጣቸው መሆኑን ገለጠ::

አቡነ አብርሃም በሊቀ ጵጵስና መንበር አንድ ዓመት ከስምንት ወር ከተቀመጡ በኋላ ሐምሌ 14 ቀን 1931 ዓ.ም አረፉ:: ከዚያም በኋላ አዲስ ሊቀ ጳጳሳት ለመምረጥና ለመተካት ከየአገሩ 72 የኢትዮጵያ ሊቃውንት ተመርጠው ተሰበሰቡ እነርሱም እንደ ቤተ ክርስቲያን ሕግ ሰባት ቀን በምህላ ሰንብተው ጸሎት ካደረጉ በኋላ አቡነ ዮሐንስ ተመረጡ:: አቡነ ዮሐንስ መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት



www.ethiopianorthodox.org

ሆነው በኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እጅ ተቀቡ:: እርሳቸውም ወዲያው 5 ጳጳሳትንና አንድ ኤጲስ ቆጶሳት ሾሙ እነርሱም:-

| የቀድሞ ስማቸው | የሢመት ስማቸው | የተመደበበት ሀገረ ስብከት |
|---|---|---|
| ሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ | ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ | የሊቀ ጳጳሳቱ ጸሐፊ |
| መምህር ገብረ ጊዮርጊስ | ብፁዕ አቡነ ጎርጎሪዎስ | የወሎ ጳጳስ |
| መምህር ሳህሌ | ብፁዕ አቡነ ማትያስ | የሸዋ ጳጳስ |
| መምህር ተክለ ማርያም | ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ | የጎጃም ጳጳስ |
| መምህር ወልደ አረጋይ | ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ | የኤርትራ ኤጲስ ቆጶስ |
| አባ ኃይለ ሚካኤል | ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ | የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ |

በዚህን ጊዜ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ቁጥር ከአቡነ ይስሐቅ ጋር 10 ደርሷል ኤጲስ ቆጶሳቱም ሦስት ሆነዋል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በጠላት ወረራ ምክንያት ውይይታቸውን በማቋረጣቸው ከላይ እንደገለፅነው በመከራው ዘመን ችግሩን ተቋቁሞ ሥራውን ያሳቋረጠው መንፈሳዊ ጉባኤው ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን መቀራረብ ጨርሶ አላጠፉም:: በደረሰበት ችግር ምክንያት የተሾሙት ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳሳት ላይ የኮኘት ቤተ ክርስቲያን ከሕገ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ነው ስትል ማውገዟን አይተናል:: እውነት ይሁን ውሸት ባይታወቅም የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የምትለው በ1921 የተሾሙት አራቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትና አምስተኛው ሊቀ ጳጳሳት ግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ ሲሾሙ ውል አለን ነው:: ውሉም:- የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሳታውቀው ሊቀ ጳጳሳት መሾም ቀርቶ ኤጲስ ቆጶስ እንኳ እንዳይሾሙ የፈረሙ መሆናቸውን አሁን ግን ያንን አፍርሰው መሾማቸውን ጠቅሳለች ሲሉ አባ ጎርጎሪዎስ ገልፀዋል:: በመቀጠልም ብፁዕነታቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ ላይ ኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ የወሰደው እርምጃ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን አኳያ ነውር የሌለው መሆኑን አክለው ገልጸዋል::[6]

6. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገፅ 79::



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ሁለት
## በጠላት ወረራ ተቋርጦ የነበረው ግንኙነት እንደገና መቀጠሉ::

በ1934 ዓ.ም የእስክንድርያ ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ የሁለቱን ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ለማቀራረብ መልዕክተኛ ለመላክ አስበው ጥያቄ አቀረቡ:: ለቀረበው ጥያቄ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቅንነት መልስ ተሰጣቸው:: ፓትርያርኩ ግን የስምምነቱን ጉዳይ ከመፈፀሙ አስቀድሞ በጠላት ጊዜ ጥሎ የሔደውን የፊተኛውን ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ መልዕክተኛ ሆኖ ከሌሎች ተከታዮቻቸው ጋር እንዲመጡ አደረጉ:: ንግግር ከተደረገ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትጠይቀው መብት ተገልጦላቸው የቀሩት መልዕክተኞች ሲመለሱ አቡነ ቄርሎስ እዚህ ቆዩ:: የሊቀ ጳጳሳቱን መንበርና ግቢውን ይዘው በሥራ ላይ የነበሩትን ኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳሳት በ1934 ዓ.ም በሰኔ ወር ግቢውን እንዲለቁ ተደርጎ ስለ ትህትና ሲባል የፊተኛው ሊቀ ጳጳስ እንዲገቡ ተወሰነ:: ውግዘት የተላለፈባቸው ጳጳሳትም ከሥራ ታግደው የስምምነቱን ፍፃሜ እንዲጠብቁ ተደረገ::

እንደ አጋጣሚ ፓትርያርክ ዮሐንስ በ1934 ዓ.ም በሰኔ ወር ስለሞቱ ሌላ ፓትርያርክ እስኪተካ ድረስ ብዙ ወራቶች አለፉ:: የእኛም ጉዳይ በዚሁ ዘገየ:: በሁለተኛው ዓመት ማለት በ1936 ዓ.ም ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ተልከው በመጡ መንፈሳዊ መልዕክተኞችና በኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ስም በተወከሉት ተናጋሪዎች መካከል በአዲስ አበባ ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር አዲስ ድርድር ተጀመረ:: በእኛ በኩል ተነስቶ የነበረው ዋነኛ ጥያቄ ከኢትዮጵያውያን አንድ ሊቀ ጳጳስ እንዲሾምና እሱም ሌሎች ጳጳሳትን እንዲሾም ነው:: ለዚህም የቀረበው ምክንያት የአገሩን ቋንቋና ልማድ ባሕል የሚያውቅ ስለሆነ ለኦርቶዶክስ እምነት መስፋፋት ይጠቅማል በማለት ነው ብሏል::

የአገር ተወላጅ ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳስ መኖራቸው ከላይ ለጠቀስነው ጉዳይ ብቻ አይደለም ለብዙ ነገሮች ይጠቅመናል:: ለምሳሌ ፋሽስት አገራችንን ሲወር እንደ አቡነ ጴጥሮስ እንደ

አቡነ ሚካኤል እንደ ደብረ ሊባኖሶች፣ ዜና ማርቆሶች፣ ማኅበረ ሥላሴና እንደቀሩትም የኢትዮጵያ ታላላቅ ገዳማት መሪዎች ሕዝቡን በመከራው ጊዜ በመንፈስ የሚያፅናኑትና በመስዋዕትነታቸው የቤተ ክርስቲያናችንን ክብር የሚያስጠብቁ የአገር ተወላጆችን መሾም አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ጭምር ነው:: ስለዚህ አንድ ሊቀ ጳጳስ ከቤተሰቦቿ ለማግኘት የሚከለክላት በቂ የሆነ ምክንያት አይገኝም::

በዚህን ጊዜ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የሰጠችው መልስ ቢኖር የሊቀ ጳጳሱን መሾም ዋናው የእስክንድርያ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚመለከተው ነው እንጂ እኛ የምንጨርሰው አይደለም:: በጉባኤ ኒቂያ የተጻፈው ስርዋፅ የትርጉም ስህተት እንደ ሆነም በግሪክ ቋንቋ ሊቆች የሆኑ አርቶዶክሳውያን ሊመረምሩትና እውነቱን ሊያገኙት ይችላሉ የሚል መንፈስ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አሰማች::

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ጉባኤ በሚሰበሰብበት ጊዜ የእኛም መልዕክተኞች በጉባኤው እንዲገኙ ተስማሙ:: በዚህን ጊዜ የእኛ መልዕክተኞች እንዲህ አሉ:- ክርስትና በኢትዮጵያ ከመሰበኩ በፊት በ325 ዓ.ም በጉባኤ ኒቂያ ተጻፈ የተባለው የሊቀ ጳጳሱን መሾም የማይፈቅድ ቢሆን በዚያን ጊዜ በጉባኤ ኒቂያ የተሰበሰቡ ሊቃነ ጳጳሳት የሮማ ቤተ ክርስቲያን፣ የአንጾኪያ፣ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለሆኑ በእነ ዚህም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የጉባኤ ኒቂያ መሠረታዊ ጽሑፍ ስለሚገኙ በእነርሱም ምስክርነት ልንስማማበት የሚቻል ነው:: ይህን የመሳሰሉትን ብዙ ጠቃላና ዝርዝር ጉዳዮች የሁለቱ ቤተ ክርስቲያን ወኪሎች ከተነጋገሩ በኋላ ዋናው ጉዳድ በእስክ ንድርያ ዓብይ ጉባኤ እንዲቆረጥ ውሳኔ ተደርጎ መልዕክተኞች ተመለሱ:: የኢትዮጵያም መንፈሳዊ ጉባኤ ከመልዕክተኞች ጋር ያደረገውን ንግግር መሠረት በማድረግ በሰኔ 14 ቀን 1936 ዓ.ም ቀጥሎ የምንመለከተውን ውሳኔ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መቃርዮስ አስተላለፈ::



*መንፈሳዊ ጉባኤ ዘመንግሥተ ኢትዮጵያ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ. ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት*
*ሰኔ 21 ቀን 1936 ዓ.ም አዲስ አበባ*

*የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባለ ስልጣኖች ለብፁዕ አባታቸው ለሊቀ ጳጳሳት አቡነ መቃርዮስ የትህትና ሰላምታቸውን ያቀርባሉ:: በቅዱስ ማርቆስ መንበር ተቀምጠው ይባርኳቸው ዘንድ ስለተመረጡ ደስታቸውን ይገልፃሉ:: ከዚህ በኋላ ቀጥሎ ያለውን አሳብ ሲያቀርቡ ብፁእ አባታቸው አቡነ መቃርዮስ በነገሩ በጣም እንዲያስቡበትና መልካም ፍፃሜ እንዲያስገኙለት ተማፅኖ ነው ነው::*

*ብፁዕ አባታችን ሆይ!*

*ኢትዮጵያ በፋሽስት መንግስት በተወረረችበት ሰዓት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ተለይታ እንድትኖር በጠላት የተመሰረተ አሳብ መሆኑ ታውቋል:: በፊተኞችም ዘመናት ውስጥ በኢትዮጵያ ላይ የጦር አደጋ በደረሰ ቁጥር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር መገናኘትዋ እየተቋረጠባት የመከራ ዘመን እስከሚያልፍ ድረስ ራሷን ችላ መኖሯ የታወቀ ነው:: የመከራውንም ዘመን በደረሰ ቁጥር በማርቆስ መንበር ላይ የተቀመጠውን አባቷን ከመፈለግ አቋርጣ አታውቅም አሁንም ወደፊትም ያላት ምኞት ይኸው መሆኑን ስትገልፅ ደስ ይላታል::*

*ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት ባለማግኘቷ ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ አደጋ በመጣ ቁጥር ለክርስቲያን የሚገባውን ሥርዓት ሁሉ የኢትዮጵያ ምዕመናን ለማድረግ አልቻሉም በዚህም ምክንያት ወደ ሌላ ሃይማኖት የሌዱና የሌላውን ሃይማኖት ባሕል የለመዱ ብዙ ኢትዮጵያውያን ናቸው:: ስለዚህ ወደፊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ማርቆስን አባትነት ሳትለቅ ሃይማኖቷ የሚፀናበትንና ምዕመናኖቿም የሚጠቀሙበትን መንገድ ለመመስረትና ለመከተል ግዴታ እንዳለባት ስለ ተገነዘበች የሚከተሉትን መብቶች በማርቆስ መንበር ላይ የተቀመጡት ቅዱስ መቃርዮስ ባርከው እንዲሰጧት ትለምናለች::*

1. ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ በቤተ ክህነት ክፍል አድገው በሃይማኖት ፀንተው ከሚኖሩት ከመንፈሳውያን አባቶች ለሊቀ ጳጳስነት የሚገባው ሰው ተመርጦ በእስክንድርያው አባታችን ተባርኮና ተቀብቶ እንዲሾምላት::
2. የእስክንድርያው ሲኖዶስ በሚመረጥበት መሠረት የኢትዮጵያም ሲኖዶስ ለጵጵስናና ለኤጲስ ቆጶስነት የሚገቡትን መንፈሳውያን አባቶች እንዲመረጥና ከእስክንድርያ አባታችን ተቀብቶ የመጣው ሊቀ ጳጳሳት ባርኮ እንዲሾማቸው::
3. በማርቆስ መንበር ላይ የሚቀመጠው አባታችን በሚመረጥ በት ጊዜ የቅዱስ ሲኖዶስ በር ለኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን ክፍት እንዲሆን መልዕክተኞቿ በምርጫው ውስጥ እንዲገኙ::



www.ethiopianorthodox.org

4. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር በእስክንድርያው ቅዱስ ሲኖዶስ ውስጥ መንበር እንዲኖራትና ሲኖዶስ በተሰበሰበ ቁጥር መልዕክተኞቹ በሚገባቸው ደረጃ ተቀምጠው እንዲገኙ::

5. ኢትዮጵያ በውድ ሳይሆን በግድ በጦር ኃይል ከእስክንድርያ ጋር እንዳ ትገናኝ ተከልክላ በተቋረጠችበት ጊዜ በሃይማኖቷ ፀንታ ወደ ሰላም ዘመን እስክትደርስ መርጣ የሾመቻቸው ጳጳሳት ከግዝቱ እንዲፈቱላት::

6. በኢትዮጵያና በእስክንድርያ መካከል ያለው የመንፈሳዊ ግንኙነት አሁን ካለው የበለጠ እንዲሆን የእናትነትና የልጅነትም መሠረት የጠነከረ ሆኖ እንዲኖር የገዳም ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ እንዲከፈት ስለዚህም የትምህርት ቤቱ አቋቋምና አካሄድ ቅዱስ አባታችን አቡነ መቃርዮስ ቅዱስ ቡራኬያቸውን እንዲሰጡን:: ከዚህም ትምህርት ቤት ተመርቀው ለጽጽስና ወይም ለቁምስና የታጩት መምህሮች በምስር /ግብፅ/ ገዳማት ውስጥ እየሔዱ ከወንድሞቻችን በኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ሲመጡ በመ ንፈሳቸው ሁሉ የተባበሩ ወንድሞች አግኝተው እንዲመለሱ::

*ከዚህ በላይ በ6ቱ አንቀጾች የተመለከቱት ጉዳዮች ለእስክንድርያና ለኢትዮጵያ አንድነት ዘላለማዊ መሠረት መስለው የሚታዩ ናቸው:: የኢት ዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደሌሎች ኦርቶዶክ ሳውያን ብቸኝነትን አትፈል ግም:: ከእስክንድርያ ጋር በአንድነቷ ፀንታ ለመኖር ስለፈለገች ነው:: በመለያየት የሚመጡትን ምክን ያቶች ሁሉ ለማስወገድ የወደደችው::*

*እነዚህን በስድስቱ አንቀጾች የተመለከቱትን ጉዳዮች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ሆኖባት የቆየችበት ምክንያት ከብፁዕ አባታችን ተልከው ከመጡት ሰዎች ጋር ከተደረገው ጉባኤ የንግግር ማስታወሻ ውስጥ ይገኛል:: ይልቁንም በአንደኛውና በሁለተኛው አንቀፅ ውስጥ የተመለከቱት ዋናዎቹ ጥያቄዎች ለቀድሞው ጊዜ አስፈላጊ አይደሉም ተብለው ተደንግገው እንኳ ቢሆን የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ መንፈስ በፍፁም አልተቀ በለውም::*

*ስለዚህ ብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ የህሳባችን ተካፋይ ሆነው የኢትዮጵያንና የእስክንድርያን መሠረት ለማናወፅ የተነሱ ትንንፋሳት በተሰ ጣቸው በታላቁ ረድኤት ለማስወገድ እንዲደ ክሙበትና እንዲችሉ የኢትዮ ጵያ ቤተክርስቲያን አጥብቃ ታሳስባለች::*[7]

*እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ*
*ዘመንበረ አቡነ ተክለ ሃይማኖት*

የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ይህን የመሰለውን መልዕ ክት ለእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አስተላልፎ ነበር:: ይህን መልዕክት አባ መቃርዮስ ባሉበት ታላቁ የአስክንድርያ ዐብይ ጉባኤ በ1937 ዓ.ም በሰኔ ወር ጉባኤ አድርጎ አንድ በአንድ

7. እድገትና ነፃነት ገፅ 66-68



ተመለከተ:: የብዙ ጊዜ ክርክርም ከተደረገባቸው በኋላ የኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያን ያቀረበቻቸውን ጥያቄዎች አንዳንዶቹን የሚያፀድቅና የሚቃወም ውሳኔ ሰጥቶ ለኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተላለፈ:: የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ከእስክንድርያ መንፈሳዊ ጉባኤ የተላከለት ውሳኔ ለቀረበው ጥያቄ ሙሉ የሆነ መልስና ትክክለኛ ውሳኔ ሆኖ ስላ ልተመለከተው ቀጥሎ የተ መለከተውን የውሳኔ ማስታወቂያ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግስት ገለጠ::

1. በጣሳት ወራሪነት ዘመን አቡነ ቄርሎስ ከጣሳት ባለ ሥልጣ ኖች ጋር ተስማምተው ብዙ ወራቶች ከቆዩ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብፅ ቤተክርስቲያን በታች ናትና በጠቅ ላላው የአስተዳደሩ መብት እንዲሰጠኝ ሲሉ ያቀረቡት አሳብ እዚህ አዲስ አበባ ላይ የማይፈፀምላቸው ቢሆን ይህንኑ አስ ፈፅማለሁ ብለው ለጉባኤው ሳይገለፁ በሊቀ ጳጳሳቱ ሥራ አቡነ አብርሃምን ወክለው በፈቃዳቸው ወደ ኢጣልያ አገር ሔዱ:: በዚያም ህሳባቸው የማይፈፀምላቸው ቢሆን ወደ ግብፅ ገብተው ስለ ቀሩ ቤተ ክርስቲያናችን ከመዘጋቱ በፊት ይል ቁንም ልዩ ልዩ የሆነ ባዕድ ሃይማኖት እየተስፋፋ የተዋህዶ ሃይማኖት እየተዳከመ የሚሔድ ቢሆን በጊዜው ካሉት ባለ ሥልጣኖች አስፈቅደን ሃይማኖታችንን ለመጠበቅና የቤተ ክርስቲያናችንን ችግር ለማቃለል ሥንል በተደነገገ በመንፈ ሳዊ ሥርዓት መክረን ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳሳትን ሾምን:: ይኸ ውም አፈፃፀም ለሃይማኖታችንና ለቤተ ክርስቲያናችን መል ካም አጠባበቅ ከመስጠት ጋር ምዕመኑ በሚገባ እያፅናናን የጠላትን ዘመን በትዕግስት እንዲያሳልፍ የተደረገ ነው እንጂ ከቅዱስ ማርቆስ አባትነት ለመለየት የተደረገ አይደለም ወደ ፊትም ቢሆን ቤተ ክርስቲያናችን በመንፈሳዊ አስተዳደርዋ ራሷን ችላ ከመኖሯ በቀር በሃይማኖት ከቅዱስ ማርቆስ አባትነት የሚለያት የለም::

2. የኮኘት ጉባኤ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቀረበላትን የትህትና ጥያቄዎች በመቀበልና የሚገባትን ክብር በመስጠት ፈንታ እንደዚህ ያለ መልስ መጻፍ የሚያሳዝን ነው:: በዚህም



www.ethiopianorthodox.org

አስተያየት ኮኘቶች የኢትዮጵያን ልጅነት እንዳልፈለጉ አረጋግጠዋል ሊባል የማይቻል ነው:: እንግዲህ እነሱ አባት ለመሆን ሳይፈልጉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የግብፅ ልጅ ልሁን እያለች ልትሽ ቆጠቆጥ የሚገባት አይደለም:: ወደፊትም የቅዱስ ማርቆስ አባትነት ሳይቀር ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም ሥልጣን ያለው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳት ከኢትዮጵያ መንፈሳውያን አባቶች መካከል በሊቃውንት ሲኖዶስ ተመርጦ እንደመጽሐፍ ስርዓት ይሾማል እንጂ ከእንግዲህ ወዲህ ግብፅ የምንሔድበት ጉዳይ የለም:: በዚህም ሙሉ ምክንያት ከዛሬ ጀምሮ ከግብፅ (ኮኘት) ጋር የተለየን ሆነናል:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ የወሰነው ይህ ውሳኔ ከንጉሠ ነገሥቱ መንግስት ቀርቦ ፍፃሜ ያገኘ ዘንድ ጉባኤው ለብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ያሳስባል::[8]

## መንፈሳዊ ጉባኤው ያደረገው ምርመራ

ይህ መንፈሳዊ ጉባኤ በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን የተቋቋመ ሲሆን፣ ብዙ ታላላቅ ነገሮችን የሠራ በጠላት ወረራ ሳይቀር ሥራውን ያላቆመ ከየክፍለ ሀገሩ የተሰበሰቡ ሊቃውንት የሚገኙበት ጉባኤ ነው:: የተቋቋመው መስከረም 8 ቀን 1918 ዓ.ም. ሲሆን፣ ስያሜውን ያገኘው የዚያን ጊዜ ነበር:: የጉባኤው ሰብሳቢ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ /በኋላ አቡነ ሳዊሮስ/ ነበሩ:: ይህ መንፈሳዊ ጉባኤ በጠላት የወረራ ዘመን ችግሩን ተቋቁሞ አልፈረሰም:: እንዲያውም 72 አባላት ያሉት የምርጫ ኮሚቴ አሰባስቦ፣ አቡነ አብርሀምን እሳቸው ከሞቱ በኋላ አቡነ ዮሐንስን /ሐዲስ ተክሌ/ ሊቀ ጳጳስ አድርጎ በችግሩ ዘመን ሾሟል::

ጠላት ኢትዮጵያን ለቆ ከወጣ በኋላ የቤተ ክርስቲያን ሙያ ያላቸውን ምሁራንን በአባልነት አካቶ እንዲሠሩ አድርጓል:: ይህ መንፈሳዊ ጉባኤ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ችግሮችን ፈትቷል:: የተለያዩ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅሙ ደንቦችን

8. ዝኒ ከማሁ 73-74



አውጥቷል:: በጣም የሚታወቀው የሥራው ውጤት በ1934 ዓ.ም መጋቢት ወር የወጣው ደንብ ሲሆን፣ የመጽሐፍ ርዕስ «የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ» የሚል ሆኖ 12 አንቀጾች አሉት:: ብሔራዊ ሲኖዶስ በኢትዮጵያ ከመቋቋሙ በፊት ይህ መንፈሳዊ ጉባኤ የጐላ አስተዋፅኦ ለቤተ ክርስቲያናችን ያደረገ ነው:: ይህ ሁሉ ሲሆን መሥሪያ ቤቱ በታላቁ ቤተ መንግሥት ቅፅር ውስጥ ነበር፤ ጽሕፈት ቤቱ ከቤተ መንግሥት ከወጣ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት ተባለ::[9]

ይህ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ የኮኘት ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው የምታነሳውን ቃል በጥሞና መርምሮታል:: የኮኘት ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ የሚሾመው ሊቀ ጳጳሳት ለዘለዓለም የግብፅ ሰው ብቻ ነው እንጂ ኢትዮጵያዊ መሆን የለበትም ትላለች:: ለዚህም ማስረጃ ከ1ሺ 600 ዓመት የቆየ ልማድ መሆኑን ከማስታወቅ በላይ ከቅዱሳን አበው ከሠለስቱ ምዕት በጉባኤ ኒቂያ ተጽፎ የተወሰነ ነው ስትል ሀሳቧን በየጊዜው ታስታውቃለች::

የዘመን ብዛት ልማድን ወይም ሥርዓትን ከማሻሻል የሚያግድ አይደለም:: ብዙ ዘመን የኖረው የኦሪት ሥርዓት እንዳይሻሻል የዘመኑ ብዛት አላስገደደውም፤ እንዲሁም ደግሞ በልዩ ልዩ አምልኮት የሚኖሩ አረማውያን አሁን በወንጌል ሲያምኑ የዘመኑ ብዛት ሥርዓት ሆኖ አላስገደዳቸውም:: ይህን የመሰለ ብዙ ምሳሌ ይገኛልና ነገሩን በአጭሩ መተው አስፈላጊ ነው:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በፈቃድዋ ትሠራበት የነበረውን ልማድ አሁን ደግሞ በፈቃድዋ ታሻሽለው ዘንድ የሚገባት ሆነ:: ምክንያቱም የቀድሞው ልማድ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ብርቱ ጉዳት የሚያደርስባት መሆኑ በሚከተሉት ነገሮች ማወቅ ይቻላል:-

9. የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ 1934፤ ዶክተር ሐዲስ የሻነው ፍንጭ ፍተሻ 1998፤ ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም M.A የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ታሪክ ክፍል ሁለት ::



www.ethiopianorthodox.org

- የሕዝቡን ቋንቋ የማያውቁና በሕዝቡ ቋንቋ የማይሰብኩ፣
- በቤተ ክርስቲያናችንና በአገራችን ላይ አደጋ በደረሰ ጊዜ ጥለው የሚሸሹ፣
- የኢትዮጵያ ሰዎች ከራሳቸው ሰዎች ሊቀ ጳጳሳት አይሹሙ የሚለው ለጥቅም ሲባል የተፈጠረ በመሆኑ
- ቃሉ በሌሎች ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ስለማ ይገኝ፣
- የክርስትና እምነት የዘርና የወገን ልዩነት ስለማያደርግ፣
- ኢትዮጵያ ክርስትናን በይፋ የተቀበለችው ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ ስለሆነ ከማመኗ በፊት የኒቂያ ጉባኤ ይህን አይነት ውሳኔ እንደማያወጣበት የታወቀ ስለሆነ ነው::

ከሁሉም በላይ አስገራሚ የነበረው ኢትዮጵያውያን እንዳ ይሾሙ በግብጾች የተጣለውን እገዳ እንዲነሣ በቀረበው ጥያቄ ላይ የነበረው የሀሳብ ልዩነት ነው:: በዚህ ጥያቄ ላይ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አሉታዊ አቋም ነበራቸው:: ለነበ ረው አሉታዊ አቋም ሁለት ምክንያቶች ይቀርባሉ::

1. ከየዋህነት በመነጨ አስተሳሰብ፣ የግብጾች አባባል ስህተት አይደለም ብሎ እውነተኛ አድርጎ መቀበል፣
2. ከራስ ወዳድነት በመነጨ አመለካከት ላይ የመሠረተ፣ ይህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በማኅበራዊ ሕይወ ታቸው ደናግል መነኮሳትና ዓለማውያን ተብለው በሁለት ይከፈላሉ:: በድንግልና የሚኖሩ ሊቃውንት ጵጵስና ተፈቅዶ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት መካከል ጳጳሳት በምርጫው ቢሾሙ ተወዳዳሪ ሆኖ የመቅረብ እድል ስለሚኖራቸው በጥያ ቄው ላይ ተቃውሞ አልነበራቸውም:: ነገር ግን ዓለማውያኑ /በህግ ያሉ/ ትዳር መሥርተው ስለሚኖሩ ለጵጵስና አይታ ጩም:: በዚህ መካከል ጳጳሳት እንዳይሾሙ የሚል ተቃራኒ አቋም ሊኖራቸው ችለዋል በማለት ይህን ጉዳይ ያጠኑ የቤተ ክርስቲያናችን ምሁራን ገልጸዋል:: [ፍንጭ ፍተሻ በዶክተር ሐዲስ የሻነው]



## ምዕራፍ ሦስት
## በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ስምምነት መደረሱ

ለዚህ ዐብይ ነገር በወቅቱ የነበሩት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከፈተኛ ትኩረት ስለሰጡት ጉዳዩ የቤተ መንግስት ጭምር ሆኖ ነበር:: በኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በኩል ያለው የጋለ ስሜት ወደ ትዕግስት እንዲመለስ የቤተ መንግስት መል ዕክተኞች ለጉባኤው ምክራቸውን አካፈሉ:: ከዚህ በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ካይሮ በሚገኘው ኤምባሲያቸው በኩል መነጋገር ጀመሩ:: በዚህም ሁኔታ ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ጋር በመ ነጋገር ብዙ ጊዜ ቆይተው ከሁለት ዓመት ድካም በኋላ እግዚአ ብሔር በፈቀደ ጊዜ ሐምሌ 6 ቀን 1940 ዓ.ም ነገሩ ወደ ስም ምነት ደረሰ:: የሚቀቡት የኢትዮጵያ መምህራን ሐምሌ 16 ቀን 1940 ዓ.ም ከአዲስ አበባ እንዲነሱና የመቀባታቸውም ሥርዓት ሐምሌ 18 ቀን እሁድ በእስክንድርያ ፓትርያርክ እንዲፈፀም ተወስኖ የተመረጡት ብፁአን አበው ሐምሌ 15 ቀን ንጉሠ ነገሥቱን ተሰናብተው ወደ እስክንድርያ ሔዱ:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስተያን የእነዚህን ብፁአን አበው አየራዊ ጉዞ ተቃንቶ የሔዱበት አሳብ ተከናውኖ በደህና ደርሰው እን ዲመለሱ በኀዘንና በጸሎት ሰነበተች የሔዱት አበው የሚከተ ሉት ናቸው:-

1. ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ወልደ ፃድቅ፣
2. መምህር ገሪማ ወልደ ኪዳን፣
3. ሊቀ ሥልጣናት መልዕክቱ ወልደ ማርያም፣
4. መምህር ዘፈረ ብርሃን ገብረ ጻድቅ፣
5. መምህር ጌታሁን ወልደ ሐዋርያት ናቸው::

### የሢመቱ ሥነ ሥርዓት በካይሮ

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ 2ኛ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ደስ የሚያሰኝ ሽልማት ልከውላቸው ስለነበር ስጦታው በባለ ስልጣኖች በኩል ሐምሌ 17 ቀን ቅዳሜ ለመስጠት ወደ ቀጠሮው ሔዱ በትረካናው



www.ethiopianorthodox.org

በግብፅና በኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ አጊጦ ነበር ፓትርያርኩም ከጳጳሳትና ከታላላቅ ሰዎች ጋር ሆነው ተቀበሏቸው ሽልማቱን አቅርበው ባስረከቡት ጊዜ የ69 ዓመት እድሜ የነበራቸው ፓትርያርኩ ደስ ስላላቸው ወዲያው ላንቃ ካባውን ለብሰው ኒሻኑን አድርገው ፎቶ ግራፍ ተነሱ::

## የአስኬማ ጸሎት

አስኬማ ማለት በመጽሐፈ ምንኩስና ከሚገኙት ከሦስቱ የምንኩስና ማዕርጎች አንደኛው ነው:: ሦስቱም ማዕርጋት:- ቆብዕ፣ ቅናት፣ አስኬማ ናቸው:: እነዚህም መጻሕፉ:- ቆብዕ ዘሠለሥቱ ደቂቅ፣ ቅናት ዘዮሐንስ መጥምቅ፣ አስኬማ ዘኤልያስ ብሎ ይደለድላቸዋል:: ሊቃውንት ግን:- ቆብን በአክሊል ሦክ፣ ቅናትን በሐብለ ተቀስሮ፣ አስኬማን በንፅህ መላዕክት፣ መስለው ይናገሯቸዋል::

ሐምሌ 17 ቀን ቅዳሜ ቅዱስ ፓትርያርኩ ለጳጳሳቱ የሚገባውን የአስኬማ ጸሎት የሚያደርሱ ስለሆነ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ በ16 ዲያቆናት ታጅበው ገቡ:: ፓትርያርኩ በመንበራቸው ላይ ሆነው የአስኬማውን ጸሎት ሲጀምሩ የጵጵስና ማዕርግ የሚቀበሉት ጳጳሳት በወለሉ ላይ በወንበር ተራ በተራ ተቀመጡ:: ከገዳመ ሱርያን የመጣ ቴዎፍሎስ የተባለ አንድ መነኩሴ በዚሁ ቀን የጵጵስና ማዕርግ እንዲቀበል ተመርጦ ኖሮ ከ5ቱ ኢትዮጵያ ውያን ጋር ስድስተኛ ሆኖ ተቀመጠ:: ፓትርያርኩ የ6ቱን ጳጳሳት ስምና የሀገረ ስብከታቸውን ስም እየጠሩ ረጅም ጸሎት አድርገው ከባረኳቸው በኋላ አስኬማውን ለያንዳንዳቸው አጠለቁላቸው:: አምስቱ የኢትዮጵያ ጳጳሳት ገና አዲስ አበባ ሳሉ የታሰበላቸውንና እነሱም ጭምር በጸሎት የመረጡት ስም ስለነበር ለፓትርያርኩ ቀደም ብሎ ተነግሮአቸው ነበርና በዚያው ስም ሰየሟቸው:: ይህም:-

1. ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ስም "ባስልዮስ"፣
2. የመምህር ገሪማ ስም "ሚካኤል"፣
3. የሊቀ ስልጣናት መልዕክቱ ስም "ቴዎፍሎስ"፣
4. የመምህር ዘፈረ ብርሃን ስም "ያዕቆብ"፣
5. የመምህር ጌታሁን ስም "ጢሞቴዎስ" ተባለ::



## ሢመተ ጵጵስና

ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም እሁድ በበትረካና በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን እንደሚፈፀም ተደርጎ (ተነግሮ) በበትረካና ተገኙ [በትረካና ማለት ፓትርያርኩ የሚቀመጥበት ሥፍራ ወይም የፓትርያርክ ግቢ ማለት ነው] በግቢውም የቅዱስ ማርቆስ ደብር ተሰርቶበታል:: ቅዳሴው በ3 ደረጃ የተመደበ ነው:: መጀመሪያ ደረጃ ቀዳስያኑ በንዋየ ቅድሳት ላይ የሚጸለየውንና ሌሎች የጸሎት ንዝ የሚፈፀምበት ነው፤ ሁለተኛው ደረጃ የምንባባት ክፍል ይባላል ይህም እስከ ፍሬ ቅዳሴው ያለው ነው:: ሥርዓተ ሢመት የሚያደረጉትም በዚሁ ጊዜ ነው:: የቅዳሴው ጸሎት ከሁለተኛው ደረጃ በደረሰ ጊዜ የጵጵስና ልብስ ያጌጡ አምስቱ ጳጳሳት በአንድ ጳጳስ እየተመሩ መጥተው ኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አጅበው ወሰዷቸው::

አዳዲሶች ጳጳሳት በመቅደሱ በር ላይ ፊታቸውን ወደ ምስዋዑ እያደረጉ በወንበር አስቀመጧቸውና ቅዱስ ፓትርያርኩ የእያንዳንዳቸውን ስምና ሀገር ስብከታቸውን እየጠሩ ሲባርኳቸው መዘምራኑ በረጅም ዜማ አሜን! እያሉ ተቀበሉ:: በመጀመሪያ ክፍል ጸሎት አዲሱን የጵጵስና ቆብ ባርከው ደፉላቸው በሁለተኛው ክፍል ከአዲስ አበባ ተይዞ የሔደው የወርቁን ካባ ላንቃ ባርከው አለበሷቸው የሹመቱ ጸሎትና ሥርዓት ካለቀ በኋላ ጳጳሳቱ ወደ መቅደስ ገቡ:: ፓትርያርኩ ገባሬ ሰናይ ካህን ሆነው ቅዳሴ ባስልዮስን ቀደሱ::

በዚህም ጊዜ 7 የግብፅ ጳጳሳትና 5ቱ የኢትዮጵያ ጳጳሳት፣ ቆሞሳትና ዲያቆናት ተራድያን ሆነው አብረው ቀደሱ:: በዚህ የሢመት ቀን ወደ 30 የሚደርሱ ልዑካን አብረው ቀድሰዋል:: ቅዳሴው ተፈፀመና ከቅዱስ ቁርባን በኋላ ፓትርያርኩ መስቀል ይዘው በአዳዲሶች ጳጳሳት አፍ ላይ "ንስኡ መንፈስ ቅዱስ" እያሉ በንፍሐት ሀብተ መንፈስ ቅዱስ አሳደሩባቸው:: ከዚህ በኋላ ስርሆተ ሕዝብ ሆነ:: የግብፅ መንግስት ሙዚቀኞችን አሰልፎ አጀባቸው፤ ቀጥሎም የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር አሰሙና ለጳጳሳቱ ሰላምታ አቀረቡ:: ጳጳሳቱም ከዚህ በኋላ ወደ ፓትርያርኩ ቤት ገቡ:: ሕዝቡ በሆታ ደስታውን ገልጦ በየቤቱ ሔደ::



www.ethiopianorthodox.org

## ጉብኝት በእስክንድርያ

የቅዱስ ማርቆስ አፅመ ርዕሱ የሚገኝበት መቃብር በእስክንድርያ ስለሆነ ይህን ስፍራ ለመሳለምና ከቅዱስ በረከቱ ለመሳተፍ አምስቱ ጳጳሳት ወደ እስክንድርያ ወረዱ ሟት በትልቁ የቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን መስዋዕት አቅርበው በኢትዮጵያዊ ሥርዓት "ቅዳሴ ባስልዮስን" ቀደሱ:: ከዚህም በኋላ ለገዳሙ እርዳታ 30 ፓውንድ ሰጥተው ለነዳያን ቸርነት አድርገው ወደ ካይሮ ተመለሱ::

## ኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳት ወደ አገራቸው መመለሳቸው

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመንበረ ማርቆስ ያላትን መንፈሳዊ ግንኙነት ሳታቋርጥ የሚገባትን መብት እንድታገኝ ከ1921 ዓ.ም ጀምሮ የሠሩት ሃይማኖታዊ ሥራ ከፍተኛ በመሆኑ በ1921 ዓ.ም ኢትዮጵያ ከልጆቿ ጳጳሳት ለማግኘት ቻለች:: እነዚህም ጳጳሳት እንደ ፋና እያበሩ በዚያ የጨለማ ሰዓት በደረሱ ጊዜ አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል በቃላቸው የዘሩትን የሃይማኖት ተክል በደማቸው አፀደቁት:: ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን የሚገባትን መብት እንድታገኝ በሰፊው ሲደክሙ ከቆዩ በኋላ እነሆ ድካማቸው ፍሬ አስገኝቷል::

ይህ ሁሉ መልካም ምኞትና ሃይማኖታዊ ተስፋ ደርሶ ብፁአን አባቶች ወደ ግብፅ ተልከው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም ተሾመው ሐምሌ 22 ቀን በዚሁ ዓመት ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል:: በዚህን ጊዜ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በቤተ መንግስታቸው በክብር ተቀብለው የሚከተለውን ተናግረዋል:- *"የኢትዮጵያ ታላቅነትና የሥልጣኔ እድገት ከሃይማኖት ትልቅነቷ ጋር የተባበረ እንዲሆን ያስፈልጋል:: ሃይማኖት የሌለበት ሥፍራ ምንም አይነት ኃይል ቢገኝ ምንም አይነት ሥልጣኔ ቢኖር ሥልጣኔውም በግፍ የተሸፈነ ኃይሉም በግፍ የታወረ ይሆናል:: የሃይማኖትንና የበጎ ምግባርን ትምህርት ለማስፋፋት ከባድ አደራ ያለበትን ኃላፊነት ተቀብላችሁ የሐዋርያነት ሥራችሁን ስትጀምሩ በእግዚአብሔር የምትፈፅሙትና ሰማያዊ ክብር የሚያስገኝላችሁ ሥራችሁ በመልካም*



*እንዲከናወንላችሁ እንለምናችኋለን"* በማለት ተናገሩ::[10] ለአምስቱም ጳጳሳት ለቤተ ክርስቲያን ማዕርግ ማረጋገጫ የሚሆን "አንበሳ ወፅአ እምገዳም ውእቱኬ ወልደ አምላክ ውእቱ" የሚል ጽሕፈትና 2ት ሥዕለ አንበሳ ያለበት በትረ ጳጳሳትና የወርቅ መስቀል ሸልመዋቸዋል::

## የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳት መሾም

ለሁሉም ጊዜ አለው ብሎ ንጉሥ ሰሎሞን እንደ ተናገረው ለ1ሺ 600 ዓመታት ያህል ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ የሚያመላልሰን ጉዳይ መፍትሔ ያገኘንበት በዚህ ወርቃማ ዘመን ነው:: ቀደምት ነገሥታት በተለይ ቅዱስ ሐርቤ እና ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ ይመኙት የነበረው ቅዱስ ምኞት ወደ መጨረሻው ግብ ደርሶ የመፈፀሙ እድል ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና በዘመኑ ለነበረው ትውልድ ሆነና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ የምትኖርበት ጊዜ ደርሶ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር በደረሰችው ስምምነት በቤተ ክርስቲያን ሕግ ጳጳስ እንደ ሥጋዊ ሹመት መዘዋወር ስለ ማይገባው የፊተኛው ሊቀ ጳጳስ ግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ የስም ሥልጣናቸውን ይዘው እንዲቆዩ በእስክንድርያ ከተቀቡት ጳጳሳት ውስጥ አንደኛው ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያን ሊቀ ጳጳሳት መንበር በእንደራሴነት እንዲጠብቁ ከአቡነ ቄርሎስ እረፍት በኋላ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ተመርጦ በእስክንድርያ ፓትርያርክ እንዲሾሙ እሱም ጳጳሳትን የመሾም ሥልጣን እንዲሰጠው ነበር::

በጥቅምት 11 ቀን 1943 ዓ.ም የፊተኛው ሊቀ ጳጳስ ግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ ታመው አረፉ:: ከ5ቱ ኢትዮጵያውያን መካከል አንድ ሊቀ ጳጳስ ለመሾም ምርጫ ለማድረግ ተወሰነ በምርጫው መሠረት በታህሳስ 30 ቀን 1943 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ መመረጣቸው ታወቀ:: በዚህ መሠረት ወደ ግብፅ ሔዱ:: ብፁዕነታቸውን ተከትለው ከሔዱት ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ አንዱ ናቸው::

10. ዝኒ ከማሁ ገፅ 98



www.ethiopianorthodox.org

## ሢመተ ሊቀ ጵጵስና በካይሮ

ጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም ሢመተ ሊቀ ጵጵስናው ሥነ ሥርዓት በማርቆስ ቤተ ክርስተያን እንደሚፈፀም በጋዜጦች ተጽ ፈው ስለነበር የእስክንድርያ ፓትርያርክም ለብዙዎች ታላላቅ ሰዎች ጥሪ አድርገው ነበር:: በሢመቱ ላይ ብዙ ሕዝብ ተገኝቶ እንደ ነበር ታሪክ ያስረዳናል:: ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ 2ኛ ገባሬ ሰናይ ቀዳሽ ሆነው ከ6 ሜጥሮጶሊሶችና ከ4 ጳጳሳት ጋር ሥርዓተ ቅዳሴውን ጀመሩ:: ከጸሎተ ወንጌል ጋር ሲደርሱ መጽ ሐፈ ሢመቱን እያነበቡ በአንብሮተ እድ ሥርዓተ ሢመቱን ሲፈ ጽሙ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በመንበሩ ፊት በወንበር ተቀምጠው ነበር::

ፓትርያርኩ በረጅም ድምፅ *"ባስልዮስ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግስት ሊቀ ጳጳስ ነው የመንፈስ ቅዱስ በረከት ይደርበት"* እያሉ በመስቀል እየባረኩ ሦስት ጊዜ በዜማዊ አነጋገር ለሕዝቡ አሰሙ፤ በቅብዐቱም ጊዜ የጸሎቱ ተካፋይ የነበሩት የሀገረ ስብ ከታቸው ሊቃነ ጳጳሳት ነበሩ:: ይህን ከፍተኛ ማዕርግ ተቀብለው ጥር 11 ቀን 1943 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ:: አቡነ ባስ ልዮስ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ለመሆን በቁ፤ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ነሐሴ 27 ቀን 1943 ዓ.ም አምስት ኢት ዮጵያውያን ጳጳሳትን፤ ግንቦት 16 ቀን 1945 ዓ.ም ሦስት ጳጳሳትን፤ ሐምሌ 21 ቀን 1948 ዓ.ም አንድ አጠቃላይ 9 ጳጳስ ቀብተው ሾመዋል:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት በማይናወጥ መሰረት ላይ ተጥሎ አስተማማኝ ደረጃ ላይ ደረሰ::

ቀደም ብሎ እንደተገለጠው እነዚያን ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ቀብተው የሾሙ አባ ዮሳብ የተባሉት የእስክንድርያ መንበር ፓትርያርክ እንደነበሩ ተገልጧል:: ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳሳትን በመሾማቸው ለብዙ ዘመናት ይዘነው የነበረ ውን ሥልጣን ለኢትዮጵያውያን አሳልፈው ሰጡብን በማለት ግብጾች አባ ዮሳብን በጣም ጠልተዋቸው በየምክንያቱ ይከሷቸው ጀመር:: በመጨረሻም መስከረም 12 ቀን 1948 ዓ.ም በተሰበሰ በው በግብጾች የጳጳሳት ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ከመንበራቸው ተነስተው ወደ ደብረ ቁስቋም ገዳም ተላኩ:: በዚህን ጊዜ ነው ኢትዮጵያ መልዕክተኞቿን ልካ ከፍተኛ ተቃውሞን የገለጠችው::



በአባ ዮሳብ ከሥልጣን መባረር ኢትዮጵያ የተቃወመችባቸው ዝርዝር ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው::

1ኛ. አባ ዮሳብ ለፓትርያርክነት በተመረጡ ጊዜ ኢትዮጵያም በተወካይዋ አማካይነት የምርጫው ተካፋይ ሆና ነበር:: በምርጫና በሹመታቸው ላይ ተካፋይ የነበረች እንደመሆንዋ እርስዋ ሳታውቀው ሊሻሩ ባልተ ገባም ነበር መብቷ ሥላልተ ጠበቀላት፤

2ኛ. የአባ ዮሳብ ፓትርያርክነት ለግብፅ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያም መሆኑ እስከታመነበት ድረስ ጉዳዩ ለኢትዮጵያ ሳይቀርብና ሐሳብዋ ሳይጠ በቅ የሁለቱ አገሮች የጋራ ፓትርያርክ ግብጾች ብቻቸውን ሊሽሩአቸው ስለማይገባ፤

3ኛ. የኢትዮጵያ ጳጳሳት በእስክንድርያው መንበር ሥር የነበሩ እስከሆነ ድረስ የእስክንድርያው መንበር የሲኖዶስ አባሎች መሆናቸው የታመነ ነው:: ይሁን እንጂ ፓትርያርክን ከመንበሩ ማስነሳት ለሚያህል ከፍተኛ ጉዳይ ሳይጠሩ ቀርተዋል:: የኢትዮጵያ ጳጳሳትም መብት ስላልተከበረ፤

4ኛ. ፓትርያርኩ የተከሰሱበት ጉዳይ በቤተ ክርስተያን ቀኖና መሠረት ከፓትርያርክነት ማዕርግ የሚያስወርድ ባለመሆኑ በእነዚህ ምክንያቶች ተቃውሞዋን ገልጣለች::

ግብጾች እነዚህን የመቃወሚያ ምክንያቶች ባቀረቡላቸው ጊዜ መልስ ስላጡ የግል ጉዳያቸው እንደመሆኑ መጠን በዚህ ጉዳይ ውስጥ የሌላ አገር ሰዎች ምንም የሚያገባቸው ምክንያት እንደሌለ ገልፀዋል:: ይህን አባባል በውይይቱ ላይ በግልጥ ባይ ናገሩትም እንኳ የተለያዩ ጋዜጦቻቸው በዐምዶቻቸው ላይ ሀሳ ባቸውን ገልጠው ቸዋል:: የጳጳሳትና የመኳንንት አባሎች የሚ ገኙባቸው የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ሁለት ጊዜ ግብጽ ተልከው ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች ጋር ብዙ ውይይት አድ ርገዋል::

በግንቦት ወር 1948 ዓ.ም የግብፅ ሲኖዶስ እንዲሰበሰብ ለጳጳሳት ጥሪ ተላለፈ:: በዚህ ስብሰባ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትም ተጠርተው ነበር:: ይህን ጥሪ ያስተላለፉት ፓትርያርኩ አቡነ ዮሳብ ተባረው በተቀመጡበት በቁስቋም ገዳም ነበር:: በዚህ ስብሰባ ላይ 7 ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ተገኝተዋል:: የጳጳሱ ደጋ ፊዎች የነበሩ ግብጻውያን ጳጳሳትና እንዲሁም ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በአንድነት ስለተሰበሰቡ ምልአተ ጉባኤው የተሟላ ሆነ:: የተሰበሰቡት ጳጳሳት በስብሰባው ካልተገኙት ጳጳሳት የበለጠ



www.ethiopianorthodox.org

ብዛት ነበራቸው በዚህም መሠረት ይህ ጉባኤ ፓትርያርኩ የተባረ ሩበትን ውሳኔ ሽሮ ወደ መንበራቸው እንዲመለሱ መወሰኑ በወቅቱ በአስተርጓሚነት የሔዱት አቶ አስራት ገብረ ማርያም ገልጠዋል::[11]

በውሳኔው መሠረት ፓትርያርኩ ወደ መኖሪያቸው ተመልሰው ሊገቡ ሲሉ የፓትርያርኩ መኖሪያ በፓሊስ እየተጠበቀ መሆኑን ስለሰሙ ወደ ኮኘት ሆስፒታል ሔደው በሕክምና እየተረዱ ቆዩ:: ከሰኔ 17 ቀን 1948 ዓ.ም ጀምሮ በሆስፒታል ቆይተው ሕዳር 4 ቀን 1949 ዓ.ም ዐረፉና አስከሬናቸው በፓትርያርክነት ክብር ተቀበረ:: ይህ ሁሉ እንግዲህ ለምን ለኢትዮጵያውያን የሊቀ ጵጵስና ማዕርግ ሰጣችሁ ተብለው ነው ከፓትርያርክነት መንበር የተነሡት::

11. መርሐ ሕይወት ሁለተኛ መጽሐፍ ገፅ 69-70::



## ምዕራፍ አራት
## ኢትዮጵያዊውን ሊቀ ጳጳስ በፓትርያርክነት ማዕርግ ከፍ መደረጉ

ከፓትርያርኩ ከአቡነ ዮሳብ እረፍት በኋላ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ መሠረት ከፍተኛ የኢትዮጵያ መልእክተኞች ወደ ግብፅ ተልከዋል:: እነዚህም መልዕክተኞች ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ፣ ብፁዕ አቡነ ሉቃስ፣ ልዑል ራስ አስራተ ካሳ፣ ደጃዝማች መኮንን ደስታ፣ ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ናቸው:: ይህ ለሁለተኛ ጊዜ የተካሔደው ንግግር የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መብት በማስከበር ረገድ ወሳኝ ነበር:: የኢትዮጵያ መልእክተኞች ያቀረቡት የመደራደሪያ ሀሳብ:- *"እኛ የራሳችን ፓትርያርክ እንደሆኑ ቆጥረን አብረን የመረጥናቸውን ፓትርያርክ እኛ ሳናውቀው ሕጋዊ ባልሆነ መንገድና ዘዴ በምታባርሯቸው ጊዜ የእኛን መብት ለመጠበቅ ፍላጎት እንደሌላችሁ አመልክታችኋል:: ይህም በመሆኑ እኛም የራሳችንን ፓትርያርክ መርጠን መሾም አለብን እንጂ በዚህ ሁኔታ ከእናንተ ጋር መቀጠል አንችልም"* የሚል ነበር::

ይህ የመደራደሪያ ሀሳብ ግብጾችን አስደንግጧቸው የኢትዮጵያን መልዕክተኞች እንዲህ በማለት ለማግባባት ሞከሩ:- እስከዛሬ ባለው አሠራር መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስተያን በእስክንድርያ መንበር ሥር ትቆይ እንጂ ለምን ከማርቆስ መንበር ትለያለች? ብለው ጠየቁ:: በዚህ ጉዳይ የኢትዮጵያውያን መልዕክተኞች መልስ:- *"እንግዲያውስ ይህን ካላችሁ በፓትርያርኩ መንበር ላይ የመቀመጡ መብት ዘር ለይቶ ሳይሆን በመንበሩ ሥር ለሚገኙ ወገኖች ሁሉ ለመምረጥ እድል ሊሰጣቸው ይገባል:: ኢትዮጵያም በእስክንድርያ መንበር ሥር እስከሆነች ድረስ የመምረጥ እድል ሊነፈጋት አይገባም"* የሚል ነው:: ግብፆች ይህን አማራጭ ሀሳብ በጣም ተቃወሙት:: ከብዙ ውይይትና ድርድር በኋላ ኢትዮጵያ የራስዋ ፓትርያርክ እንዲኖራት ወደ ስምምነት ተደረሰ ይላሉ በስብሰባዎቹ ሁሉ በአስተርጓሚነት የተገኙት አቶ አሥራት ገብረ ማርያም::[12]

12. ዝኒ. ከማሁ ገጽ 71-72



www.ethiopianorthodox.org

እዚህ ላይ ይህን ባትፈቅድ ኖሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምን አማራጭ ነበራት? ቢባል፡-

1. በወቅቱ ከአሥር በላይ ጳጳሳት ስለነበራት በቅናና ቤተ ክርስቲያን መሠረት ፓትርያርክ የመቀባት መብት ነበራት፤
2. ከሌሎች እህት አብያተ ክርስቲያናት (ከሶርያ፣ ከአርመን) የሚሾመውን ልጇን ልካ የፓትርያርክነት ማዕርግ መቀበል ትችል ነበር።[13]

በዚህ የፓትርያርክነት ማዕርግ ለማግኘት የመፈቀድ ጉዳይ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ናቸው። በወቅቱ ተሹመው የነበሩት የእስክንድርያ ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ 6ኛ ሲሆኑ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሰፊ ክርክርና ውይይት የታየበት ድርድር ከተካሔደ በኋላ ሰኔ 18 ቀን 1951 ዓ.ም ስምምነት ላይ የተደረሰበትን ታሪካዊ ሰነድ በፕሮቶኮል ተፈረመ። ሰነዱ በፓፓው መጽደቅ ስለነበረበት ለፓትርያርክ ቄርሎስ 6ኛ ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ የማፅደቂያው ጽሑፍ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ተላከ [ይህን ፕሮቶኮል "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመጀሪያው ፓትርያርክ" የሚለውን መጽሐፍ ከገፅ 99-105 በእንግሊዝኛ በአማርኛ ቀርቧል እርሱን ይመለከቷል] ይህን ታላቅ የምሥራች ያገኙ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ግብፅን ለመጎብኘት ፈቃደኛ በመሆን ካይሮ ሲገቡ በተለይም ለግብፅ ቤተ ክርስቲያን ልዩና ታላቅ ክብር ሆነ።

የንጉሠ ነገሥቱ ጉብኝት ክብሩ ለኮፕት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄንም ወሳኝ ምዕራፍ ላይ የሚያደርስ ታሪካዊ ጉብኝት ነበር። ጉብኝቱ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ መሠረት ያደረገ በመሆኑ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የፓትርያርክነት ደረጃ የማግኘቱ ጉዳይ በግርማዊነታቸውና በአቡነ ቄርሎስ 6ኛ በተደረገ ውይይት የመጨረሻውን እልባት እንዳስገኘ ተረጋገጠ። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያው ፓትርያርክ በዓለ ሢመት ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም እንዲሆን ስለ ተወሰነና የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ብፁዕ

13. ግብጻውያን እነዚህን ሁለት ነገሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ሳይሆን አይቀርም የፈቀዱት የሚል ግምት አለ።



ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ባስልዮስ እንዲሆኑ መፈቀዱን ሰኔ 20 ቀን 1951 ዓ.ም የተጻፈ ደብዳቤ በልዑል ድጅዝማች አስራተ ካሳ እጅ ለፓፓ ቄርሉስ 6ኛ ተሰጠ። ይህ ደብዳቤ እላይ የጠቀስነው የፕሮቶኮሉ ሥምምነት የአፀፋ (አባሪ) ደብዳቤ ነው ሙሉ ቃሉ የሚከተለው ነው።

*ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*
*ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*
*ለቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ሳድሳዊ*
*የእስክንድርያ ፓፓና የመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ*
*ካይሮ በትረካና*
*የቅዱስነትዎ ጸሎትና ረድኤት አይለየን እያልን*
*ሰላምታችንን እናቀርባለን !*

*በመንበረ ማርቆስ ስብከት ሥር ያሉትን የግብፅና የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ግንኙነት በሚገባ ስለማስተካከል ጉዳይ በቅዱስነትዎ መሪነት በመልዕክተኞቻችን መካከል ሰኔ 18 ቀን 1951 ዓ.ም ስምምነት መደረጉን በመግለፅና የተፈረመውን ፕሮቶኮል በማያያዝ ሰኔ 18 ቀን 1951 ዓ.ም የጻፉልን ደርሶናል። ለእኛና ለልጆቻችን ለሰጡን ቡራኬ ስለሕዝባችን ላቀረቡት ጸሎት ምስጋናችን እንዲደርስዎ እንወዳለን።*

*የቅዱስነትዎ ብርቱ ፈቃድና መልካም አስተያየት ያገኘው ይህ ስምምነት የቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ግንኙነት የበለጠ የሚያጠነክር ነው። ወደዚህ ለመድረስ ሁላችንም የደከምንበትና ያሰብንበት ጉዳይ ዛሬ ከፍፃሜ ደርሶ በማየታችን በጣም ደስ ይለናል።*

*አሁንም በመጀመሪያ ጊዜ የመንበረ ተክለ ሃይማኖት ወራሽ የሆኑት የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ አሁን የያዙትን መንበር እንደያዙ ሆነው "የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት እንዲሆኑ ስለፈቀድን የፓትርያርክነት ስያሜ በቅዱስነትዎ እጅ በቡራኬ እንዲቀበሉ ልከናቸዋል።*

*ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ለቅዱስነትዎ መልካም ጤንነትና የሰላም ዘመን እንዲሰጥ የቤተ ክርስቲያን ፍቅርና አንድነት እንዲያፀና እንመኛለን።*

*ሰኔ ዐሥራ ዘጠኝ ቀን ዐሥራ ዘጠኝ መቶ አምሳ አንድ ዓመት ምህረት በነገሥን በሐያ ዘጠነኛው ዓመት ተጻፈ።*

*ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ*
*ንጉሠ ነገሥት*

ከዚህ በኋላ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስም ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ሰኔ 19 ቀን ካይሮ ገቡ። ለሥርዓተ ሢመቱ በወጣው መርሐ-ግብር መሰረት ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም እሁድ እለት



www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያዊው የብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሢመት ኘትርክና ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት ተፈፀመ:: ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በፓፓው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ 6ኛ እጅ የፓትርያርክነት አክሊል ተቀዳጁ:: የመጀመሪያውም ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ለመሆን በቁ:: የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘመናት ጥረትና የቤተ ክርስቲያ ኒቱ ፍላጎት በእግዚአብሔር ፈቃድ ተፈፀመ:: "ኢትዮጵያ ከመምህራኖቿ መካከል ጳጳስ አይሹሙ" የምትለው ያቺ እፀበለስዋ የሐሰት ሥርዋፅ ፍሬ ሳይገኝባት ደርቃ ቀረች ሥርዋም ተነቀለ:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ መብትና ፍፁም ክብር እውን ሆነ:: ኢትዮጵያውያን አባቶችም ኤጲስ ቆጶሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ከዚያም አልፎ ፓትርያርኮች ለመሆን በቁ::

## የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የሕይወት ታሪክ

ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ (የበፊት ሥማቸው እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ) በ1884 ዓ.ም መጋቢት 14 ቀን ሚዳ ሚካኤል በሚባል ሥፍራ ከደብተራ ወልደ ጻድቅ ሰሎሞንና ከወለተ ማርያም ባዩ ተወለዱ:: ደብተራ ወልደ ጻድቅ ሰሎሞን አገራቸው ይፋት ውስጥ ቀወት ጌስ ማርያም ነው:: የሚኖሩት ግን ሚዳ በጎተራ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመዘምርነት አገልግሎት ነበር:: እናታቸው ወ/ሮ ወለተ ማርያም ባዩ (በኋላ እማሆይ ወለተማርያም) አገራቸው መንዝ ውስጥ ላሎ ምድር ነበር::

በተወለዱ በ14 ዓመታቸው ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ሔደው ከአለቃ ገብረኢየሱስ ቅኔ ተማሩ፤ ቀጥሎም ከአባ ገብረ ሕይወት ቅዳሴ ተምረው በዚያው በገዳሙ እየተረዱ በግ ብረ ዲቁና ያገለግሉ ነበር:: በ1905 ዓ.ም ነሐሴ 24 ቀን በደ ብረ ሊባኖስ የምንኩስና ሥርዓት ፈፀሙ:: በ1907 ዓ.ም አዲስ አበባ መጥተው ከሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ የቅስና ማዕርግ ተቀበሉ::

በ1910 ዓ.ም ግንቦት 21 ቀን የመናገሻ ማርያም ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ ሲተከልና ሲገደም ለገዳሙ የመጀመሪያ መምህር ሆነው ተሾሙ:: በዚህም ጊዜ የቁምስና ማዕርግ ተጨመረላቸው:: አባ ገብረ ጊዮርጊስ በዚህ ገዳም መጻሕፍ



ቅዳሴ እያስ ተማሩና ካህናቱን እያስተዳደሩ 14 ዓመት ከቆዩ በኋላ በ1924 ዓ.ም የካቲት 26 ቀን አዲስ አበባ የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል አለቃ ሆነው ተሾሙ:: ከአንድ ዓመት በኋላም በ1925 ዓ.ም መጋቢት 12 ቀን በኢየሩሳሌም ባሉት የኢትዮጵያ ገዳማት ላይ ራይስ ሆነው ተሾሙ::

መምህር ገብረ ጊዮርጊስ ከሁለት ዓመት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው መጥተው የካቲት 24 ቀን 1927 ዓ.ም እጨጌነት ተሾሙ:: እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ በ1928 ዓ.ም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን ተከትለው እስከ ማይጨው ዘመቱ:: ከዚያም በኋላ በስደት ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ተቀመጡ:: በ1932 ዓ.ም ሰኔ 2 ቀን ኢጣልያ ከዓለም ጦርነት ስትወገድ በዚያም ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በአሜድላ ላይ ሰንደቅ ዓላማ ሲተከል ጸሎተ ቡራኬውን ያደረሱት ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ናቸው:: ከዚያም በኋላ በዘመቻው ሁሉ ከግርማዊነታቸው ሳይ ለዩ ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ::

እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ በእጨጌነት ማዕርጋቸው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እያስተዳደሩ ከቆዩ በኋላ በ1938 ዓ.ም ሚያዝያ 19 ቀን አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የጳጳሳት ምርጫ ለጵጵስና ተመረጡ:: ከዚያም በኋላ ካይሮ ላይ ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም ባስልዮስ ተብለው በፓትርያርኩ በአቡነ ዮሳብ እጅ ጵጵስና ተቀብለው የሸዋ ጳጳስ ሆኑ:: የሸዋ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም ካይሮ ላይ በፓትርያርኩ በአቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብተው ሊቀ ጳጳሳት ዘመንግሥተ ኢትዮጵያ ሆኑ:: ከሰባት ዓመት በኋላ ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም በአቡነ ቄርሎስ 6ኛ እና አንድ መቶ አስራ ስድስተኛ የእስክንድርያ ፓትርያርክ እጅ ተቀብተው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆኑ:: በዚህ የሢመት በዓል ላይ 16 ግብፃውያን 3 ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ተገኝተዋል:: ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ከ1951 ዓ.ም1962 ዓ.ም በፓትርያርክነት ሲያገለግሉ ቆይተው በተወለዱ በ73 ዓመታቸው በ1962 ጥቅምት 2 ቀን አርፈው በደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ::

ምንጭ - ዜና ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ገፅ 226
- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ፓትርያርክ ገፅ 82
- ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን፤



www.ethiopianorthodox.org

ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ፓትርያርክ እየተመራች ጳጳሳትን ትሾማለች። በዚህ የታሪክ ዘመን ቤተ ክርስቲያናችን ይህን ታላቅ በረከትን አግኝታለች። አንድ ታላቅ አባት ስለዚህ መንበር ሲናገሩ "... ይህ መንበር ቅዱስ በመሆኑ ያለፈውን የሚናገር የወደፊቱን ትንቢት የሚገልፅ ያዘኑትን የሚያረጋጋ የተቸገሩትን የሚረዳ፣ መንፈሳውያን አገልጋዮችን የሚመግብ፣ ከፍተኛ መንበር ነው። ይህ መንበር የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን ለክብርና ለታሪክ ልዩ ልዩ ለሃይማኖት ተከታዮች ያከብሩታል ለታሪክ ልዕልና ይከበራል። ይህ መንበር በቀላል የተገኘ አይደለም በሥጋዊ አካልም ቢሆን ስለመንበሩ ሲባል በከፍተኛ ደረጃ አድክሟል። እንግዲህ ይህ መንበር ለአገራችን እንደ ታላቅ በረከት ነውና የምንመለከተው..." በማለት ገልጸዋል።[14]

በአጠቃላይ ይህን ዝርዝር ሃሳብ መገለፅ ያስፈለገበት ምክንያት በወቅቱ ምን ያህል ጥረት እንደተደረገ ለማስገንዘብ ነው። ጥረቱም በውጤት እንደተደመደመ ተገልጿል። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት አጥታው የኖረችውን መንፈሳዊ መብትና ታላቅ ክብር እንድትቀዳጅ ያደረጉት የ31 ዓመታት ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ብቻ አልነበረም። ብዙ ገንዘብ ተከፍሎበታል፣ ንብረትም ታክሎበታል፣ ስጦታው፣ ሽልማቱና ገፀ በረከቱ ቀላል አልነበረም የቀድሞዎቹ ነገሥታት አንድ ጳጳስ ከግብፅ ለማስመጣት ሲሉ የሚያፈሱት የአገር ሀብት ብዙ ነበር። አንደኛ ለግብፅ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወርቅ ይጫንላቸዋል፤ ሁለተኛ የሚመጣው ጳጳስ መንገድ እንዲያገኝ ወይም ወደ ኢትዮጵያ ተሹሞ እንዲላክና እንዲፈቀድ ግብፅን ለሚያስተዳድሩ የእስላም መሪዎች (ሡልጣኖች) ጭምር ነበር ገፀ በረከቱ የሚላከው።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ መሆን ይህን ሁሉ አስቀርቶታል። በዚህ ሢመታቸው ወቅት እዚያው ግብፅ ንጉሠ ነገሥቱ ባረፉበት ቤተ መንግሥት የሚከተለውን ታሪካዊ ንግግር አሰምተዋል:- "በግርማዊነትዎ መሪነት ሁል ጊዜ ከክብር

14. ይህን የተናገሩት የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጎርጎሪዎስ ሲሆኑ፤ የተናገሩበት ምክንያት:-ለ3ኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ለነበሩት ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት 10ኛው በዓለ ሢመት ሲከበር ያስተላለፉት መልዕክት ነው። ትንሣኤ ቁጥር 107።



ወደ ክብር በመሸጋገር ላደገችው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህ የፓትርያርክነት ማዕርግ ዛሬ ስለተፈፀመላትና ለዚህ ማዕርግ የእኔ ደካማ ሰውነት ቀዳሚነትን ለማግኘት ስለታደለ ከሁሉ አስቀድሜ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ። ወደዚህ ወደ ከፍተኛው ማዕርግ ለመድረስ ሲፈቀድልኝ ለግርማዊነትዎ ያለኝን የታማኝነት ቃል ኪዳን በፊትዎ ቆሜ ለማረጋገጥ አጋጣሚ ምክንያት አግኝቻለሁ። ግርማዊነትዎ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለማሳደግና ይህ ዛሬ የተገኘው ማዕርግ ከእነመብቱ ለኢትዮጵያ እንዲሆን ባለፉት 31 ዓመታት ውስጥ የተደረገው ድካምና ትጋት ይህን ፍሬ ለማፍራት በቅቷል። እስከ ዛሬም ድረስ ወደዚህ ግብ ለመድረስ በግርማዊነትዎ ለተደረገው ሰላማዊ ትግል መደምደሚያ ይሆናል። የአንድ ነፃ መንግሥትና ያንድ ነፃ ሕዝብ እናት መሠረታዊነቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ረገድ ራሷን ችላ የምትተዳደር እንድትሆን ግርማዊነትዎ ያደረጉት ድካም ከታሪክ በላይ ስለሆነ ዘመንዎ ዘመነ ሰላም እንዲሆንና ትውልዱ መንግሥትዎ እንዲባርክ "እግዚኦ ኩነኔከ ሀበ ለንጉሥ ወፅድቀከኒ ለወልደ ንጉሥ አግረር ፀሮ ታሕተ እገሪሁ ዕቀብ ንግሦ ወሠራዊቶ ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ" እያለች ቤተ ክርስቲያን ባለማቋረጥ ወደ እግዚአብሔር ትፀልያለች። ግርማዊነትዎ ምድረ ግብፅን በሚጎበኙበት በዚህ በአሁኑ ጊዜ አጋጣሚ ሆኖ በተገኙበት በመንበረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ሳድሳዊ የተፈፀመው ይህ የፓትርያርክነት ሥነ በዓል ለመጪው ትውልድ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ የታሪክ ምዕራፍ የያዘ ይሆናል። ይህንኑ ጉዳይ ወደ ፍፃሜ ለማድረስ በእግዚአብሔር መንፈስ ለተመሩትና እድል ላገኙት ለመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ ለቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ሳድሳዊ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ። ልዑል እግዚአብሔር ግርማዊነትዎን በሰላምና በጤና ጠብቆ ለብዙ ዘመናት ያኑር። የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ በረከትና ረድኤት በግርማዊነትዎና በግርማዊት እቴጌ ላይ በልዑል አልጋ ወራሽና በንጉሣዊ ቤተሰብ ሁሉ ላይ ይደር፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይባርክ ይቀድስ ኢትዮጵያ በነፃነት ትኑር"

ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ የሚከተለውን አሰምተዋል:- "በአፍሪቃ መካከል የክርስቲያን ደሴት ሆና የኖረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገባትን ትልቅነትና ክብር እንድታገኝ በዘመናችን ደክመንበታል። ድካማችንን ባርኮ ይህንን ፍሬ እንዲያፈራ ላደረገልንና ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ለኢትዮጵያ የተገኘበትን ይህን ቀን ለማየት ላበቃን ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋናችንን እናቀርባለን። በሐዋርያው በቅዱስ ማርቆስ ልጆች መካከል ዛሬ የተገኘው ይህ መልካም መግባባትና መከባበር ሁለቱ ቤተ ክርስቲያኖቻችን በመደጋገፍ የሚፈፅሙትን መንፈሳዊ አገልግሎት ከፍ የሚያደርገውና ለብዙ ፍሬ የሚያበቃው ነው። ከዚህም በቀር ከ330 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ዛሬ የኖረው የሁለቱ ቤተ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ግንኙነት ወደ ፊትም ጸንቶ እንዲኖር ላደረግነው ጥረት መተማመኛ የሚሆን ጽኑ መሠረት ነው። ይህ ከፍተኛ ሥራ በዘመናችን ተጀምሮ በዘመናችን እንዲፈፀም እድል ስላገኘን ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ምስጋና ከፍ ያለ



www.ethiopianorthodox.org

ነው:: ለጉዳዩ አፈፃፀም መልካም አስተያየት ለሰጡትና በብርቱ ፈቃድ ለደከሙበት አባታችን ለእስክንድርያ ፓፓና ለመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ ለቅዱስ አባ ቄርሎስ ሳድሳዊ ያለንን ታላቅ አክብሮት ስንገልፅ ደስ ይለናል:: የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ጊዜ ለሆነው ለዚህ ማዕርግ በቅተው ክብድ አደራ ያለበትን የፓትርያርክነት ተግባርዎን ሲጀምሩ ሥራዎን ለማከናወን እግዚአብሔር ይርዳዎ' በማለት አሰምተዋል:: ይህን ዝርዝር ሃሳብ ያለበትን ታሪካዊ ሥራ ትውልዱ እንዲረዳው በማለት በሠፊው እንደዘገብኩት አምናለሁ:: የዘመን ታሪካቸውን ይዘው የወጡ ታሪካዊ ጽሑፎች በምንጭነት ተጠቅሜባቸዋለሁ::

ከመጀመሪያው ከብፁዕ ወቅዱስ አባታችን አቡነ ሰላማ ከሣ ብርሃን ጀምሮ እስከ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ ከእስክንድርያ እየተቀቡ እየተላኩ የመጡ 111 ጳጳሳት ናቸው::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ሊቃውንት መሾም ከጀመረችበት ከ1921 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ባሉት 78 ዓመታት ውስጥ 120 ኢትዮጵያውያን አባቶች ተሹመዋል:: ይኸውም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ 19ኛ ግብፃዊ 5 ጳጳሳት፣ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ 2ኛ 5 ጳጳሳት፣ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ 17 ጳጳሳት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ 9 ጳጳሳት፣ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት 28 ጳጳሳት፣ በቀድሞ ፓትርያርክ በአቡነ መርቆርዮስ /በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 54 ማስታወሻውን ተመልከት/ 6 ጳጳሳት፣ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ይህ መጽሐፍ እስከተዘጋጀበት ጊዜ 49 በጠቅላላ 120 ኢትዮጵያውያን አባቶች ተሹመዋል::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በራስዋ ቅዱስ ሲኖዶስ የምትመራ ሲሆን፣ 40,559,021 በላይ ምእመንዋን፣ 424,769 [illegible] ሠራተኞችን የመምራትና ማስተዳደር የሚያስችላ [illegible] ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት በቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት፣ በጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ጽ/ቤት በሀገር ውስጥ 38 በውጭ ሀገር 10 በአጠቃላይ በ48 አኅጉረ ስብከት በ481 ወረዳዎችና [illegible].537 የአጥቢያ ሰበካ አብያተ ክርስቲያናት መዋቅርዋን [illegible]ዝርጋት አገልግሎቷን አጠናክራለች::

በውጭ ሀገር፣ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም፣ በአውሮፖ፣ አሜሪካ፣ ካሪቢያን ደሴቶች፣ አውስትራሊያ በአፍሪካ፣ በእስያ



እያከናወነች ሲሆን በዚህም ሐዋርያዊ የአገልግሎት አድማስዋን አስፍታለች::[15]

## በብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ባስልዮስ ዘመን ሹመት ያገኙ ጳጳሳት

**ነሐሴ 27 ቀን 1943 ዓ.ም፣ ግንቦት 15 ቀን 1945 ሐምሌ 15 ቀን 1945**

| የቀድሞ ስማቸው | የሢመት ስማቸው | የተሾመበት ሀገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| መምህር ሐረገ ወይን | ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ | የኢሊባቡር ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ጸባቴ ተ/ጊዮርጊስ | ብፁዕ አቡነ ገብርኤል | የወሎ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ | ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ | የኢየሩሳሌም ሀገር ስብከት ጳጳስ |
| መምህር ገብረ ጊዮርጊስ | ብፁዕ አቡነ ጎርጎሪዎስ | የከፋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| | ብፁዕ አቡነ ማርቆስ | የኤርትራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መምህር ጽጌ | ብፁዕ አቡነ ማርቆስ | የጎጃም ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መምህር ወልደ ሚካኤል | ብፁዕ አቡነ ሉቃስ | የአርሲ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ንቡረ እድ ገብረ ሚካኤል | ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ | የከፋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊቀ ሊቃውንት ገብረ መስቀል | ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ | የትግራይ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |

15. የቁጥር አሀዞች በምንጭነት የተወሰዱት ቤተ መጻሕፍት ወመዘክሩ ሲመረቅ የወጣ ልዩ እትም ላይ ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማ[illegible] ካቀረቡት ጽሑፍ ሲሆን፣ የቁጥር መረጃው እስከ 1996 ያለውን አካቷል:: ከዚህ በኋላ ላለው በአዘጋጁ የተጨመረ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

## በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በ1951 ዓ.ም የፓትርያርክነት ማዕርግ ካገኙ በኋላ የሾሟቸው ሐምሌ 17 ቀን 1952 ዓ.ም

| የቀድሞ ስማቸው | የሚመት ስማቸው | የተሾሙበት ሀገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| ሊ.ቀ ሊ.ቃውንት መሀረ ትርፌ | ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ | የጎንደር ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መ/ር ገብረ እግዚአብሔር | ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ | የባሌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መምህር ጥበቡ ደስታ | ብፁዕ አቡነ አብርሃም | የሆሣዕና ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ መዘምር | ብፁዕ አቡነ ሰላማ | የአርሲ ነጌሌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| | ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ | የኢሉባቡር ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መምህር ወልደ ሚካኤል | ብፁዕ አቡነ ሚካኤል | የቦረና ነገሌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መምህር ገብረማርያም | ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ | የአሰላ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ኤዎስጣጢዎስ /ሚያዝያ 15 1953 የተሾሙ/ | ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ | የኤርትራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ኃይለኢየሱስ እጅጉ | ብፁዕ አቡነ ሉቃስ | የደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |

## በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዘመን
## የካቲት 5 ቀን 1964 ዓ.ም፤ መስከረም 17 ቀን 1968 ዓ.ም. ሹመት ያገኙ ጳጳሳት

| የቀድሞ ስማቸው | የሚመት ስማቸው | የተሾሙበት ሀገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| መምህር ተጸላ ሰፋፋ | ብፁዕ አቡነ እንድርያስ | የጎንደር ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መምህር ተስፋ ወልደ ሥላሴ | ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ | የከፋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊ.ሊ.ቃ.ኃ/መ/ገ/መስቀል | ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ | የኢየሩሳሌም ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ንቡረ እድ አበበ ሻውል | ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ | የቦረና ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ገብረ እግዚአብሔር ደገ | ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል | የዝዋይ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ገብረ ኢየሱስ መሸሻ | ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ | የትሪንዳድና ቶቤጎ ሀገረ ስብከትን |
| አባ ገብረ መድህን ገ/ዮሐንስ /5ኛው የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ፓትርያርክ/ | ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ | የውጭ ሀገር አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነትና የመነባራዊ ኑሮ አገልግሎት ኃላፊ ጳጳሳ:: |
| ሊቀ ሊቃውንት ክፍለ ዮሐንስ ኃ/ሚካኤል | ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ | ጳጳስ |
| ጸባቴ በጽሐ ጌታሁን | ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ | ጳጳስ |



## በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመን ሹመት ያገኙ
## ጥር 13 ቀን 1971 ዓ.ም

| የቀድሞ ስማቸው | የሚመት ስማቸው | የተሾሙበት ሀገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| አባ መዝገቡ ክፍሌ | ብፁዕ አቡነ ጎርጎሪዎስ 2ኛ | የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ዜና ገብርኤል | ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ | የወለጋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ላዕከ ማርያም ማንደፍሮ | ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ | የአሜሪካ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊቀ/ሥ/መአዛ ቅ/ገ/ሕይወት | ብፁዕ አቡነ ናትናኤል | የትግራይ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ፍስሐ | ብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ | የሲዳሞ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ሐዋዝ | ብፁዕ አቡነ ሰላማ | የባሌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊቀ ጉባኤ ገብረ ሚካኤል | ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል | የወሎ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ስብሐት ለአብ በየነ | ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ | የጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መልአከ ምህረት ያሬድ ግርማይ | ብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ | የኤርትራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ፀጋዬ ቢሆነኝ | ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ | የኢሉባቡር ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ተክለ ማርያም አስራት | ብፁዕ አቡነ ማትያስ | በኢየሩሳሌም ጳጳስ |
| አባ ኀሩይ ፈንቴ | ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ | የከፋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ዘሊባኖስ ፈንታ 4ኛው የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ፓትርያርክ የነበሩ | ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ | የአጋዴን ሀገረ ስብከት ጳጳስ |



www.ethiopianorthodox.org

## ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት

ጥር 14 ቀን 1972 ዓ.ም፤ ሐምሌ 12 ቀን 1973 ዓ.ም፤ ሐምሌ 17 ቀን 1975 ዓ.ም.፤ ህዳር 9 ቀን 1977 ዓ.ም.፤ ግንቦት 30 ቀን 1979 ዓ.ም.፤ ግንቦት 7 ቀን 1980 ዓ.ም የሾሟቸው

| የቀድሞ ስማቸው | የሢመት ስማቸው | የተሾሙበት ሀገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| ዶክተር አባ ኢያሱ ገብሬ | ብፁዕ አቡነ ገብርኤል | የኤርትራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ዶክተር ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ሥላሴ ተስፋ | ብፁዕ አቡነ ጢሞቴወስ | የከፋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ዶክተር ግርማ ወልደቂርቆስ | ብፁዕ አቡነ ገሪማ | የሱዳን የኢ/ቤ/ክ ጳጳስ |
| ሊቀ ሊቃውንት ኤፍሬም | ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም | የአርሲ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ገብረ እግዚአብሔር ፀጋዬ | ብፁዕ አቡነ ኤልያስ | በጅቡቲ የኢ/ቤ/ክ ጳጳስ |
| አባ ብርሃኑ ካሳ | ብፁዕ አቡነ በርናባስ | የአሰብ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ዮሐንስ ከኃሊ | ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ | የኢየሩሳሌም የኢ/ቤ/ክ ጳጳስ |
| አባ ተክለ ማርያም | ብፁዕ አቡነ ማትያስ | የወሎ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መምህር ዋካ | ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ | የገዳማት ጳጳስ |
| መምህር ወልደ ትንሣኤ ግዛው | ብፁዕ አቡነ ዲዮስ ቆሮስ | የምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊቀ ሥልጣናት ኤልያስ አበበ | ብፁዕ አቡነ ኒቆዲሞስ | የምስራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊ/ኅ/መርጎ ጽድቅ ገ/ሕይወት | ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ | የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መልአከ አሚነ ዘካርያስ ኃ/ማርያም | ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ | የወላይታ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መልአከ ሣህል መዘመር ተገኝ | ብፁዕ አቡነ ቶማስ | የድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ተክለ ማርያም አምደ ብርሃን | ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ | የገዳማት ጳጳስ |



## በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ዘመን ሹመት የገኙ ጳጳሳት

ጥቅምት 18 ቀን 1983 ዓ.ም

| የቀድሞ ስማቸው | የሢመት ስማቸው | የተሾሙበት ሀገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| አባ ተወልደ ብርሃን | ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ | የገዳማት ጳጳስ |
| ሊቀ/ሥ/ሀ/ ማርያም ወርቅነህ | ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ | የቅ/ጳ/ከ/መ/ት/ቤት ዲን |
| መ/ሰ/ኃ/ማርያም ደምሴ | ብፁዕ አቡነ ተክለሃይማኖት | የምዕራብ ሸዋ ገረ ስብከት ጳጳስ |
| መጋቢ/ ኃ/ኢየሱስ ከበደ | ብፁዕ አቡነ ጎርጎሪዎስ | |
| ሊቀ ሥልጣናት ገ/ማርያም ገ/ሥላሴ | ብፁዕ አቡነ አረጋዊ | በሱዳን የኢ/ቤ/ክ ጳጳስ |
| መምህር ኀሩይ መንግስቱ | ብፁዕ አቡነ በርናባስ | የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |

## በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመን የተሾሙ ጳጳሳት

ከጥር 30 ቀን 1985፤ ህዳር 4 ቀን 1987 ዓ.ም.

| የቀድሞ ስማቸው | የሢመት ስማቸው | የተሾሙበት ሀገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| መጋቢ ገ/ማርያም ኃ/ማርያም | ብፁዕ አቡነ አብሳዲ | በኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳሳት ረዳት ኤጲስ ቆጶስ |
| አባ ላዕከ ማርያም አስራት | ብፁዕ አቡነ ሆርያቆስ | የአፍሪካ ክፍለ ዓለም ኤጲስ ቆጶስ |
| አባ አረጋዊ ወልደ ገብርኤል | ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ | የመላው አውሮፓ ኤጲስ ቆጶስ |
| አባ ወልደገብርኤል ወ/ሥላሴ | ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ | የካሪቢያን ደሴቶች የላቲን አሜሪካ |
| መጋቤ ካህናት አባ አማን ዘውዴ | ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ | የጋንቤላ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መልአከ ሰላም አባ ብርሃነ ሥላሴ ተ/ኃይማኖት | ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ | የድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊቀ ሥልጣናት አባ ገ/ማርያም ፈለቀ | ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ | የኢሉባቡር ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መምህር ኪዳነ ማርያም አለባቸው | ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ | የደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊቀ ጉባኤ አሰበ ዮሐንስ ቤተ | ብፁዕ አቡነ ኤልያስ | የምዕራብ ሀረርጌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ተጠምቀ ተ/ሃይማኖት | ብፁዕ አቡነጎርጎሪዎስ | የምስራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ኃይለ ኢየሱስ ክንፈ ሚካኤል | ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዲቅ | የከንባታ ሀድያና ጉራጌ ዞን አህጉረ ስብከት ጳጳስ |



www.ethiopianorthodox.org

## በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ
## ሐምሌ 5 ቀን 1991 ዓ.ም የተሾሙ

| የቀድሞ ስማቸው | የሚመት ስማቸው | የተሾሙበት ሀገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| ቆሞስ አባ ገብረ ወልድ ሀ/ማርያም | ብፁዕ አቡነ ኤርሚያስ | በአ.አ. የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳት ቤተ ክርስተየን ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ገ/ሥላሴ ኃ/ማርያም | ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ | የድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ገ/ሥላሴ በዛ | ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ | በአፍሪካ የኢ.ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ሠረቀ ብርሃን ጽጌ | ብፁዕ አቡነ ዮናስ | የአፋር ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ አምሐ ሥላሴ አሳየኸኝ | ብፁዕ አቡነ ኤጲፋንዮስ | የከፍቾ ሸኮች የቤንች ማጂ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ቶማስ በቀለ | ብፁዕ አቡነ ኤልያስ | የወለጋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ገብረ ማርያም ልመንህ | ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ | የጋምቤላ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ኃ/ኢየሱስ ተስፋ | ብፁዕ አቡነ ኢሳይያስ | የሰሜን ምዕራብ አውሮፓ ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ጎሐ ጽባሕ ጥሩነህ | ብፁዕ አቡነ እንድርያስ | የሰሜን ጎንደር ሀገረስብከት ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ገ/ሚካኤል በየነ | ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ | የኦጋዴን ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ሙሴ ወርቅነህ | ብፁዕ አቡነ ሙሴ | በአረብ ኢምሬቶች ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ፍስሐ ወ/ፃድቅ | ብፁዕ አቡነ ስምኦን | የአሶሳ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ተክለድንግል ደሴ | ብፁዕ አቡነ ድሜጥሮስ | የነገሌ ቦረና ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ገ/ዮሐንስ ተጠ ምቀ | ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ | የደቡብ ምዕራብ አውሮፓ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ኃይለ ጊዮርጊስ ኃ/ሚካኤል | ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ | የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ኃ/ኢየሱስ | ብፁዕ አቡነ ሉቃስ | የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |



## በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ
## ነሐሴ 22 ቀን 1997 ዓ.ም. የተሾሙ

| የቀድሞ ስማቸው | የሚመት ስማቸው | የተሾሙበት ሀገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| መ/ር ተክስተብርሃን ወ/ሳሙኤል | ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል | የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መ/ር ሀብተማርያም መኮንን | ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል | የሚዛን ተፈሪ ጳጳስ |
| አባ ብርሃነ ሥላሴ | ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ | የትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን ሀገረ ስብከት ማይጨው ጳጳስ |
| መ/ር ኃይለ ሥላሴ ይግዛው | አቡነ ሉቃስ | የሴቲት ሁመራ ጳጳስ |
| አባ ቃለጽድቅ እውነቴ | ብፁዕ አቡነ አብርሃም | የስብከተ ወንጌል የሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የበላይ ኃላፊ ጳጳስ |
| አባ ፍቅረማርያም ታደሰ | ብፁዕ አቡነ ዳንኤል | ዩአሶሳ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊቀ ጉባኤ አባ አካለወልድ ወ/ሰማያት | ብፁዕ አቡነ ያሬድ | የምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊቀ ሥልጣናት ተክለሚካኤል ዓባይ | ብፁዕ አቡነ ሚካኤል | የትግራይ ክልል የሰሜናዊ ምዕራብ ዞን ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መልአከ ምሕረት አባ ገብረኢየሱስ ቡልቶሳ | ብፁዕ አቡነ ሔኖክ | የምዕራብ ወለጋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ጸባቴ ተክለሐዋርያት ባሳዝነው | ብፁዕ አቡነ ዕንባቆም | የደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ጳጳስ /ጂንካ/ |
| ጸባቴ ክፍለዮሐንስ ተክለሃይማኖት | ብፁዕ አቡነ ቀሌምንጦስ | የምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ሊቀሥልጣናት ሐረገወይን ገ/ሥላሴ | ብፁዕ አቡነ ሰላማ | የርእሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን ጳጳስ |
| አባ ገብረ እግዚአብሔር ኃይሉ | ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ | የመቀሌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| መልአከ ኃይል አባ አፈወርቅ ጌታነህ | ብፁዕ አቡነ ኦግቴዎስ | የዋግህምራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| ቆቡረዕድ ገ/ዋሕድ ግርማይ | ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ | የአዲግራት ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ አካለወልድ ሞገስ | ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ | የነገሌ ቦረና ሀገረ ስብከት ጳጳስ |
| አባ ወ/ጊዮርጊስ ገብረክርስቶስ | ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ | የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ |



www.ethiopianorthodox.org

## በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎብ
## ሐምሌ 9 ቀን 1998 ዓ.ም. የተሾሙ

| የቀድሞ ስማቸው | የሚመት ስማቸው | የተሾሙበት ሀገረ ስብከታቸው |
|---|---|---|
| መልአከ ስብሐት ቆሞስ አባ ማርቆስ ተረፈ | ብፁዕ አቡነ ማርቆስ | በሰሜን አሜሪካ የካሊፎርኒያ ግዛት ጳጳስ |
| መልአከ ሰላም ቆሞስ አባ መልአኩ ጌታነህ | ብፁዕ አቡነ ፋኑኤል | በሰሜን አሜሪካ የዋሽንግተን ዲሲና ሜሪላንድ ጳጳስ |
| መልአከ ፀሐይ አባ ገብረትንሣኤ ኃይሉ | ብፁዕ አቡነ እንጦንስ | የምዕራብ አውሮፓ ጳጳስ |
| መልአከ ሰላም ቆሞስ አባ ገብረሚካኤል | ብፁዕ አቡነ ድሜጥሮስ | በሊባኖስ በተባበሩት የዐረብ ኤምሬቶች ጳጳስ |
| ቆሞስ አባ ገብርኤል | ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ | የደቡብና የምዕራብ አፍሪካ ጳጳስ |

**ማሳሰቢያ**: በፓትርያርኮቹ የተሾሙ ብፁአን አበው የስም ተፋልሶ ቢኖር፤ ወይም በአንዱ ፓትርያርክ የሾመውን ለሌላው ደርቤው ከሆነ አስተካክላችሁ አርሙት ለዚህም አስቀድሜ አመሰግናለሁ::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጥር 26 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው መግለጫ የቀድሞው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን 4ኛወ ፓትርያርክ አባ መርቆርዮስን ጨምሮ አባ ዜና ማርቆስ፤ አባ ኤልያስ፤ አባ ጎርጎርዮስ እና አባ መለከጼዴቅ በተባሉት ላይ ውግዘት ያስተላለፈ ሲሆን ሥልጣነ ክህነታቸው ተሽሮ በቀድሞ ስማቸው እንዲጠሩ መወሰኑን የገለጸ መሆኑን ልብ ይሏል::



# ምዕራፍ አምስት
## በአገር ውስጥ በመሾም የመጀመሪያው ቅዱስ ፓትርያርክ

ቤተ ክርስቲያናችን ካስገኘቻቸው ታላላቅ አባቶች መካከል በክፍለ ዘመናችን ከነበሩት አባቶች አንዱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ 2ኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ናቸው:: ቅዱስነታቸው ሚያዝያ 16 ቀን 1902 ዓ.ም በጎጃም ክፍለ አገር በደብረ ማርቆስ አውራጃ በማቻከል ወረዳ ደብረ ገነት ኤልያስ በሚባል ታላቅ ደብር ከአቶ ጀንበሬ ውቤና ከወ/ሮ ዘርትሁን አዳላሁ ተወለዱ አባታቸው ከጊዜ በኋላ መንነው ገዳም በመግባት መንኩሰው አባ ወልደ ማርያም ተብለዋል::

የቅዱስነታቸው አእምሮ ትምህርት ለመቀበል እንደ ደረሰ በተወለዱበት በደብረ ኤልያስ የዜማና የንባብ ትምህርት ተማሩ:: በዚሁ ደብር የቅኔና የመጽሐፍ ትርጓሜ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት ሊቅ ከመምህር ገብረ ሥላሴ ቅኔ ከእነ አገባቡ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ:: ቀጥሎም በ1920 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ከተማ መጥተው ከመምህር ሐዲስ ተክሌ (በኋላ ንቡረ እድ ተክለ ሃይማኖት) በመጨረሻም ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ይባሉ ከነበሩት ኢትዮጵያዊ ሊቅ የመጻሕፍት ሐዲስትንና የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ ጠንቅቀው አወቁ::

ከዚያም ለዚህ ከፍተኛ ክብር እንዲበቁ ቅዱስነታቸውን የእግዚአብሔር መንፈስ መርቷቸው መንፈሳዊ ሕይወት በመምረጥ በ1930 ዓ.ም ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄደው ማዕርገ ምንኩስናን ተቀብለዋል:: በዘመናዊ ትምህርት ረገድ በ1934 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሊቃውንት የአገራቸውን ቋንቋ ብቻ ሳይሆን የውጭ ቋንቋም ተምረው የዘመኑ ሥልጣኔ ተካፋዮች እንዲሆኑ በቅዱስነታቸው አቅራቢነት ሃያ ሊቃውንት ተመርጠው በቤተ መንግሥት ውስጥ ይሰጥ የነበረውን የውጭ ቋንቋ አጥንተዋል::

በ1935 ዓ.ም በንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድና ትዕዛዝ በመካነ ሥላሴ ገዳም (ዛሬ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል) መምህር ተብለው በአስተዳዳሪነት ተሾሙ:: በ1938 ዓ.ም የመካነ ሥላሴ ገዳም መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ



www.ethiopianorthodox.org

ተብሎ በንጉሠ ነገሥቱ ሲሰየም አስተዳዳሪውም ሊቀ ሥልጣናት እንዲባል ስለተፈቀደ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከንጉሠ ነገሥቱ ከራስ ወርቅና ከላንቃ ካባ ጋር ሙሉ ሽልማት ተሸል መው የመጀ መሪያው የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ገዳም ሊቀ ሥልጣናት ሆኑ:: ከዚህ በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት በንጉሠ ነገሥቱ ጥረት ኢትዮጵያውያን አበው ጵጵስና እንዲ ሾሙ በእስክንድርያና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስምምነት ሲደረግ ሚያዝያ 19 ቀን 1938 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የጳጳሳት ምርጫ ሊቀ ሥልጣናት መልዕክቱ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከ5ቱ ኢትዮጵያውያን ተመራጮች አንዱ ሆነው ከፍተኛ ድምፅ ስለተመረጡ ለሹመት ወደ ግብፅ ሔዱ:: ይሁንና ሹመቱ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ለሁ ለት ዓመታት ቢዘገይም ከሁለት ዓመታት በኋላ ጉዳዩ እልባት ስለአገኘ አምስቱ ተመራጮች ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም እን ደገና ወደ እስክንድርያ ሔደው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በነበሩ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ እጅ ከሌሎች አራት ኢትዮጵያውያን ጋር አቡነ ቴዎፍሎስ ጳጳስ ዘሐረርጌ ተብለው ተሾሙ::

በ1942 ዓ.ም የካቲት 11 ቀን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ ያን ቅዱስ ሲኖዶስና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፈቃድ እንደራሴ ሆኑ:: በኢትዮጵያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መካከል በነበረው ስምምነት መሠረት ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በያዙት የሐረርጌ ጳጳስነትና እንደራሴነት ላይ በኢትዮጵያ የብ ፁዕ አቡነ ዮሳብ ወኪልነት ተሰጣቸው:: ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ከፍተኛውን የፓትርያርክነት መብት ካገኙ በኋላ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የሐ ረርጌ ሊቀ ጳጳስ ተባሉ:: በዚህ ረገድ በመካነ ሥላሴ ገዳም መም ህር ተብለው በአስተዳዳሪነት 3 ዓመት፣ በሊቀ ሥልጣንነት 2 ዓመት፣ በጳጳስነት 12 ዓመት በሊቀ ጳጳስነት 11 ዓመት በአጠቃላይ 28 ዓመታት ለኢትዮ ጵያ መንፈሳዊ አገልግሎት አበርክተዋል:: ከዚሁ ውስጥ ሃያው ዘመን በእንደራሴነት የሠሩበት ሲሆን፣ በዚህ ረጅም የሆነ የመ ንፈሳዊ ሥልጣን ዘመናቸው ወደ ፊት እንደምናየው ከፍተኛና ፍሬያማ የሆነ የተቀደሰ አገልግሎት ለቅድስት ቤተክርስቲያን ካበረከቱ በኋላ በተወለዱ በ61 ዓመታቸው መጋቢት 29 ቀን



1963 ዓ.ም በተደረው የሁለተኛው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ምርጫ አንደኛ በመውጣት ሁለተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሆነው ተመርጠዋል:: ይልቁ ንም የቅዱስነታቸው ሁለተኛ ፓትርያርክነት ልዩ የሚያደርገው "በሀገር ውስጥ በመሾም የመጀመሪያው ቅዱስ አባት" መሆና ቸው ነው::

## ቅዱስነታቸው ለፓትርያርክነት ማዕርግ መመረጥ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በሞት በተለዩ ጊዜ ከቅዱስ ሲኖዶስ በመላ ኢትዮጵያ አርባ ቀን መዋዕለ ኀዘን እንዲሆን በተወሰነው መሠረት አርባ መዋዕለ ኀዘን በጸሎተ ፍትሐት እንደተፈፀመ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በብ ፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ እንደራሴ ሊቀ መንበርነት የኢትዮጵያ ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ አድርጓል:: ይኸውም ቅዱስ ሲኖዶስ በሞተ የተለዩትን ፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ የፓትርያርክነቱን ማዕርግ በተቀበሉ ጊዜ በኢትዮጵያ መልዕክተኞተና በግብፅ አባ ሎች መካከል የተጻፈ ከዛሬ በኋላ ሌላ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በሚሾምበት ጊዜ በእስክ ንድርያው ፓትርያርክ እጅ ይሾማል የሚል የውል አይነት ደብተር ለኢትዮጵያ ሲኖዶስ ቀርቦ በንባብ ከተሰማ በኋላ ቅዱስ ሲኖዶስ በሐሳቡ ቃል በቃል ተነጋገረበት::

ጽሑፉ የኢትዮጵያን ክብር የሚነካ በመሆኑ ዛሬ የሰው ዘር ሁሉ ለሥጋዊ ነፃነቱ እንኳ በሚጋደልበት ጊዜ ኢትዮጵያ ይህን የመንፈስ ነፃነት የሚያሳጣውን ደብተር ሕግ አድርጋ መቀበል የለባትም በማለት ቅዱስ ሲኖዶስ በአንድ ድምፅ ተስ ማምቶ ለንጉሠ ነገሥቱ:- ይህን ከሐዋርያት ቀኖና ሕግ የሌለው በሰው ልማድ የቆየውን ባሕል ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራስ ላይ ወርዶ ኢትዮጵያ እንደሌሎች እህት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ራሷ መርጣ ራሷ መሪዋን እንድትሾም ይፈቀድልን ዘንድ እናመልከት ሲል ወስኗል:: በዚህ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሰ ረት ለንጉሠ ነገሥቱ የተጻፈ ማመልከቻ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ከሙሉ ሲኖዶስ አባሎች ተፈርሞ መጋቢት 17 ቀን 1963 ዓ.ም



www.ethiopianorthodox.org

ተጽፎ ለዐፄ ኃይለ ሥላሴ ቀርቧል:: ይኸውም የኢትዮጵያ ቅዱስ ሲኖዶስ ማመልከቻ በንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ተቀባይነት አግኝቶ ቅዱስ ሲኖዶስ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና አጥንቶ ባቀረበው ደንብ መሰረት መፈቀዱን በሚከተለው ከጽሕፈት ሚኒስቴር በተጻፈው ደብዳቤ ታውቋል::

ሢመተ ፓትርያርክ የምሥራች
የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የክብር አክሊል
የተቀዳጀችበት አብሳሪ ቃለ ንጉሠ ነገሥት

ቁጥር 1ሺ 836/63 ፈ5/1ሺ 809
መጋቢት 21 ቀን 1963 ዓ.ም

ለብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ
የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እንደራሴና
የሐረር ጠ/ግዛት ሊቀ ጳጳስ
አዲስ አበባ
ብፁዕ ሆይ!

ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ምርጫ አፈጻጸም ደንብ ማውጣት የኢትዮጵያ ቅዱስ ሲኖዶስ በቤተ ክርስቲያን ሕግ ቀኖና መሰረት አጥንቶ መጋቢት 16 ቀን 1963 ዓ.ም ሊቃነ ጳጳሳቶቹ ተስማምተው የፈረሙበት ለግርማዊነታቸው ቀርቦ ከታየ በኋላ በዚሁ በቀረበው ደንብ መሰረት እንዲፈፀም መፈቀዱን በማክበር አስታውቃለሁ::

ለብፁዕነትዎ ከተገባ ሰላምታ ጋር
ፊርማ ሰሎሞን ገብረ ማርያም
ምክትል ሚኒስትር
ማኅተም የጽሕፈት ሚኒስቴር

በዚህ መሠረት በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ካገኘ በኋላ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው የሆነውን በምድሯ ላይ በራሷ ልጆች ፓትርያርክ ለመቀባት የሚያስችል ደንብ አውጥታ አዘጋጀች:: [የደንቡን ዝርዝር ኢየሩሳሌምን እወቁ በአባ ፊሊጶስ የተዘጋጀ ገፅ 41-44 ይመለከቷል]

በዚህ ደንብ መሠረት መጋቢት 29 ቀን 1963 ዓ.ም በመንበረ ፓትርያርኩ በተፈጸመው የምርጫ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ለፓትርያርክነት ምርጫ እጩዎች ሆነው የቀረቡት 3 ሊቃነ ጳጳሳት ነበሩ:: እነሱም 1.በወቅቱ የኢትዮጵያ መንበረ



ፓትርያርክ እንደራሴና የሐረርጌ አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ቅዱስነታቸው፣ 2.ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የወለጋ አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ 3.ብፁዕ አቡነ ጢሞቴ ዎስ የሲዳሞ አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ናቸው::

የእነዚህ ሦስት አባቶች ስም ዝርዝር ከመጋቢት 26 ቀን እስከ መጋቢት 29 ቀን ድረስ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን መንበር ላይ ተቀምጦ ጸሎተ ቅዳሴ ሲደረግበት ሰንብቶ በኋላ መጋቢት 29 ቀን በመንበረ ፓትርያርኩ በተደረገው ምርጫ ቅዱስነታቸው ከፍተኛውን ድምፅ ማለትም ከተሰጠው ድምፅ 80 በመቶ አግኝተው ሊመረጡ ችለዋል:: ይህ ምርጫ ለንጉሠ ነገሥቱ ቀርቦ ከጸደቀ በኋላ ለሕዝብ ይፋ ሆኗል::

## የቅዱስነታቸው በዓለ ሢመት አከባበር

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በዓለ ሢመት ግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ.ም በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መኳንንቱና መሳፍንቱ ከልዩ ልዩ አገሮች የመጡ የሃይማኖት መሪዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ካህናትና ምዕመናን በተገኙበት ታሪካዊና ደማቅ በሆነ ሥነ ሥርዓት ተከብሮ እንደዋለ ታሪክ ያስረዳናል:: ኢትዮጵያ በ1ሺህ 600 ዓምት የክርስትና ታሪኳ ውስጥ ከራሷ ተወላጅ ፓትርያርክ መርጣ በራሷ ምድርና በራሷ ሊቃነ ጳጳሳት ስትሾም የመጀመሪያ ጊዜ እንደመሆኑ መጠን ለበዓለ ሢመቱ የተዘጋጀው ኘሮግራም የቤተ ክርስቲያንን ባሕል ጠንቅቆ የያዘና እጅግ ሰፊ ነበር::

ስለ በዓሉ አከባበር የቅዱስነታቸውን የሕይወት ታሪክ ይዘው የወጡ ዘገባዎች በሰፊው ገልፀውታል:: ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከመንበረ ፓትርያርክ ተነሥተው የማዕርግ ልብስ በለበሱ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መብራት በያዙ ልዑካን "ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር" የሚለውን መዝሙር በሚያዜሙ መዘምራን ታጅበው ከጠዋቱ 2 ሰዓት ከአሥር ደቂቃ ላይ ከቤተክርስቲያኑ ዐውደ ምህረት ሲደርሱ ከአድባራቱ የተመረጡ ቀሳውስትና ዲያቆናት ልብሰ



www.ethiopianorthodox.org

ተክህኖ ለብሰው ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር መግቢያ አንስቶ እስከ ዐውደ ምህረቱ ድረስ ግራና ቀኝ ተሰልፈው ተቀበሏቸው:: በዚህም ወቅት የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የደወል ድምፅ አሰምተዋል::

ፓትርያርኩ ወደ ቅድስቱ ዘልቀው እንደቆሙ ጸሎተ ቅዳሴው ተጀምሮ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ በበዓሉ መካከል ለበዓለ ሢመቱ የተዘጋጀው ልዩ ልዩ ጸሎት ቀጠለ:: በዚህም ጊዜ እህትማማች ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የመጡ ፓትርያርኮችና ሊቃነ ጳጳሳት በየተራ እየቀረቡ የጸሎቱ ተካፋዮች ሆነው ነበር:: ቀጥሎም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተስማሚውን ጸሎት አደረሱ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የፓትርያርክ የማዕርግ ልብስ አልብ ሰው አክሊለ ክብሩን አቀዳጅተው አርዌ ብርቱን አስጨበጧቸው:: ይህም በተደረገበት ወቅት በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የነበሩት መዘምራንና ምዕመናን "አክዮስ" ይደልዎ! የሚለውን የማረጋገጫ ቃል ሦስት ሦስት ጊዜ በማሰማት ደስታቸውን ገለፁ:: ከዚህ በማ ያያዝም ንጉሠ ነገሥቱ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያ ርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ታላቁን የሰሎሞንን ኮርደን ኒሻን አጠለቁላቸው::

[ከጥሩ ወርቅ የተሰራና በአልማዝ ያጌጠ ሰንሰለት ሆኖ በአን ገት የሚጠለቅና በደረት የሚደረግ ኘላክ አለው:: በሰንሰለቱ ዙሪያ "አምላክነስ ኃይልነ ወጸወንነ" የሚል ጽሕፈት አለበት:: መልኩ በቀኝ ንግሥተ ሣባ ወደ ሰሎሞን እንደ ቀረበች በግራ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር እንደ ዘረጋች ሆኖ ተስሎበታል ከፍ ብሎ ሁለት አንበሶች የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ እንደ ያዙ ሆነው የወርቁን ሰንሰለት አያይዘው ይታያሉ:: ይህ የወርቅ ሰንሰለት ያለው የሰሎሞን ኒሻን የወጣው ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ በጫኑበት በ1923 ዓ.ም ነው:: ይህ ባለወርቅ ሰንሰለት ኒሻን ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና ንጉሠ ነገሥቱ ከሚሸልማቸው ከውጭ አገር ታላላቅ ነገሥታት በቀር ለሌላ ሰው አይሰጥም:: በተለይ ለኢትዮጵያ በሰላምም በጦርም አገልግሎት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ያደረጉ ንጉሠ ነገሥቱ ከሚ ሰጡት በቀር አይሸለምም::] (ዝክረ ነገር ገፅ 670)

ቅዱስነታቸውም ቃለ ሃይማኖት አሰሙ:: ለበዓለ ሢመቱ ክብር ሲባል 17 ጊዜ መድፍ ተተኩሶ ነበር:: ከጸሎተ ወንጌል ቀጥሎ ያለው የጸሎተ ቅዳሴው ሥነ ሥርአት የተካሔደው በአዲሱ ፓትርያርክ እየተመራ ሲሆን፣ ጸሎተ ቅዳሴው ካበቃ



በኋላ ፓትርያርኩ በበዓለ ሢመቱ ሥነ ሥርዓት ላይ ተካፋይ የሆኑትን የውጭ አገር መንግስታት እንደራሴዎች የእጅ ሰላምታ በመስጠት አሰናበቱ ከዚያም ንጉሠ ነገሥቱና ፓትርያርኩ ታጅበው ወደ ዐውደ ምህረቱ ሲወጡ መዘምራን በመደመቀ ሽብሸባ ተቀበሏቸው:: ይህም እንዳበቃ የበዓሉ ተካፋይ የሆኑ የውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ተወካዮች በየተራ እየተነሱ ለብ ፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ሆኖ መመረጥና መሾም የተሰማቸውን ልባዊ ደስታ በመግለፅ ንግግር አድርገዋል:: ቀጥሎም ቅዱስነታቸውና ንጉሠ ነገሥቱ ሰፋ ያለ ንግግር ካደረጉ በኋላ ጠቅላላ ኘሮግራሙ 7 ሰዓት ሲሆን ተፈፅሞ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ቡራኬ ከሰጡ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ቤተ መንግ ስታቸው ሲመለሱ፣ ቅዱስነታቸው ግን በሞተር ብስክሌት ታጅበው ወደ መንበረ ፓትርያርክ ሄዱ:: ግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ.ም የፓት ርያርኩ በዓለ ሢመት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በተከበረበት ጊዜ የተሰበሰበው ሕዝብ ብዛት በብዙ ሺ የሚቆጠር ሲሆን የቀረውም ሕዝብ የበዓሉን ሥነ ሥርዓትና አፈጻጸም ሁኔታ በቀጥታ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ስለተላለፈለት መከታተል ችሏል::

## ቅዱስነታቸው ከፈጸሙአቸው ታላላቅ ሥራዎች ጥቂቶቹ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለዑል እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ አባትነት ስለመረጣቸው ሕይወታቸውን ለፈጣሪያቸው መሥዋዕት አድርገው እከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ለክርስቶስ ፍቅርና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እድገት የፈፀሙአቸው ዐበይት ተግባራት ብዙዎች ሲሆኑ ለዝክረ ነገር ያህል ጥቂቶቹን እናቀርባለን:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ተስፋ ጥሎበት የነበረው የመንፈሳዊ ኮሌጅ ከተቋቋመ በኋላ ቅዱስነታቸው ትምህርት ቤቱን በመምራትና በማስተዳደር ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የዘመናዊ እውቀት በር ከፋች የሆኑ መሁራንን እንዲያፈራ አድርገዋል:: አያሌ መንፈሳዊ ወጣቶችንም ወደ ውጭ አገር ለመንፈሳዊ ትምህርት በመላክ ለቤተ ክርስቲያኗ ሆነ ለአገር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ ምሁራንን ተመራማሪዎችን አስገኝተዋል::



www.ethiopianorthodox.org

በሊቀ ሥልጣንነታቸውም ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሥራዎች ሰርተዋል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያውያን አበው መርጣ ጳጳሳት ለመሾም እንድትችል ለረጅም ጊዜ በተደረገው ጥረት ቅዱስነታቸው ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። ከኢትዮጵያ እስክንድርያ በየጊዜው በተደረገው ጉዞ ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያን መልዕክተኞች በመምራትና በውይይቱም ጉልህ ተሳትፎ በማድረግ ጥረቱ ፍሬያማ እንዲሆን ካደረጉት መልእክተኞች መካከል የመጀመሪያውን ቦታ ይዘዋል። ቅዱስነታቸው በፈጸሙት ሐዋርያዊ ተልእኮ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች አስተምረው ለክርስትና አብቅተዋል። ለምሳሌ ያህል በ1949 ዓ.ም በባሌ ጥቅላይ ግዛት ባደረጉት አድካሚ ጉዞ በገደብ አውራጃ፤ በዶዶላ፣ በሲሮፍታ፣ በሄቤና፣ በኮኮሳና በጋጣ እየተዘዋወሩ የወንጌልን ትምህርት በማስተማር 24 ሺህ የአዋማና ልዩ ልዩ እምነት ተከታዮችን በማሳመንና በማጥመቅ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ አድርገዋቸዋል። የቅዱስነታቸው ሐዋርያዊ ሥራ በሁለት ክፍለን መመልከቱ ይጠቅማል።

## 1. በሀገር ውስጥ ያከናወኗቸው

### 1.1 ሰበካ ጉባኤ

"ቃለ አዋዲ ዘይሰብክ በገዳም" የሚለውን የነቢዩ ኢሳይያስን ቃል መሠረት በማድረግ በሁለተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ቃለ አዋዲ በሚል ሥያሜ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ደንቦች በፊርማቸው አፅድቀው አውጥተዋል ጥቅምት 15 ቀን 1965 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደርበትን ሰበካ ጉባኤ አስተዳደር ደንብ፤ ግንቦት 1 ቀን 1965 ዓ.ም የቤተ ክርስቲያኒቱን ንዋያተ ቅድሳትና መጻሕፍት አመዘጋገብ፤ ታህሳብ 16 ቀን 1967 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዋና ሥራ አስኪያጅን ሥልጣንና ተግባር የሚወስን ደንብ፣ አውጥተው የቤተክርስቲያንን አስተዳደር ለወቅቱ የሚስማማ ሕግ በመምራትና ንብረቷንና ቅርሷን በማስጠበቅ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። በተለይም የሰበካ ጉባኤ ደንብ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሰለጠነው ዓለም የሚገኙ አብያተ



ክርስቲያናት እንደሚመሩበት የተሻሻለ ደንብ እንድትተዳደር አስችሏታል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከአገልግሎቷ መስፋፋት ጋር አገልጋዮቿም እየበዙ በመሔዳቸውና ከአገልግሎታቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አበል ለመክፈል ባለመቻሏ ብቻ ሳይሆን ያለባትን የወደፊት ግዴታም ቅዱስነታቸው አርቀው በመመልከት የሰበካ አስተዳደር ጉባኤን መስርተው በቃለ አዋዲ እንዲመራ ያደረጉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። ዛሬ በዚህ በሰበካ ጉባኤ አማካኝነት በሚገኝ ገቢ የእያንዳንዱ ሰበካ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናት በየወሩ የማይናቅ ደመወዝ እየተከፈላቸው ይገኛሉ። ይህም የቅዱስነታቸው የድካም ውጤት ስለሆነ የታሪካቸው የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ እንደሚኖር እውን ነው።

### 1.2 የልማት ሥራ

ድኅረ ሢመተ ፕትርክና ቅዱስነታቸው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለአገሪቱ ያስገኙት ሌላው ታላቀ የሥራ ፍሬ የልማት ድርጅት እንዲቋቋም ማድረጋቸው ነው። በተቻለ አቅም ቤተክርስቲያኒቷ በልማት መስክ ከመንግስት ጎን ሆና ረሀብ፣ ድንቁርና፣ በሽታን የምትዋጋበትን መንገድ አስቀድመው ያስቡ ነበር። በአንድ ወቅት ይህን በተመለከተ እንዲህ ብለዋል፡- *"ወደፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ድርሻ በሃይማኖት ሥራ ተካፋይ እንሆናለን የምዕመናኑን ኑሮ የሚሻሻልበትን መንገድ መሻት ተገቢ ነው። በኢኮኖሚ መጠንከር ያስፈልጋል ፍላጎታችንን አምላክ እንዲያሟላልን እንጸልያለን"* ብለው ነበር። በዚህ ፍላጎት መሠረት ቅዱስነታቸው በሐምሌ ወር 1960 ዓ.ም በስዊድን ኡብሳላ ላይ ተሰብስቦ ያነበረው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ጉባኤ ቤተክርስቲያን በልማት ተሳታፊ የምትሆንበትን ዘዴና ሥልት ሲቀየስ በጉባኤው ላይ ተካፋይ ስለ ነበሩ በተከታታይ ዓመታት በተደረጉ ጥረቶች ሁኔታዎች ከተመቻቹ በኋላ በጥር ወር 1963 ዓ.ም "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በልማት ተካፋይነት" በሚል ርዕስ በምክክር ጉባኤ በአዲስ አበባ ተደረገ።

የዚህ ጉባኤ ውጤት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚሽን ከታህሳስ 26 ቀን 1964 ዓ.ም ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org

አስተዳደር ራሱን ችሎ እንዲቋቋም አስቻለ:: ይህ ኮሚሽን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በ6 ሀገረ ስብከቶች ባቋቋማቸው የካህናት ማሰልጠኛዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ካህናትን በልዩ ልዩ ልማት ነክ ትምህርቶች እያሰለጠነ በመላ ሀገሪቱ ከማስማራቱና የካህናቱንም ሕይወት ከመለወጡ ሌላ በድርቅ ለተጎዱ አካባቢ፣ ድንገተኛ አደጋ ለደረሰባቸው ወገኖች በአጠቃላይ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ኢትዮጵያውያን የገንዘብና የቁሳቁስ ርዳታ በማድረግ የቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ ተልእኮ እያሟላ ያለ ድርጅት ነው:: ስለዚህ ይህን የመሰለ ክርስቲያናዊ ድርጅት እንዲመሰረት ያደረጉት ቅዱስነታቸው ለቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ ባለ ውለታ ናቸው::

## 1.3 የምግባረ ሠናይ ድርጅት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በዘመነ ፓትርያርክነታቸው ከመሰረቷቸው ድርጅቶች መካከል የምግባረ ሰናይ ድርጅት አንዱ ነው:: በ1966 ዓ.ም በወሎ ክፍለ አገር አስከፊ ድርቅ ተከስቶ ብዙ ወገኖቻችን ለረሀብና ለሞት በተጋለጡ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከሌሎች በጎ አድራጊዎች ጋር በመተባበር አቅሟ የፈቀደውን የገንዘብ እርዳታ ብታደርግም በዚህ ብቻ መወሰን እንደማይገባ በመገንዘብ ቅዱስነታቸው አዲስ አበባ በሚገኘው በሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት ቅፅረ ግቢ አንድ የህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት እንዲቋቋም አዝዘው በረሀቡ ምክንያት እናትና አባታቸውን ያጡ 50 ለጋ ሕፃናት በዚህ ድርጅት እንዲረዱ አደረጉ:: ይህ በቅዱስነታቸው የተመሰረተው የህፃናት አስተዳደግ ጉባዔ ዛሬ ከ36 ከማያንሱ ሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች በመመሥረት ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በሚገኘው እርዳታ ከ10ሺ ያላነሱ ህፃናትን በማሳደግና በመንከባከብ ላይ ይገኛል:: ይህም የፓትርያርክ ቴዎፍሎስ የአርቆ አስተዋይነት የሥራ ውጤት ነው::

## 1.4 ራስን የመቻል እቅድና ተግባር

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ የምትተዳደረው በአብዛኛው



ከመሬት ግብር በሚገኝ ገቢ ነበር:: "መሬት ላራሹ" የሚለው ድምፅ እየተስተጋባ ሲመጣ ቤተ ክርስቲያን ከመሬት የምታገኘው ገቢ ወደ ፊት አንድ ቀን ሊቋረጥ እንደሚችል አበክረው የተገነዘቡት ቅዱስነታቸው የቤተ ክርስቲያኗን ገቢ ያግዛል ብለው በማሰብ ከባንክና ከዓለም አቀፍ በተገኘ ብድር በኪራይ መልክ የገቢ ምንጭ የሚያስገኙ ታላላቅና መጠነኛ ህንፃዎችን አሳንፀዋል:: በአዲስ አበባ በወረዳ 14 ቀበሌ 07 ከቅድስተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ወደ አራት ኪሎ በሚወስደው መንገድ በስተቀኝ የሚያተዩት ሁለት ባለ 12 ፎቅ ትላልቅ ህንፃዎች ቅዱስነታቸው ኘላናቸውን በውጭ አገር መሐንዲሶች በማሰራት ያሳነጿቸው ናቸው:: እነዚህ ህንፃዎች እስካሁን የተወረሱ ቢሆንም፣ ለመንግሥት እየቀረበ ባለው ጥያቄ መሰረት ለቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ ጠቃሚ ገቢ ሊያስገኙ ይችላሉ:: በዚህ በህንፃ ሥራ ረገድ ሳይጠቀስ መታለፍ የማይገባው ቅዱስነታቸው በአዲስ አበባ ጎፋ ሰፈር በተባለው አካባቢ ያሳነፁት የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራልና በዘመናዊ መልክ ያሳደሱት በምስራቅ ጎጃም አገረ ስብከት የሚገኘው የደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ነው:: ቅዱስነታቸው እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ማነፅ ማደስ ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ ስቴድዮም አካባቢ ያሠሩትን ህንፃ ኪራይ መተዳደሪያ እንዲሆናቸው ለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት በኑዛዜ ሰጥተው እስከ አሁን አበል ይከፈልባቸዋል::

## 1.5 ሢመተ ጳጳሳት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ጳጳሳት ከሊቃውንቷ መካከል መርጣ በራሷ ፓትርያርክ ቀብታ መሾም ከጀመረች አንስቶ መንፈሳዊ ሥራ እድገት እያሳየች በውጭ አገርም እየተስፋፋች በመምጣቷ አዳዲስ ጳጳሳትን መሾም አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ የካቲት 2 ቀን 1964 ዓ.ም 6 ቆሞሳት ለጵጵስና ማዕርግ ተመረጡ:: የእነዚህም ቆሞሳት የጵጵስና በዓለ ሢመት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ እየተመራ የካቲት 5 ቀን 1964 ዓ.ም በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተፈፅሟል:: በዚህ ቀን ከተሾሙት ጳጳሳት መካከል ሁለቱ



www.ethiopianorthodox.org

በውጭ አገር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ሆነው ሲመደቡ የቀሩት 4ቱ በተለያዩ ሀገረ ስብከቶች ተመድበው እንዲሰሩ ተደርጓል:: ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ለ2ኛ ጊዜ ጳጳሳትን ቀብተው የሾሙት በ1968 ዓ.ም ነው:: በዚህ ጊዜ የተሾሙትም ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ፣ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስና ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሲሆኑ የእነዚህን ጳጳሳት ሹመት ሰበብ አድርጎ ወታደራዊው መንግሥት በማይመለከተው የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ በመግባት ቅዱስነታቸውን ለእስራት ብሎም ለሞት አብቅቷቸዋል::

## 1.6 ቤተ ክርስቲያን ማሳነጽ

ቅዱስነታቸው በሐረርጌ ጳጳስ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ ሀገረ ስብከት ህዝቡን የትምህርትና የሃይማኖት ሕይወት የሚያሟሉ ታላላቅ ሥራዎች ሰርተዋል:: ከእነዚህም ሥራዎች ዋና ዋናዎቹ ብንጠቅስ:- በቅዱስነታቸው ስብከት ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተመለሱት የምዕመናን ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየበዛ በመሄዱ ምዕመናን እግዚአብሔርን የሚያመልኩባቸው 12 አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት የንጉሠ ነገሥቱን ድጋፍ እየጠየቁና ምዕመናኑን እያተጉ በዘመናዊ መልክ እንዲሰሩ አድርገዋል:: ቅዱስነታቸው ታላቅና ዘመናዊ የሆነውን የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በጎፋ ሰፈር በግል ገንዘባቸው አሳንፀዋል:: ይህ ቤተ ክርስቲያን ሥራው ተጠናቆ ለአገልግሎት ዝግጁ የሆነው ጥቅምት 17 ቀን 1967 ዓ.ም ነው:: በዘመነ ፓትርያርክነታቸው ከፈፀሟቸው ዓበይት ተግባራት አንዱ የሆነው ይህ ቤተክርስቲያን ነው:: ከአንድ እስከ 6 የተመለከትናቸው ዋና ዋና ነገሮች ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ 2ኛ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ከሢመተ ፕትርክናቸው በኋላ ያከናወኗቸው ሥራዎች ናቸው::

## 1.7 ቅርስን ማስጠበቅ

ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በረጅም ታሪኳ ያፈራቻቸውን የጽሑፍ፣ የሥዕል የቅርፃ ቅርፅ የኪነ ጥበብ ቅርሶችን ተቃራኒ እምነት ያላቸው ኃይሎች አጋጣሚ ባገኙ ቁጥር እየተነሡ ቢያወድሙባትም ወይም ዘርፈው ወደ ባሕር



ማዶ ቢያሻግሩትም ከውድመትና ከዝርፊያ የተረፉ በየጊዜው የተከማቹ በርካታ ቅርሶች አሏት:: ቅዱስነታቸው ከእነዚህ ቅርሶች ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ የሚያደርግ የቅርሳ ቅርስ መምሪያ በመንበረ ፓትርያርኩ ሥር እንዲቋቋም ከማድረጋቸውም በላይ ቅርሶቹ በዘመናዊ ዘዴ የሚጠበቁበትን ሥልት ከመፈለግ አልተቆጠቡም:: በዚህ መርጃ ድርጅት የገንዘብና የመሣሪያ እርዳታን በመጠየቅ የብራና መጻሕፍት የማይክሮ ፊልም ድርጅት አቋቋሙ:: በዚህ ሥራ ልምድና እውቀት ካለው በአሜሪካ ሚኒሶታ በቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርስቲ ከሚገኝ የማይክሮ ፊልም ድርጅት ጋርም በመነጋገር የቴክኒክ ባለሙያ በማስመጣት የዘመን ጥርስ የበላቸው የብራና መጻሕፍት ጨርሰው ሳይጠፉ ከየገዳማቱና ከየአድባራቱ በማሰባሰብ በማይክሮ ፊልም እንዲቀረጹ አድርገዋል::

# 2. ቅዱስነታቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ የፈጸሟቸው ሥራዎች

ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም ጋር ለመቀራረብ በምታደርገው የተፋጠነ እርምጃ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም በዘመናዊ መንፈሳዊ ሥልጣኔ ወደፊት መራመድ አስፈላጊ በመሆኑ ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እየወከሉ በልዩ ልዩ ኢኩሚኒካል (ECUMENICAL) ጉባኤዎች ላይ በመገኘት የኢትዮ ጵያን ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር አቀራ ርበዋታል:: እነዚህም:-

- በ1938ዓ.ም በእንግሊዝ አገር በበርኒንግሃም ከተማ በተደረገው የሰንበት ት/ቤቶች ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በመወከል ተገኝተዋል:: በዚህም ጊዜ የሰንበት ኢኩሜኒካል ትምህርት ቤት ጽሕፈት ቤት አቋቁመዋል:: የትምህርተ ክርስትና የሰንበት ት/ቤት ተብሎም ተሰይሟል::
- በ1940 ዓ.ም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በሆላንድ አመስተርዳም ላይ ሲቋቋም ቅዱስነታቸው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥም በጉባኤው ላይ በመገኘት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥራች አባል እንድትሆን አድርገዋል::
- በ1944 ዓ.ም ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ግሪክ አገር የገባበትን 1ሺ 900 ዓመት ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት በተከበረበት ጊዜ ቅዱስነታቸው የግሪክ



www.ethiopianorthodox.org

ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ባደረገችላቸው ጥሪ መሠረት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስም ከመገኘታቸውም ሌላ ማውንት ኦቶስ በተባለው ሥፍራ ላይ የሚገኙትን ከሃያ በላይ የሚሆኑትን ታሪካውያን ገዳማት በኦፊሴል ጎብኝተው ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የተላከውን ሥጦታ አበርክተዋል።

- በ1947 ዓ.ም ደግሞ እንግሊዝ አገር ማንቼስተር በተባለው ከተማ በተደረገው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ተገኝተዋል። በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርም ደንብ መሠረት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ መልዕክተ ኞች የሚገኙበት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጠቅላላ ጉባኤ በየስድስት ወይም በየሰባት ዓመት አንድ ጊዜ እንዲካሔድ በተወሰነው መሠረት የመጀመሪያው ጠቅላላ ጉባኤ በ1949 ዓ.ም በአሜሪካ ኢቫንስተን ላይ በተደረገ ጊዜ ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያ መልዕክተኞችን በመምራት በጉባኤው ላይ ተገኝተዋል።
- በ1954 ዓ.ም ኒውዴልሂ (ህንድ) ላይ በ1960 ዓ.ም ደግሞ ኡፕሳላ ስዊድን ላይ ጠቅላላ ጉባኤ በተደረገ ጊዜ ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያን መልእክተኞች በመምራት የጉባኤው ተካፋይ ሆነዋል። በ1964 በግሪክ፣ በቁስጥንጥንያና በእስክንድርያ፣ በ1965 ዓ.ም ደግሞ በዮኤስ አሜሪካን፣ በካሪቢያን ደሴቶች፣ በደቡብ አሜሪካ ጉብኝት በማድረግ ለቤተ ክርስቲያኒቱ እንደ ማይክሮ ፊልም ማንሻ ያለ ጠቃሚ ርዳታ ከማስገኘታቸውም ጋር የውጭ ግንኙነትን በማደስና በማጠናከር ሰፊ ድርሻ አበርክተዋል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሰሜን አሜሪካና በካሪቢያን ደሴቶች እምነቷን እንድታስፋፋና እንድታስተ ምር፣ አብያተ ክርስቱያናትም እንዲቋቋሙና እንዲታነፁ የራሷን ካህናት እየላከች ሐዋርያዊ ሥራ የሠራችው ቅዱስነታቸው ባደረጉት ጥረትና በሰጡት ከፍተኛ አመራር መሆኑን ሕያው ሥራቸው ይመሰክራል።
- በ1951 ዓ.ም አቢጃን (አይቤሪኮስት) ላይ የተደረገውን የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ጉባኤ በፕሬዝዳንትነት መርተዋል።
- ከጥር ሁለት እስከ ጥር 12 ቀን 1963 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ በአፍሪካ አዳራሽ በተደረገው ጠቅላላ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይም ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞችን በመምራት ተገኝተዋል።
- በ1975 እ.ኤ.አ ናይሮቢ (ኬንያ) ላይ የተካሔደው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ቴዎፍሎስን የሚቀጥለው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ፕሬዝዳንት አድርጎ መርጧቸው ነበር። ወታደራዊ መንግሥት እድሜአቸውን አሳጠረው እንጂ። በእንደራሴነታቸው ዘመን ወደ ውጭ አገር እየተላኩ በአሜሪካ በትሪንዳድ፣ በቶቤጎ፣ በብሪቲሽ፣ ጊየና፣ በሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ



አብያተ ክርስቲያናት እንዲሰሩና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት በመላው ዓለም እንዲሰራጭ ሐዋርያዊ ጥረት ያደረጉ ታላቅ የቤተክርስቲናችን አባት ናቸው።

የአፍሪካ ሐብያተ ክርስቲያናት ማኅበርም የቅዱስነታቸውን መንፈሳዊ አባትነት አክብሮ በመመልከትና ችሎታቸውን በመረዳት ከሦስቱ ያጠቅላላው ጉባኤ ፕሬዝዳንቶች አንዱ እንዲሆኑ ሁለት ጊዜ በማከታተል ስለመረጣቸው ወታደራዊው መንግስት በግፍ ከሥልጣን አውርዶ እስከ አሰራቸው ጊዜ ድረስ ከሦስቱ ፕሬዝዳንቶች አንዱ ነበሩ። ከዚህ በቀር በ1957 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተደረገው የምሥራቅ ኦርቶዶክስ (Orantal Church) አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በአገራችን እንዲካሔድ የተዋጣለትም ዝግጅት እንዲደረግ ከፍተኛ ጥረት ከማድረጋቸውም በላይ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንም በመምራት በጉባኤው ላይ ተገኝተዋል፤ ጉባኤውም የተሳካ ውጤት እንዲኖረው ከፍተኛ አስተዋ ፅኦ አድርገዋል።

## ቅዱስነታቸው በ1965 ዓ.ም በአሜሪካና በዌስት ኢንደስ ያደረጉት ታሪካዊ ጉብኝት

የዚህ ጉብኝት ጠቅላላ አላማ በወቅቱ አብረው የነበሩት የያኔው አባ ገብረ መድህን ገብረ ዮሐንስ የአሁኑ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ እንዲህ በማለት የሳቸውን የሕይወት ታሪክ በጻፉት መጽሐፍ ገልፀዋል፡- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በዩኤስ አሜሪካ በዌስት ኢንዲስና በደቡብ አሜሪካ ጉብኝት ያደረጉት ከግንቦት 8 እስከ ሰኔ 4 ቀን 1965 ዓ.ም ነበር። ይህ ወቅት በአገር ውስጥ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ዕድገት ለማፋጠን እንደ ልማት ኮሚሽን፣ ሰባካ ጉባኤ፣ ማይክሮ ፊልም ፕሮጀክት ወዘተ... ለመሳሰሉት የሥራ ዘርፎች መሰረት የጣሉበትና የውጭ እርዳታ የሚፈልጉበት ጊዜ ነበር። ከአገር ውጭ ደግሞ ይህ ወቅት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ እያደገ መጥቶ ለአንድነት፣ ለሰላም፣ ለፍትሕ ለእርስ በእርስ መደጋገፍ ትብብር ከፍተኛ ትኩረት የሰጡበትና እነዚህንም አላማዎች



www.ethiopianorthodox.org

ተግባራዊ ለማድረግ በአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች መካከል የጉብኝት ልውውጥ ጎልቶ የሚታይበት ጊዜ ነበር:: እንደዚሁም ቅዱስነታቸው የቅዱስ ጳውሎስን አርአያ በመከተል በሰሜን አሜሪካና በዌስት ኢንዲስ ቀደም አድርገው ያቋቋሟቸውን አብያተ ክርስቲያናት መኅብረትና ማጠናከር የሚፈልጉበት ጊዜ ነበር:: እነዚህን የመሳሰሉት አላማዎች ለማሳካት ነበር ቅዱስነታቸው ይህን ጉብኝት ያደረጉት ከንግግራቸው የተወሰደው ተከታይ ጥቅስ የጉብኝቱን አላማ የበለጠ ግልፅ ያደርገዋል::

*"በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካም ተቀባይነትና ተሰሚነት ያላት ቤተክርስቲያናችን... አስፈላጊውን የልማት መሠረትና የአስተዳደር መዋቅር በመዘርጋት ለስብከት ወንጌል መስፋፋት ግንባር ቀደም ልትሆን ትችላለች:: ለዚህም በዓለም ላይ ሁሉ የእህት አብያተ ክርስቲያናት ጸሎት ግንዛቤና ትብብር እንፈልጋለን"*

ይህን ዓላማ በመያዝ ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ተጉዘው ግንቦት 8 ቀን 1965 ዓ.ም ዮኤስ አሜሪካ የገቡት ቅዱስነታቸው:- በኒውዮርክ ከተማ፣ በኦምሃ፣ ኔብራስካ፣ በሚኒሶታ፣ በዋሽንግተን ዲሲ፣ በአትላንታ፣ ጆርጂያ፣ በናሽቪል፣ ቴነስ፣ በፊላደልፊያ፣ ፔንስልቫንያ፣ በፕሪኒስተን፣ ኒውጀርሲ፣ በቦስተን ማሳቹሴትስ የሚገኙ ታላላቅ ካቴድራሎችን የታወቁ አለማቀፋዊ ድርጅቶችን ሰፋፊ ዮኒቨርስቲዎችን በመጎብኘት ከታላላቅ የሃይማኖትና የፓለቲካ መሪዎች፣ የዮኒቨርስቲ ፕሬዚዳንቶች ጋር በመገናኘት ተነጋግረዋል:: በታላላቅ ካቴድራሎች ቀድሰው አቁርበዋል፣ ዓለምአቀፋዊ የጸሎት ሥነ ሥርአቶችን መርተዋል:: ባሰሟቸው ስብከቶች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምዕመናንን አፅናንተዋል::

በዚህ ጉብኝት ወቅት በቦስተን ማሳቹሴትስ ከተማ ግንቦት 28 ቀን 1965 ዓ.ም በመገኘት የቦስተን ዩኒቨርስቲ የቲኦሎጂ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሸልመዋቸዋል:: በዚህ የሽልማት ሥነ ሥርዓት ላይ የዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት የቅዱስነታቸውን ታላላቅ ሥራዎች በአጭሩ የሚጠቅስ ንግግር አሰምተዋል ይህም:-

*"ከ12 ሚሊዮን የማያንሱ [በወቅቱ የነበረው የአገራችን ምዕመናን ብዛትን የሚያመለክት ነው] ክርስቲያኖች የመንፈስ አባት የሆኑት ለቤተ ክርስቲያንና ለአገርዎ አዲስ አቅጣጫ ለመቀየስ ብርቱ ጥረት የሚያደርጉና በጣም የተከበሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሆይ! በዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ በዓል ያደረጉት ተሳትፎ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ 25ኛ ዓመት ጋር ተገጣጥሟል:: በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤን የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ በዘዴና በፀጋ ያስተናገዱ እርስዎ ነበሩ:: አሁንም ጥንታዊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባል ከሆነችበት ከመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዚዳንት አንዱ ነዎት:: በተለያዩ የሥልጣን ደረጃዎች ላይ ሆነው የካህናትንና የምዕመናንን ትምህርት ለማሳደግ ጥረት አድርገዋል:: አመጣጡ ከንጉሥ ሰሎሞንና ከንግሥተ ሳባ ዘመን ጋር በተያያዘው የተቀደሰ ባሕል መንፈሳዊነት በሕዝቡ ልቦና እንዲሰርፅ አበረታተዋል:: ስለዚህ በዩኤስ አሜሪካ አብያተ ክርስቲያናትና በታላላቅ ዩኒቨርስቲዎች ያደረጉትን ታሪካዊ ጉብኝት በሚያጠቃልሉበት በዚህ ወቅት የቦስተን ዮኒቨርስቲ ለቅዱስነትዎ የቴኦሎጂ የክብር ዶክተርነት ዲግሪ ሲሰጥ ክብር ይሰማዋል"* በማለት ፕሬዚዳንቱ ዲግሪውን ለቅዱስነታቸው ሰጡ:: ይህ የአሜሪካን ጉብኝት 15 ቀናትን ፈጅቷል::

ከዚህ ከአሜሪካ ጉብኝት በኋላ በዌስት ኢንዱስ የጎበኟቸውም አገሮች ነበሩ ኪንግስተን ጃማይካ፣ በጆርጅታውን ጉያና (ደቡብ አሜሪካ)፣ በትሪኒዳድ፣ በቶቤጎ አገሮች ተመሳሳይ ጉብኝት አካሒደው ከትሪኒዳድ አውሮኘላን ጣቢያ ተነስተው በለንደን፣ በጄኔቫና በኢየሩሳሌም አድርገው ወደ ኢትዮጵያ መመለሳቸው የቅዱስነታቸውን የሕይወት ታሪክ ባዘጋጁት መጽሐፍ ላይ 5ኛው የአገራችን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ገልጸዋል::[16]

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በሚሔዱባት አገር አፅንኦት እየሰጡ የሚናገሯቸው ነገሮች የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለማሳደግ ከፍተኛ ራእይ እንደነበራቸው የሚያመለክቱ ናቸው:: እነዚህም:-

1. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተችው በሐዋርያት ዘመ ን ሲሆን ጥንታዊ ባሕሏን ጠብቃ የኖረችና ከ12 ሚሊዮን [በወቅቱ ማለት ነው] በላይ ተከታዮች ያሏት በመሆኗ የምዕራቡ ዓለም ሚሲዮናውያን የአፍሪካን ምድር ከመርገጣቸው ከረጅም ጊዜያት በፊት ጀምሮ በኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ ሥልጣኔንና ባሕልን ማስፋፋት መቻሏን፤

16. የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ታሪክ ከምዕራብ ሀገሮች ጉብኝት በፊትና በኋላ ገፅ 31::



www.ethiopianorthodox.org

2. በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በተቀረው አፍሪካም የክርስትና እምነትን ባልተቀበለ ሕዝቦች መካከል ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ረገድም ይህቺ ቤተ ክርስቲያን የተሻለ እድል ቢኖራትም እስከ አሁን ድረስ በገንዘብና በሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት ይህ ተግባሯን ለማሳካት ትብብርና ድጋፍ የሚያስፈልጋት መሆኑን፤

3. የኢትዮጵያን የልማት ጥረት በመደገፍ በኩልም የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል፤ ፍትሕን ማስፈን፣ ክርስቲያናዊና ሰብአዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል እንዲኖርና በሀብታሞችና በድሆች መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት እንዲጠብ ማድረግ እንደ ሚያስፈልግ፤ ለዚህም ጥረት መሳካት ቤተ ክርስቲያኗ ልዩ ሀላፊነት እንዳለባትና ትምህርትን ማስፋፋት እንደሚገባ ተገን ዝባ ካህናቱን በማሰልጠን ላይ መሆኗን፤

4. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አፍሪካዊ መለያ እንዳላት የጥቁር አፍሪካ ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን በማለት የሰየሟት ቅዱስነታቸው ካልበለፀጉት አገሮች አንዷ ከሆነችው ኢትዮጵያ ርዳታ የሚያስፈልጋት መሆኑን፤ የልማትን ጥረት በማገዝ መተባበር እንደሚገባቸው እነዚህን የመሳሰሉ ለቤተ ክርስቲያናቸው መስፋፋት ብቻ ሳይሆን እውነተኛ ሐዋርያዊ ቤተ ክርስቲያን መሆኗንም በየአጋጣሚው ለውጭ አገር ሰዎች ይገልጡ ነበር::[17]

እኒህ ታላቅና ቅዱስ አባት ከሰማዕትነት ሥነ ገድላቸው ሌላ በቅርብ የሚያቋቸው ሰዎች እንደሚናገሩት:- የሚያስደንቅ ልዩ ሥነ ባህርይ ነበራቸው:: ይኸውም ከሁሉም ነገር በላይ እጅግ በጣም ትዕግስተኛ መሆናቸው ነው:: ብዙዎች ሊታገሱት የማይችሉትን ጉዳይ እርሳቸው በነበራቸው የመንፈስ ጥንካሬ ስሜታቸው ምንም ሳይጎዳ በቀላሉ በሚያሳልፉበት ጊዜ ተመል ካችን ሁሉ ያስገርሙ ነበር:: በቅን አስተሳሰባቸው በሚያቀር ቡት፣ ክብርን ተስማሚነትንና ሞገስን በተመላው ንግግራቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወደዱና የተከበሩ ከመሆናቸውም በላይ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ያስከበሩ ታላቅ አባት ነበሩ:: በመንፈስ ቅዱስ ጠባቂ ሆነው ለተሾመላት ቤተ ክርስቲያናችን በዓይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ ታላቅ ሰፊ ሥራ ሰርተዋል::

ይሁን እንጂ ሕይወት ተለዋዋጭ እንደመሆንዋ በአንድ ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ክፉና ደጋግ ዘመናት ይፈራረቃል:: ከ1933 - 1966 ዓ.ም የነበረው መልካም ዘመን አልፎ የችግር ዘመን ሲተካ ከማንም በላይ ቤተ ክርስቲያናችን ችግር ገጥሟታል:: ይህም ታላቁን አባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ

17. ዝኒ ከማሁ ገጽ 49-50



በሰማዕትነት የተገደሉበት ይህ ዘመን ነበር:: አብረዋቸው ታስረው የነበሩ ነገር ግን በአጋጣሚ ከሞት የተረፉ ሰዎች እንደመሰከ ሩት ቅዱስነታቸው ለመጨረሻ ጊዜ ከታላቁ ቤተመንግስት እስር ቤት የተወሰዱት ሐምሌ 7 ቀን 1971 ዓ.ም ነበር:: ሲወ ሰዱ ነው እንጂ ወዴት እንደሚሔድ በምን አኳኋን እንደ ተገደሉ፤ የትስ እንደተቀበሩ መስካሪዎች የሚያውቁት ነገር የለም:: ስለዚህ የእኝህ ፓትርያርክ ሕይወት ለቤተሰቦቻቸው፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብና በመላው ዓለም የሚገኙ ወዳጆቻቸው እን ዲሁም ለሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ሁሉ ለ13 ዓመታት ስውር ሆኖ ቆይቷል:: ስውር እንዲሆንም የተደረገበት ምክንያት እንኳን ለሞት ለእስራት እንኳ የሚያበቃ ምንም ወንጀል ሳይኖ ርባቸው ያለፍትሕ በግፍ በመገደላቸው ነው::

የቅዱስነታቸው መቃብርና አሰቃቂ አሟሟት ያውቁ የነበሩ አቶ ቀንአ የተባለ ሐኪም ነሐሴ 5 ቀን 1983 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሬድዮ ጣቢያ ለጋዜጠኞች በሰጡት ቃለ ምልልስ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አዲስ አበባ በሚገኘው በእንጦጦ አውራጃ በከፍተኛ 12 ቀበሌ 22 በሚገኘው በራስ አሥራተ ካሳ ግቢ ውስጥ ከሌሎች እስረኞች ጋር በሚዘገንን ሁኔታ በገመድ አንቀው መግደላቸውንና እዚያው መቀበራቸውን ከፍ ተብሎ የተገለፁ ሰው አስታወቁ:: ስለዚህ ቤተሰቦቻቸውና መላው የኢት ዮጵያ ሕዝብ የእኒህን ታላቅ ቅዱስ አባት ሞት የተረዳው በዚች ሰዓት ነው:: መቃብሩ ጥልቀት ስለነበረው ሚያዝያ 20 ቀን 1984 ዓ.ም ከጠዋቱ 4 ሰዓት ቁፋሮ ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 22 ቀን 1984 ዓ.ም ከቆየ በኋላ ልክ 8 ሰዓት ላይ የቅዱስነታቸው አፅም ለብሰውት የነበረው ሐር መሰል ቀሚስ ከኋላው ክፍት የሆነ ጫማቸው፣ በራሳቸው አድርገውት የነበረው የምንኩስና ቆብ ከምን አይነት ጨርቅ እንደተሰራ አይታወቅም እንጂ የቆቡ ጨርቅ ተበልቶ የቆቡ ማወፈሪያ ጥጥ መሰል ነገሮች ከአፅሙ ራስ ቅል ጋር አብረው ሆኖ የቅዱስነታቸው አፅም በደረት ተደፍቶ እንደተጣለ ሊገኝ ችሏል::

የቅዱስነታቸው አፅም እንዲህ በማያጠራጥር ሁኔታ ከተ ገኘ በኋላ ሚያዝያ 23 ቀን 1984 ዓ.ም ሳጥኑ በወርቀ ዘቦ የተጌጠ መጎናፀፊያ ተላብሶ በብፁአን ሊቃነ ጳጳሳት ትከሻ ተይዞ ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ባለውለታ መሆናቸውን የሚጠ



www.ethiopianorthodox.org

ቁም ያሬዳዊ ዜማ እየተሰማ ወደ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተክርስቲያን አርፎ ከቆየ በኋላ ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ.ም በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አውደ ምህረት ጸሎተ ፍትሐት ተደርጎለት ሲያበቃ ያን ጊዜ አቃቤ መንበር የነበሩት ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ በቅዱስ ሲኖዶስ ስም ያስተላለፉት መልዕክት የሚከተለው ነበር:-"*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከዛሬ ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሰማዕት ተብለው እንዲጠሩ ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል*" ሲሉ ያስተላለፉት ነው::

ይህ መልዕክት በወቅቱ በቦታው ተሰብ ስቦ የነበሩት ብፁዐን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች አምባሳደሮችና ካህናት የሚገኙበት ሕዝብ በጭብጨባ የተቀበለው ስለሆነ የሰማዕትነቱ ስያሜ ጸድቆ እነሆ መጠሪያ ቸው ሆኗል:: የቅዱስነታቸው የሰማዕቱ የአቡነ ቴዎፍሎስ አፅም በክብር ያረፈው ራሳቸው ባሠሩት በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ነው:: በዚህ ቅፅረ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ነታቸው ቤተ መዘክርና ሐውልት ይገኛል::

በመሆኑም እስከ አሁን እንደተመለከትነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ስለ እድገትዋ ብዙ በመድከም፣ ይልቁንም ከእስ ክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር በተደረጉት ድርድሮች መንበሩ እንዲገኝ ጉልህ አስተዋፅኦ ያደረጉ፤ ስለ ክብሯም በሰማዕትነት በመሰዋት ከፍተኛ ውለታ ለዋሉላት ለእኝህ ታላቅ አባት ከላይ የተጠቀሰውን የሰማዕትነት ስያሜ፣ ቤተ መዘክር በማቋቋም ስማቸው ሕያው ሆኖ እንዲኖርና ለትውልድ እንዲተላለፍ አድ ርጋለች:: የቅዱስነታቸውን የሕይወት ታሪክና ሥራቸውን የያዙ ዘገባዎችን በማሳተም ትውልዱ እንዲያውቀው አበርክታለች:: አንድ ትጉህ ሐዋርያ ሊቀበል የሚገባውን እስከ ደም ጠብታ ድረስ የመመስከር እድል አግኝተዋል:: እኔም የቅዱስነታቸውን የሕይወት ታሪክና ሥራ እንደዚሁም ፍፃሜያቸውን በተመለከተ የታተሙትን የጽሑፍ መረጃዎች በምንጭነት ተጠቅሜባቸ ዋለሁ::[18]

18. ሰማዕቱ፡ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ.ም:: ዝክረ ቴዎፍሎስ ሰማዕት ሐምሌ 4 ቀን 1989 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከመምህ ርነት እስከ ፓትርያርክነት 1963 ዓ.ም፤ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ታሪክ ከምዕራብ ሀገሮች ጉብኝት በፊትና በኋላ 1987 ዓ.ም::/



## ስለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የተሰጡ የአክብሮትና የአድናቆት አስተያየቶች

ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዕድ ገት ለዓለም ሰላምና ለክርስትና ትምህርት ማስፋፋት ያሳዩትን በተግባር ላይ የተመሰረተ መንፈሳዊ እንቅስቃሴና ችሎታ በተለ ይም ከ1930ዎቹ ጀምሮ በፓትርያርክነት ሥልጣን ላይ እስከ ነበሩበት ጊዜ ድረስ በኢኩሚኒካል ግንኙቶች የነበራቸውን ጉልህ ተሳትፎ እንዲሁም ሰብአዊና መንፈሳዊ ሰብእናቸውን በማድነቅ በማክበር ልዩ-ልዩ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ተወካዮች ጋዜጠኞችና ዕውቅ ሰዎች ከሰጧቸው አስተያየቶች መካከል ጥቂቶችን በጥቅስ መልክ አስፍረናቸዋል::

❖ *"...እናታችን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ ከመንፈሳዊ ሹማምንቶችዋ በዋጋና በችሎታ ከሁሉ ከፍ ያሉትን ቅዱስነ ትዎን ርዕስና መሪ አድርጋ በመምረጥዋ እጅግ ደስ ብሎናል"*

[ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቫስኪን የመላው አርመን ቤተ ክርስቲያን ካቶሊኮስ ሚያዝያ 29 ቀን 1963 ዓ.ም]

❖ *"...ቅዱስነትዎ... ለዓለም ሰላም ለአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የዓላ ማው ደጋፊ መሆንዎ ስለማይጠረጠር ቅዱስነትዎ ለዚህ ተግባር መመ ረጥ ለእኛ በክርስቶስ ወንድሞችዎ ለሆነው ሁሉ ከፍ ያለ የመንፈስ ደስታ ስለ አተረፈልን ከእግዚአብሔር በተሰጥዎ የፍቅር ምርኩዝ የኢ ትዮጵያን ቤተክርስቲያን በቅን እንዲያገለግሏት እድሜ እንዲያጎናፅፍዎ አምላካችን ፈቃዱ ይሁን"*

[ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጁስቲንያን የሮማንያ ፓትርያርክ]

❖ *«የኢትዮጵያ ሕዝብ ንግሥት ሕንደኬ ከዓለም አማኞች መጀመሪያ እንደነበረች ሁሉ ብፁዕ ወቅዱስነትዎ ከጥንት ጀምሮ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረውን አለመግባባት ለማስወገድ ጥረት ካደረ ጉት የመጀመሪያው በመሆንዎ የቅዱስነትዎን በመካከላችን መገኘት የምንመለከተው እንደታላቅ የእግዚአብሔር በረከት ነው:: ከዚህም የተነሣ ብርሃን ገፅዎ መላ ኢትዮጵያን በሥዕል ሊያሳየን ችሏል»*

[ብፁዕ አቡነ ኤሮኒሞስ የአቴንስና የመላው ግሪክ ሊቀ ጳጳስ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ግሪክን በጥቅምት ወር 1964 ዓ.ም. በይፋ በጐበኙበት ጊዜ የተናገሩት::] ዜና ቤተ ክርስቲያን ልዩ እትም 1964 ገፅ 40



www.ethiopianorthodox.org

❖ "... በአባታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ፈቃድ ለዚህ ከፍተኛ ክብር መብቃትዎ በከፍተኛ ሥራዎና በችሎታዎ ነው::
[አባ መቃርዮስ የቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ወኪል]

❖ "...ለመላ ኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ደስታ የሆነው ይህ ከፍተኛ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የፓትርያርክነት በዓል ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አንድ አካል የሆኑት የመላው ምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲ ያናት ደስታ ነው..."
[በእስክንድርያ የግሪክ ፓትርያርክ]

❖ «በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት በታላቁ አትናቴዎስ ተቀብቶ ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ በሆነው በቅዱስ ፍሬምናጦስ አማካኝነት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተላለፈችው ሐዋርያዊት ሥልጣን በብፁዕ ወቅዱስነትዎ ላይ እንዳረፈች እናረጋግጣለን... በአፍሪካ አኅጉር ውስጥ እንደ ታላቅ ሐውልት አድርገው የገመቱት የመካከለኛው ዘመን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ታሪካዊ ራእይ ከፍተኛ ወኪል መሆንዎን በቅዱስነትዎ ሰውነት ላይ እናያለን::»
[ብፁዕ ወቅዱስ አቴናጎራስ የቁስጥንጥንያና የኢኩሙኒካል ፓትርያርክ ቅዱስነታቸው ቁስጥንጥንያን በጐበኙበት ጊዜ የተናገሩት] ዜና ቤተ ክርስቲያን ልዩ እትም 1964 ገፅ 40

❖ «ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ በቅዱስነትዎ የሚታወቁት በኢትዮጵያ አገርዎ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ነው:: ለዚህ ይህ ዛሬ የተሰጥዎ ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ለቅዱስነትዎ የሚገባ ነው»
[ሜትሮፖሊታን ኒቆዲሞስ የሩስያ ቤተ ክርስቲያን ተወካይ]

❖ "... ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ ቅዱስነትዎ ለዓለም ሰላም ጥረት ከሚያደርጉት አበው አንዱ ነዎት ባለዎት ዕውቀትና ልዩ ችሎታ መልካም ታሪክ ያላትን ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያንን ወደፊትከተራመዱት የዓለም አብያተ ክርስቲያን ጋር እኩል እንደሚያራምዱአት ተስፋ ጥለንብዎታል..."
[የቡልጋሪያ ቤተ ክርስቲያን ተጠባባቂ ፓትርያርክ]

❖ "ዛሬ በመላው ዓለም ጦርነት በበዛበት በዚህ አስቃቂ ጊዜ በኢትዮጵያ የተገኙት አዲሱ ሙሴ ብፁዕ ወቅዱስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት አቡነ ቴዎፍሎስ እጃቸውን ከዘረጉ ሳያጥፉ ስለ ዓለም ሰላም እንደሚፀልዩና ኢትዮጵያውያን ምዕመናንም እንደሚረዱ አቸው እናምናለን"
[የግሪክ ሊቀ ጳጳስ የአቡነ ኤሬኒሞስ ተወካይ]

❖ "ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ ይህ ከፍተኛ የፓትርያርክነት ሹመት የሰላምና የሥራ ሹመት እንደሚሆን እንመኛለን"
[የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፓፓ ጳውሎስ ስድስተኛ ተወካይ]



## ከመጽሐፎች ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች ስለ ቅዱስነታቸው የተሰጡ አድናቆት

❖ "በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የአገራቸው የኢትዮ ጵያ ጳጳሳት የሚሾሟቸው አቡነ ቴዎፍሎስ ለሁለተኛ ፓትር ያርክነት ተመርጠዋል"
[አልሀራም ጋዜጣ ሚያዝያ 30 ቀን 1963 ዓ.ም]

❖ "...ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ... በብሔራዊና በኢንተርናሽናል መንፈሳዊ ጉባኤዎች ላይ በመገኘት... ያቀረቧቸው ጠቃሚ ሀሳቦች እውነተኛ የሃይማኖት መሪ የሚያሰኟቸው ሆነው ተገኘ ተዋል፤ ስለ ትህትናቸው፣ ስለ ተመራማሪነታቸው፣ ለሰው ልጆች ደህንነት አሳቢና ተቆርቋሪ ስለመሆናቸው በሰፊው ይነ ገራል፤ ብፁዕነታቸው ዓለምን ተዘዋውረው ያዩ በሥልጣኔ የሚያምኑ የሰውን ሁኔታ አጣርተው የተረዱና ለዓለም ሰላም አጥብቀው የሚጸልዩ የሃይማኖት አባት ናቸው"
[የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ 19ኛ ዓመት ቁጥር 19]

❖ «ኢትዮጵያ በአዲሱ አመራርዋ ከሌላው ዓለም ጋር ለመቀራረብ በምታደርገው የተፋጠነ እርምጃ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ወደፊት መራመድ አስፈላጊ በመሆኑ ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስ ቲያን እየወከሉ በልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች ላይ በመገኘት የኢ ትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር አቀራርበዋል»
[ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከመምህርነት እስከ ፓትርያርክነት] 1963 ዓ.ም.

❖ «ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ነቢይም ሐዋርያም ነበሩ... ነቢይ ነበሩ ሲባል በመጭው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ሊደርስባት ከሚችለው የለውጥ ማዕበል የምትድንበትን አስቀድመው በመረዳት የቤተ ክርስቲያን መድኅን የሆነውን የሰበካ አስተዳደር ጉባኤን በማዋቀራቸው ነው:: ....ሐዋርያ ነበሩ ሲባል ደግሞ ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋትና ላልደረሳ ቸው ለማዳረስ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ራሳቸው ጭምር እየሔዱ በማስተማርና እንዲሁም በድርጅትና በገንዘብ በማጠናከር ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት መሠረት መጣላቸው ነው::»
[ፍንጭ ፍተሻ በዶክተር ሐዲስ የሻነው 1998]

❖ "...ይህን ማዕርግ ብፁዕነታቸው ያገኙት ያለፈው ሥራ ጊዜያቸው ጉልህ በመሆኑ ነው:: ...ብፁዕነታቸው ለሁሉም ብድግ ብለው እንግዳ መቀበልን ይወዳሉ:: ፈገግታቸውና አነጋገራቸው ወዝ አለው:: ቀና ብለው መቀ መጥን ይወዳሉ፤ ሲወያዩ በሐሳብ የሚጠመዱ ይመስላሉ፤ ገና ብዙ



www.ethiopianorthodox.org

*የሥራ እርምጃ የሚጠብቃቸው መሆኑን የተረዱ ሆነው ይታያሉ... ከኢትዮጵያ ትምህርት ሌላ እንግሊዝኛ አቀላጥፈው ይናገራሉ፤ ጣልያ ንኛ ችሎታ አላቸው አረብኛ ይቀናቸዋል። እነዚህን ሁለት ቋንቋዎች የተማሩት ሰው በመለመን በግል ጥረት ነው ለምን እንደተማሩ ሲጠየቁ ማወቅ ይበጃል ብዬ ነው ብለዋል።"*

[አዲስ ዘመን ጋዜጣ ግንቦት 18 ቀን 1963 ዓ.ም]

- *"...ለዚህም ነው ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አቡነ ቴዎፍሎስ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ቀዳማዊ ሲሆኑ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለተጎናፀፈችው ፍፁም ነፃነት ቀዳማዊ ፓትርያርክ ሆነው የተሰየሙት ይህም ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለአገሪቱም ሕዝብ ዳግም ልደት ተብሎ ሊታሰብ ይገባዋል። ..."*

  [ድምጸ ተዋህዶ ጋዜጣ]

- *«... ምሥጢራትን በተሞላው በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የነበራቸው ጥልቅ ዕውቀት የመጻሕፍትን ትርጓሜ የማመስጠር ተሰጥኦዋቸው፤ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ሥራዎች ከፍልስፍናና ከነገረ መለኮት አንጻር የመተርጐም ችሎታቸው ለምሁርነታቸው ጋልዕ ማስረጃዎች ነበሩ።... ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ ትኩረት ይሰጡ ስለነበር ፓትርያርክ ሆነው ከተሾሙ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ በርካታ ጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናትንና የመንግሥት መሪዎችን የጐበኙ ሲሆን፤ ይህ ጉብኝታቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ካሉ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ጋር የቅርብ ግንኙነት እንድትፈጥር ጥርጊያ መንገድ ከፍቶላታል»*

  [አምስተኛው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ አጭር የሕይወት ታሪክ የምዕራብ ሀገሮች ጉብኝት በፊትና በኋላ] 1987 ዓ.ም.

- *...እ.ኤ.አ 1948 ዓ.ም አመስተርዳም ላይ በተደረገው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ብፁዕነታቸው በመገኘት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኩል አስፈላጊውን ጥያቄ ለጉባኤው አቅርበዋል ... የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥራች አባል እንድትሆን ስላደረጓት ብፁዕነታቸው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ባለውለታ አባት ናቸው። ...ትዕግስት ክፉን በክፉ አለመቃወም እድገት ወይም ዕርጋታና አርቆ አስተዋይነት በተፈጥሮ ጸጋ የተገኙ የብፁዕነታቸው የተለዩ ሀብታት ናቸው።*

  [ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ 25ኛ ዓመት ቁጥር 63]



# የኢትዮጵያ ነገሥታት ስም ዝርዝር
# ከአብርሀ አጽብሐ እስከ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ

ኢትዮጵያ በምድር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የመሠረተችና ሰዎች የኖሩባት ሀገር ናት። ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ሕልውናዋ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በምድሯ ላይ ወጥ የሆነ መንግሥት የነበረባት ሀገር ናት። እስራኤላውያን የመጀመሪያውን ንጉሥ ሳአልን ከማንገሳቸው በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ንጉሥ እንደነበር ታሪክ ያስረዳናል። በኢትዮጵያ መዲና በቅድስቲቱ የታሪክ፣ የባሕል፣ የሃይማኖት ከተማ በሆነችው በአክሱም ከ1030 ዓ.ዓ. ጀምሮ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ነበረች። በዚህ መሠረት በአክሱም ቤተ መቅደስ ሥርዓተ ንግሥና ተፈፅሞላቸው የነገሡ ነገሥታት ብዙ ናቸው።

ከመጀመሪያው ኒገደ አሪ እስከ ንጉሥ ስብታህ 21 ነገሥታት፣ ከነገደ ካም ንጉሥ ሰብታህእስከ ጴአሬ 1ኛ22 ነገሥታት፣ ከነገደ እግአዝያን ንጉሥ አኩሁናስ እስከ ንግሥተ ሳባ [ነገደ ሴም ወይም ደቂቀ ዮቅጣን] 52 ነገሥታት፣ ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ባዚን 67 ነገሥታት፣ ከልደተ ክርስቶስ በኋላ እስከ አብርሐ ወአፅብሐ 4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን 36 ነገሥታት፣ ከአብርሐ ወአፅብሐ እስከ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ድረስ 121[1] ነገሥታት ነግሠዋል።

በጠቅላላው በአክሱም ርዕሰ ከተማነት ከ255 ያላነሱ ነገሥታት ዘውድ ተቀዳጅተው በመንገሥ ኢትዮጵያን የመሩ ሲሆን፤ አክሱምም ለ5392 ዘመናት ያህል በሃይማኖት ማዕከልነት በመንበረ መንግሥትነት ታሪክ የመዘገባት ከተማ ናት። በዚህ መሠረት የክርስትና ሃይማኖት በዘመናቸው ከተገለጠው ከአብርሐ አጽብሐ ጀምሮ የነገሡ የኢትዮጵያ ነገሥታት ስማቸውና የነገሡበት ዘመን በዝርዝር ከዚህ ቀጥሎ ሰፍሯል።

1. አንዳንድ የታሪክ መጻሕፍት በዘመነ ክርስትና የገሡትን ነገሥታት ብዛት ከላይ ከጠቀስኩት ቁጥር ከፍና ዝቅ ያደርጉታል። ሆኖም ተቀራራቢ መስሎ የታየኝ ይህ ቁጥር ብቻ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።



www.ethiopianorthodox.org

| ተ.ቁ. | ከአብርሃ ወአፅብሐ እስከ ኃይለሥላሴ ያሉ ነገሥታት | በዙፋን ላይ የቆዩበት ዘመን | የነገሡበት ዓ.ም |
|---|---|---|---|
| 1 | አብርሐና አፅብሐ በአንድነት | 26 | 332 |
| 2 | አብርሐ ለብቻው | 12 | 344 |
| 3 | አስፍሐ ደልዝ | 7 | 351 |
| 4 | ሣህል | 14 | 365 |
| 5 | አርፍድ /ገብረ መስቀል/ | 4 | 369 |
| 6 | አድኃና ንግሥት | 5 | 374 |
| 7 | ርትዕ | 1 | 375 |
| 8 | አስፍሐ 2ኛ | 1 | 376 |
| 9 | አጽብሐ 2ኛ | 5 | 381 |
| 10 | አሜዳ 1ኛ | 15 | 396 |
| 11 | አብርሃ 2ኛ | 7 ወር | |
| 12 | እለሣህል | 2 ወር | |
| 13 | እለገበዝ | 2 ዓመት | 398 |
| 14 | ሣህል | 4 | 402 |
| 15 | አብርሀ | 10 | 412 |
| 16 | አድህና ንግሥት 2ኛ | 6 | 418 |
| 17 | ኢዮአብ | 10 | 428 |
| 18 | ጸሐም | 2 | 430 |
| 19 | አሜደ 2ኛ | 1 | 431 |
| 20 | ሣህል ሣህለ አሕዛብ | 2 | 433 |
| 21 | ጽባሕ /መሐረነ ክርስቶስ/ | 3 | 436 |
| 22 | ጸሐም 3ኛ | 2 | 438 |
| 23 | እልገበዝ 2ኛ | 6 | 444 |
| 24 | ኢጋሌ /ኢጋቤ/ | 1 | 445 |
| 25 | ሌዊ | 2 | 447 |
| 26 | አሜዳ 3ኛ /ያዕቆብ/ | 3 | 450 |
| 27 | አርማህ ዳዊት | 14 | 464 |
| 28 | አምሲ | 5 | 469 |
| 29 | ሶልአዶባ | 9 | 478 |
| 30 | አልአሜዳ | 8 | 486 |
| 31 | ታዜር 2ኛ ስሙ ኤዛና | 7 | 493 |
| 32 | ካሌብ | 30 | 523 |
| 33 | ዘእስራኤል | 1 ወር | |
| 34 | ገብረ መስቀል | 14 | 537 |
| 35 | ቆስጠንጢኖስ ሳህል | 28 | 565 |
| 36 | ወሰን ሰገድ መሐረነ ክርስቶስ | 15 | 585 |



| | | | |
|---|---|---|---|
| 37 | ፍሬ ሠናይ | 23 | 603 |
| 38 | አድርገዝ → መሐመድ ተነሣ | 20 | 623 |
| 39 | አካለ ውድም | 8 | 631 |
| 40 | ግርማ አስፈር | 15 | 646 |
| 41 | ዝርጋዝ | 10 | 656 |
| 42 | ድግና ሚካኤል | 21 | 682 |
| 43 | ባህር ኢክላ | 19 | 702 |
| 44 | ጉም | 24 | 711 |
| 45 | አስጉምጉም | 5 | 730 |
| 46 | ላትም | 16 | 746 |
| 47 | ተላትም | 21 | 766 |
| 48 | ያደኅሽ | 13 | 780 |
| 49 | አይዞር | 6 ሰዓት | |
| 50 | ድድም | 5 | 785 |
| 51 | ውድድም | 10 | 795 |
| 52 | ውድማ አስፈሬ | 30 | 725 |
| 53 | አርማህ | 5 | 830 |
| 54 | ድግናዝን | 19 ዓመት 10 ወር | 849 |
| 55 | ግዳዝን | 10 ወር | 850 |
| 56 | ጉዲት /ዮዲት/ | 40 | 890 |
| 57 | አንበሣ ውድም | 20 | 910 |
| 58 | ድልነአድ ማዕደይ | 10 | 920 |

## ከዛጉዬ እስከ ይኩኖ አምላክ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 59 | መራ ተክለሃይማኖት | 13 | 933 |
| 60 | ጠጠውድም | 40 | 973 |
| 61 | ጃን ስዩም | 40 | 1013 |
| 62 | ግርማ ስዩም | 40 | 1053 |
| 63 | ይምርሐነ ክርስቶስ | 40 | 1097 |
| 64 | ቅዱስ ሐርቤ | 40 | 1233 |
| 65 | ላሊበላ | 40 | 1273 |
| 66 | ነአኩቶ ለአብ | 40 | 1313 |
| 67 | ይትባረክ ወልዱ ለላሊበላ | 17 | 1232 |
| 68 | መይራሪ | 15 | 1245 |
| 69 | ሀርበይ | 8 | 1255 |



www.ethiopianorthodox.org

## የአፄ ይኩኖ አምላክና የልጆቻቸው መንግሥት

| | | | |
|---|---|---|---|
| 70 | ይኩኖ አምላክ | 15 | 1268 |
| 71 | አግባ ጽዮን | 9 | 1277 |
| 72 | ጽንፈ አርእድ | 1 | 1278 |
| 73 | ሕዝበ አሰግድ | | 1279 |
| 74 | ቅድመ አሰግድ | 1 | 1280 |
| 75 | ጃን አሰግድ | 1 | 1281 |
| 76 | ሰብአ አሰግድ | 1 | 1282 |
| 77 | ውድም አርዕድ | 15 | 1297 |
| 78 | አምደ ጽዮን | 30 | 1327 |
| 79 | ሰይፈ አርዕድ | 28 | 1355 |
| 80 | ውድም አስፈሬ | 10 | 1365 |
| 81 | ዳዊት | 30 | 1395 |
| 82 | ቴዎድሮስ | 4 | 1399 |
| 83 | ይስሐቅ | 15 | 1414 |
| 84 | እንድርያስ | 6 ወር | |
| 85 | ሕዝበ ናኝ | 4 | 1418 |
| 86 | በድል ናኝ ከእንድርያስ ጋር | 1 ፤ 6 | 1419 |
| 87 | አምደ ኢያሱ | 7 | 1426 |
| 88 | ዘርአ ያዕቆብ | 34 | 1460 |
| 89 | በእደ ማርያም | 10 | 1470 |
| 90 | እስክንድር | 16 ፤ 15 | 1486 |
| 91 | አምደ ጽዮን | 7 ወር | 1487 |
| 92 | ናኦድ | 13 | 1500 |
| 93 | ልብነ ድንግል | 30 | 1530 |
| 94 | ገላውዴዎስ | 19 | 1549 |
| 95 | ሚናስ | 4 | 1553 |



## ከሰርፀ ድንግል እስከ መሳፍንት

| | | | |
|---|---|---|---|
| 96 | ሰርፀ ድንግል | 34 | 1587 |
| 97 | ያዕቆብ | 7 | 1594 |
| 98 | ዘድንግል | 1 | 1595 |
| 99 | ሱስንዮስ | 28 | 1623 |
| 100 | ፋሲል | 36 | 1659 |
| 101 | ዮሐንስ 1ኛ | 15 | 1674 |
| 102 | ኢያሱ አድያም ሰገድ | 24 | 1698 |
| 103 | ተክለ ሃይማኖት 1ኛ | 2 | 1700 |
| 104 | ቴዎፍሎስ | 3 | 1703 |
| 105 | ዮስጦስ | 5 | 1708 |
| 106 | ዳዊት | 5 | 1713 |
| 107 | በካፋ | 9 | 1722 |
| 108 | ዓለም ሰገድ ኢያሱ | 25 | 1747 |
| 109 | ኢዮአስ | 15 | 1762 |
| 110 | ዮሐንስ | 5 ወር | |
| 111 | ተክለ ሃይማኖት 2ኛ | 7 ዓ፣ 7 ወር | 1770 |
| 112 | ሰሎሞን | 2 | 1772 |
| 113 | ተክለ ጊዮርጊስ | 5 | 1777 |
| 114 | ዘመነ መሳፍንት (ሣህለ ሥላሴ ንጉሥ ሸዋ ኃይለ መለኮት) | 88 ዓ. 3ወ<br>33 ዓ. 4ወ | 1845<br>/1838-1846/ |
| 115 | ቴዎድሮስ 2ኛ | 8 | 1860 |
| 116 | ተክለ ጊዮርጊስ 2ኛ | 15 | 1863 |
| 117 | ዮሐንስ 4ኛ | 18 | 1881 |
| 118 | ዳግማዊ ምኒልክ | 47 ዓ. 7 ወ | 1906 |
| 119 | ኢያሱ | 3 | 1909 |
| 120 | ዘውዲቱ | 13 ዓ. 7 ወ | 1922 |
| 121 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ | 43 | 1923 |


ለዚህኛው ክፍል የመጻሕፍት ምንጭ:

- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እድገትና ነፃነት በኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት 1944
- አክሱም የሃይማኖት የሥልጣኔ መሠረት [የሐውልቱን መመለስ ምክንያት በማድረግ በመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽ/ቤት የተዘጋጀ] ሚያዝያ 1997


ж ж ж



www.ethiopianorthodox.org

# እጨጌዎች

ይህ ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠው ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ነው። መሥራቹም እርሳቸው ናቸው። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ «መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ» ላይ ይህ ስያሜ እንዴት እንደመጣ እንደሚከተለው አስፍረዋል:-

«ሐጼጌ /ማዕከላይ ስም/፤ ዘይቤው እጨ እጨጌ ሱታፌ መንግሥት፤ ባለ ሲሦ መንግሥት፤ ምሥጢሩ ሊቀ ሀገር፤ ሊቀ ካህናት ርዕሰ አድባራት ወገዳማት። ኢትዮጵያ እንደ ኒቂያ ሕግ ትምህርቱንና ንጽሕናውን ጠባዩንና አኗኗሩን አስተዳደጉን አይታ መርምራ ይደልዎ ብላ መርጣ መስክራ ባልሾመችው ሌሎች ከወገናቸው መርጠው በሚሾሙት ቋንቋውን በማታውቀውና ቋንቋዋን በማያውቅላት በባዕድ በእንግዳ በውጭ ሀገር ጳጳስ ስለተመራች… ክብሯንና መንበረ ክብሯን አካታ ፈፅማ ይቅርብኝ ብላ ለባዕድ መስጠትን ስለጠላች አፍአዊ ስሙን መልካዊ ወይም ባስልዮስ እንደማለት ሐጼጌ ብላዋለች። ጳጳስ ሲታጣ በግልፅ የጳጳስ ሥራ እየሠራ አቡንና እጨጌ ይባላል፤ ጳጳስም ቢኖር ሳገሩ እንግዳ ለሕዝቡ ባዳ ስለሆነ፤ አፈ ድዳ ቀንደ ጐዳ መስሎ ያቀረቡለትን ቅስና ዲቁና ከመሾም በቀር ሊፈርድና ሊተች ሊሰብክ ሊያስተምር አይችልምና በሕዝብና በካህናት ላይ ሥልጣኑና መብት ወትሮ የእጨጌ ነው። በዕግዕና በዕጋዕ ዘይቤም ሲፈታ፡ መጨጊያ መክዳ ያሰኛልና ይህ ስም ዕጨግናን ከጽጽስና አዛምዶ አዋሕዶ አጣምሮ አስተባብሮ ያሳያል። ይኸውም እንደ ግራና ቀኝ መከዳ ንጉሡን አማክለው አቡኑ በቀኝ እጨጌው በግራ መቀመጣቸው ይታወቃል። አቡን ሲታጣ ግን ቀኙ የእጨጌው ነው» ይላሉ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ገጽ 457።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ሥላሴ ደግሞ ዋዜማ በተባለው መጽሐፋቸው ስለዚህ ስም ትርጉም እንደሚከተለው አስቀምጠዋል። «አቡነ ተክለ ሃይማኖት በደቡብ ገብተው ሲያስተምሩ በተለይ ወላይታ /አማሮ/ ላይ የአማሮ ሕዝብ ሽምግልናቸውን አይቶ «ጨ» አሏቸው ጨ ማለት በአማሮ ቋንቋ ሽማግሌ ማለት ነው። በዘመን ብዛት ግን እጨጌ ተባለ። ትርጓሜውም ሽማግሌ ሆይ ማለት ነው» ይላሉ። /ዋዜማ ገፅ 101/



ከላይ እንደጠቀምኩት እጨጌነት የጀመረው በ1263/63/ ዓ.ም. ይኩኖ አምላክን ቀብተው ባነገሡት በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ነው። በዚህ መሠረት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አመራር /አስተዳደር/ ውስጥ ከፍተኛውን ኃላፊነት ይዘው የነበሩ እነዚህ እጨጌዎች ናቸው። በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያኒቱ ንብረት የሚቆጣጠርና በበላይነት የሚመራ እጨጌው ነው። ይህ አሠራር ግብጻውያኑን ጳጳሳት አያስደስታቸውም ነበር። የማይደሰቱበትም ምክንያት ሥልጣናቸው በእጨጌው እንደተወሰደባቸው ይገምቱ ስለነበር ነው።[1]

ለግንዛቤ እንዲረዳን ከመሥራቹ ከአቡነ ተክለሃይማኖት ጀምሮ እስከ አቡነ ባስልዮስ ድረስ ያሉትን እጨጌዎች እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን። የእጨጌነቱን ሹመት የጀመሩበትንና የለቀቁበትን ዘመን የተወሰኑት ተቀምጢዋል። በሠንጠረዡ ውስጥ ሁለት ዓይነት ምልክት ይታያሉ። መስቀላዊው ምልክት የእጨጌነቱን መንበር በሞት የለቀቁ ሲሆኑ፤ ኮከባዊው ምልክት ደግሞ በሽረት የለቀቁትን የሚያመለክት ነው። ምክንያቱም ነገሥታቱ ይህን የእጨጌነቱን ሹመት በሹም ሽር ይመለከቱት ነበር። በዚህ መሠረት አንዱን እጨጌ እስከ 4 ጊዜ ሾመውትና ሽረውት ይታያል። ነገር ግን በዚህ ዝርዝር ላይ ተራ ቁጥሩ የተጻፈው ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠውን ሹመት በመከተል ብቻ ነው።

1. የጣልያን ፋሽስት መንግሥት ኢትዮጵያን ሲወር የመጨረሻው ግብጻዊ የኢትዮጵያ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ የእጨጌነቱን ሥልጣን ከኢትዮጵያውያን እጅ ወስዶ ያስረክባቸው ዘንድ ከወራሪው ጠላት ተወካይ ጋር ይደራደሩ ነበር። ይህ የማይፈጸምላቸው መሆኑን ሲያውቁ ሮም እዚያም ስላልተሳካላቸው ወደ ግብፅ ገብተው ቀርተዋል። በዚሁ መጽሐፍ ገፅ 19-20 ተመልከት።



www.ethiopianorthodox.org

| ተ.ቁ | የእጨጌዎች ስም በተራ ቁጥር | እጨጌነት የጀመሩበት ወርና ዘመን | እጨጌነቱን የለቀቁበት ወር ዘመን | በሹመት የቆዩበት ዓ.ም. ወር | በዘመናቸው የነበሩ ነገሥታት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቡነ ተክለሃይማኖት | ሐምሌ 1260 | ነሐሴ 24 1299 | | ይኩኖ አምላክ |
| 2 | እጨጌ ኤልሳዕ | 1299 ዓ.ም. | ጥቅ. 12 1300 | | ይኩኖ አምላክ |
| 3 | እጨጌ ፊሊጶስ | | | | ዓምደጽዮን |
| 4 | እጨጌ ሕዝቅያስ | | | | ሰይፈ አርዕድ |
| 5 | እጨጌ ቴዎድሮስ | | | | |
| 6 | እጨጌ ዮሐንስ | | | | |
| 7 | እጨጌ ዮሐንስ ከማ | | | | |
| 8 | እጨጌ እንድርያስ | | | | |
| 9 | እጨጌ መርሐ ክርስቶስ | ነሐሴ 24 1455 | ጥር 24 1489 | ከ3 ወር 33ዓመት✞ | |
| 10 | እጨጌ ጴጥሮስ | | | | |
| 11 | እጨጌ እንባቆም /ተሽረው ሲኖሩ ሚያ. 21 1553 ሞቱ/ | | | * | |
| 12 | እጨጌ ያዕቆብ | | | | |
| 13 | እጨጌ ማትያስ | | | | ሚናስ |
| 14 | እጨጌ ዮሐንስ | | | | ሠርፀ ድንግል |
| 15 | እጨጌ ዮሐንስ | | | መጋ 27 1551 ✞ | ሠርፀ ድንግል |
| 16 | እጨጌ በትረ ወንጌል | | | | ሠርፀ ድንግል |
| 17 | እጨጌ አብርሃም | | | | በሱስንዮስ |
| 18 | እጨጌ ዘወንጌል ዘደብረ ዕጌ | | | | በሱስንዮስ |
| 19 | እጨጌ ዘሚካኤል | | | | ዐፄ ፋሲል |
| 20 | እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ዘሚልማ | | | | ዐፄ ፋሲል |
| 21 | እጨጌ ዘክርስቶስ ዘሸሚ | | | | ዐፄ ፋሲል |
| 22 | እጨጌ የማነ ብርሃን ዘትግራይ | | | | ዐፄ ፋሲል |
| 23 | እጨጌ ዘክርስቶስ ዘጸንከላ | | 1660* | | ዐፄ ዮሐንስ |
| 24 | እጨጌ ሕርያቆስ ዘማህደረ | ሚያ. 24 1661 | 1665* | 4 ዓመት | ዐፄ ዮሐንስ |



| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | እጨጌ ዘክርስቶስ 2ኛ ጊዜ | 1765 | | | |
| | እጨጌ ሕርያቆስ 2ኛ ጊዜ | ጥር 2 1669 | 1670* | 1 ዓመት | |
| 25 | እጨጌ ቃለ አዋዲ | 1670 | 1675 | 5 ዓመት | ኢያሱ አድያም |
| | እጨጌ ሕርያቆስ 3ኛ ጊዜ | 1676 | | | ኢያሱ አድያም |
| 26 | እጨጌ ፀጋ ክርስቶስ ዘጋሽና | | | | ኢያሱ አድያም |
| 27 | እጨጌ ዮሐንስ ዘአንጋር | | ነሐሴ 1682* | | |
| 28 | እጨጌ ሰፋኔ ክርስቶስ | ኅዳር 3 1683 | ታህ. 1683 | 1 ዓመት ከ1 ወር | |
| | እጨጌ ዮሐንስ 2ኛ ጊዜ | ታህ. 22 1683 | ታህ. 5 1686* | 3 ዓመት | |
| | እጨጌ ፀጋ ክርስቶስ 2ኛ ጊዜ | ታህ. 1686 | ጥቅ. 1689* | 2 ዓመት ከ10 ወር | |
| 29 | እጨጌ ዘሚካኤል | ጥቅ. 5 1689 | | | |
| 30 | እጨጌ አግናጥዮስ | ጥር 1691 | መጋ. 10 1695* | 4 ዓመት ከ2 ወር | |
| 31 | እጨጌ ወልደ ሐዋርያት | ሚያ. 3 1695 | | | |
| 32 | እጨጌ ተወልደመድኅን | | | | |
| 33 | እጨጌ መተከ | | መጋ. 28 1698✞ | | |
| | እጨጌ ዮሐንስ 3ኛ ጊዜ | ሐም. 7 1699 | ሐምሌ 29 1700* | 1 ዓመት | |
| 34 | እጨጌ ዘሚካኤል | | | | ዮስጦስ/ ዘሚካኤል |
| 35 | እጨጌ ዘወል ማርያም ዘሞጊና | | ታህ. 1701 | | ዳዊት |
| 36 | እጨጌ ተክለ ሃይማኖት ዘትግራይ | መጋ. 27 1702 | ነሐሴ 22 1703* | 1 ዓመት ከ5 ወር | ዳዊት |
| | እጨጌ ዘሚካኤል 2ኛ ጊዜ | ጥቅ. 27 1704 | ሚያ. 6 1708* | 4 ዓመት ከ5 ወር | |
| | እጨጌ ዘሚካኤል 3ኛ ጊዜ በሽረት እንዳሉ ታህ. 2 1718 ሞቱ | ነሐሴ 13 1708 | ሐምሌ 11 1711* | 3 ዓመት | |
| | እጨጌ ተክለሃይማኖት 2ኛ ጊዜ | 1713 | መጋ. 27 1716* | 3 ዓመት | |



www.ethiopianorthodox.org

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | እጨጌ ዮሐንስ 4ኛ ጊዜ | ሚያ. 27 1716 | ሚያ. 22 1717✣ | 1 ዓመት | |
| | እጨጌ ዘወልደ ማርያም 2ኛ ጊዜ | ሰኔ 28 1717 | ጥቅ. 5 1721* | 3 ዓመት ከ3 ወር | |
| | እጨጌ ተክለሃይማኖት 3ኛ ጊዜ በሽረት እያሉ ግንቦት 18 1747 ሞቱ | ጥቅ. 22 1721 | | | |
| 37 | እጨጌ አቡልዲስ ዘማህደረ ማር. | | | | |
| 38 | እጨጌ ኤዎስጣቴዎስ ዘሰከይ | 1737 | ግን. 23 1748* | 11 ዓመት | |
| 39 | እጨጌ ሄኖክ ዘቤተልሔም የሞቱት ታህሳስ 24 1774 ነው | ሰኔ 1 1748 | * | | |
| 40 | እጨጌ ኢሳይያስ ዘአዘዞ | | | | |
| 41 | እጨጌ ተስፋ ጊዮርጊስ ዘጎሐጽዮን | 1774 | | | ሕዝቅያስ |
| 42 | እጨጌ ወልደ ኢየሱስ ዘጉንደር | | ግን. 10 1790* | | ሕዝቅያስ |
| 43 | እጨጌ ወልደ ዮና | ግን. 10 1790 | 1814✣ | 14 ዓመት | ኢዮአስ |
| 44 | እጨጌ አርከ ዮሐንስ ዘስጋ | 1814 | 1815* | 1 ዓመት | ጊጋር |
| 45 | እጨጌ ፊሊጶስ ዘተድባበ ማርያም | 1815 | | | ራስ ጉግሳ |
| 46 | እጨጌ ገብረ ሥላሴ ዘጉርፎ | | | | ራስ አሊ |
| 47 | እጨጌ ወልደ ማርያም ዘውቅሮ | | | | ራስ አሊ |
| 48 | እጨጌ ማኅፀንተ ሚካኤል ዘየረኛ | | | | |
| 49 | እጨጌ ገብረ ማርያም ዘጎንጅ | | | | |
| 50 | እጨጌ ገብረ ሥላሴ ዘቋልሃ | | | | |
| 51 | እጨጌ ወልደ ማርያም ዘዋልድባ | 1847 | ጥቅ. 19 1852✣ | 5 ዓመት | |



| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 52 | እጨጌ ወልደ ትንሣኤ ዘጋሸላ | | | | ቴዎድሮስ |
| 53 | እጨጌ ገብረ ኢየሱስ ዘርበጋ | | | | ተክለ ጊዮርጊስ |
| 54 | እጨጌ ቴዎፍሎስ ዘቀርነ አምባ | 1864 | | | አፄ ዮሐንስ |
| 55 | እጨጌ ገብረ ሥላሴ ዘሀማሴን | ኅዳ. 1 1882 | ጥቅ. 24 1895✣ | 13 ዓመት | ምኒልክ |
| 56 | እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ዘበጌምድር | 1895 | ሰኔ 9 1910✣ | 15 ዓመት | ምኒልክ |
| 57 | እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዘደራ | ኅዳ. 12 1916 | ጳጉ. 2 1925✣ | 10 ዓመት ከ10 ወር | ዘውዲቱ |
| 58 | እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዘሚዳ/ሸዋ/ | የካ. 14 1927 | | | ኃ/ሥላሴ |

**ማሳሰቢያ:** በሠንጠረዥ ላይ የሚታየው የዘመናት ክፍተት ወይም ዓመተ ምሕረት ያልተገኘላቸው ባዶውን የተተወው ወደፊት ትውልዱ ዘመኑን ሲያገኘው ይሞላዋል በሚል መንፈስ ነው:: ወደፊት ግን ይህ መጽሐፍ ድጋሚ የመታተም እድል ሲያገኝ መጠነኛ ጥናት ተወስዶና በዚህ ታሪክ ዙሪያ ጥልቅ ጥናት ያላቸውን አባቶች ተጠ ይቆ አጥጋቢ ነገር ሲገኝ የምሞላው መሆኑን ላሳስብ እወዳለሁ:: ከአንባብያንም ጥቆማን እፈልጋለሁ::

ለዚህኛው ክፍል የመጽሐፍ ምንጭ

- የኢ.ቤ. የመጀመሪያው ፓትርያርክ
- ዋዜማ ጎሩይ ወልደሥላሴ

፠ ፠ ፠



www.ethiopianorthodox.org

# ዓቃቤ ሰዓት

ዓቃቤ ሰዓት የሚለው ሥልጣን ስያሜ በቤተ ክርስቲያን ከሚታወቁት የቀኖናና፣ የሃይማኖት የአስተዳደር፣ ሥልጣኖች ውስጥ ያለ አይደለም። ሥልጣኑ ሙሉ በሙሉ በቤተ መንግሥት የሚገኝ የመንግሥት ሥልጣን እርከን ሲሆን፤ ተጠሪነቱ ቀጥታ ለንጉሠ ነገሥቱ ነው። ይህ ሥልጣን ከመቼ ጀምሮ ተግባራዊ እንደሆነ ባይታወቅም የላስታ ሥርወ መንግሥትን ጨምሮ ረዥም ታሪክ ያለው ነው። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያስረዱን በሀገራችን የመጀመሪያውና ትልቁ የቤተ መንግሥት ሥልጣን ነው። ቤተ ክርስቲያንን ወክለው በቤተ መንግሥት የነበሩ እነዚህ ዓቃቤ ሰአቶች ናቸው።

በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አፄ ይኩኖ አምላክ ይህ ሥልጣን ለሐይቅ እስጢፋኖስ ሰጡት። በገዳሙ መሥራች በአቡነ ኢየሱስ ሞዓ የጸሎት እርዳታ ወደ ንግሥና የወጣው አፄ ይኩኖ አምላክ አንዳንድ ውለታዎችን ፈፅሞ የዓቃቤ ሰዓት ሹመት ሰጥቷቸዋል። አቡነ ኢየሱስ ሞዓ ግን ብሕትውናውን ስለመረጡ በዚህ ሥልጣን ይሠሩ የነበሩት ከእርሳቸው በኋላ በሐይቅ የተሾሙ አበምኔቶች ነበሩ።

የዚህ ሹመት ተግባር ንጉሡንና ሕዝቡን ማገናኘት ነበር። ማንም ሰው ጉዳዩን ወደ ንጉሡ የሚያቀርበው በአቃቤ ሰዓቱ በኩል ሲሆን፤ መልሱንም የሚያገኘው በዚሁ ሰው አማካኝነት ነበር። ሹመቱ ቁልፍ ቦታ በመሆኑ ይህን ሹመት የሚይዘው ሰው ምን ያህል ኃላፊነት እንደነበረበት ግልፅ ነው። የመነኮሳቱ ለዚህ ሥልጣን መብቃት ምንጩ የንጉሠ ነገሥቱ ፍላጐት ብቻ ሳይሆን የሰዎችም ችሎታ ጭምር ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ከዚያ በኋላ የነገሡ ነገሥታት ሥልጣኑን ለሌላ በሰጡት ነበር።

የዓቃቤ ሰዓትነት ሹመት ክብር ለእጨጌው ከሚሰጠው ክብር ምንም ያህል አይለይም ይህም የካባ ሥርዓቱን አድርሰው ያለብሱታል፤ ፊቱን በሻሽ ይሸፍኑታል፤ በዙፋን ወንበር ላይ ያስቀምጡታል፤ ከእግሩ በታች ምንጣፍ ያነጥፋሉ፤ መኳንንቱ ከበር ውጭ ድረስ ይሸኙታል፤ በመብራት በንጉሡ በቅሎ ሆኖ ወደ ቤቱ ይሔዳል የእጨጌነቱም ክብር ከዚህ ብዙም ያልራቀ ነው።



የዓቃቤ ሰዓትነት ሥራ አንድ አበምኔት ከሚፈፅመው በላይ ሲሆን፤ በኋላ ግን ሹመቱ የሚሰጠው በመነኮሳቱ ለተመረጠ ሰው ሳይሆን፤ ንጉሡ ሥራውን ይፈፅመዋል ብሎ ላመነው ሰው መሆን ጀመረ። የዚህን ጊዜ ሹመቱ ከቤተ ክርስቲያን እየቀረ መጣ። ነገር ግን ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ በገዳሙ የትምህርትና የህብት መድከም የሥልጣኑ አስፈላጊነት መቀዝቀዝ ከቤተ መንግሥት ሥልጣን እርከኖች እንዲነሳ አድርጐታል[1]

በሐይቅ ግን ከግራኝ ወረራ በኋላ በጐንደር ዘመን ሳይቀር ዓቃቤ ሰዓቱ ለመንግሥት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበረው። ለዚህም አቡነ ብስጣውሮስ አንዱ ተጠቃሽ ናቸው። እንግዲህ ከሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ከአቡነ ኢየሱስ ሞዓ በኋላ ያሉ አበምኔቶች ደርበው የያዙት ይህን የዓቃቤ ሰዓት ተሿሚዎች ስም በEMML 703 ቁጥር ተሰጥቶት ያገኘሁትን[2] ከዚህ በታች አስፍሬዋለሁ።

1. ከመቼ ጀምሮ እንደቀረ በትክክል አይታወቅም ነገር ግን እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ሥልጣኑ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ይታወቅ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ።
2. መረጃው ስም ብቻ አስቀምጧል፤ ሆኖም እነማን በማን ዘመን እንደነበሩ አይጠቁምም። ነገር ግን የርዕሱ ስያሜ የተሟላ እንዲሆን ከላይ የገለፅኩት ማብራሪያ ለግንዛቤ እንዲረዳን እና ወደፊት በሐይቅ እስጢፋኖስ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶች ይህ ፍንጭ ለመስጠት የተሠነዘረ ነው። በመካከለኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታሪክ የዳበረ እውቀት ያላቸው ሊቃውንቶች አቃቤ ሰዓቶቹ በእነማን ዘመነ መንግሥት እንደነበሩ ይጽፋሉ የሚል ተስፋ አለኝ።



www.ethiopianorthodox.org

1. ተክለ ኢየሱስ ሞአ
2. ክርስቶስ ተስፋነ
3. ዘኢየሱስ
4. ክርስቶስ ሞአ
5. ዮሐንስ
6. ቀውስጠስ
7. ገብረ ኢየሱስ
8. ታዴዎስ
9. ሠረቀ ብርሃን
10. ኤፍሬም
11. ብንያም
12. በኪሞስ
13. ገብረ ኢየሱስ
14. ዮሐንስ
15. ዓምደ ጽዮን
16. ዮሐንስ
17. ዓምደ ጽዮን
18. ገብረ ክርስቶስ
19. ገብረ አልፋ
20. አሮን
21. ዘብርሃን
22. ዘወንጌል
23. ዲዲሞስ
24. ዘታዎስ
25. ተስፋ ኢየሱስ
26. መርህናም
27. ዘኢየሱስ
28. ዘክርስቶስ
29. ብርሃነ መስቀል
30. ተስፋነ መስቀል
31. ቴዎድሮስ
32. ዮሴፍ
33. ንዋየ እግዚእ
34. ሚካኤል
35. ተስፋ ጊዮርጊስ
36. አምላክ ሞአ
37. አምላክ ብነ
38. ሕፃን መዋኢ
39. ገብርኤል
40. በትረ እስጢፋኖስ
41. ጳውሎስ
42. ዘጊዮርጊስ
43. አጽብአ ክርስቶስ
44. ቃለ አብ
45. መበይነ ክርስቶስ
46. ሐዋርያ ክርስቶስ
47. ሳእከ ማርያም
48. ማኅተመ ክርስቶስ
49. ኢዩኤል
50. ወልደ ሐዋርያት
51. ኢዮስያስ
52. ወልደ ገብርኤል
53. ማዕቀበ እግዚእ
54. ወልደ ብርሃን
55. ጳውሎስ
56. ወልደ ኢየሱስ
57. ወልደ መድኅን
58. ሰአልናከ መሐሪ
59. ሰአልናከ ፈጣሪ

ᯤ ᯤ ᯤ



# የግብፅ ቤተ ክርስቲያንና በመንበሯ ላይ የተቀመጡ ፓትርያርኮች

የኮኘታውያን ነገድ የወረደው /የመነጨው/ ከግብፅ ፈር አናውያን ዘር ነው:: ኮኘት የሚለው ቃልም «ግብጻውያን» ማለት ነው:: በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሳው ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመችው በወንጌላዊው ማርቆስ ነው ይላል:: ቅዱስ ማርቆስ ከአይሁድ ወገን እግዚአብሔርን ከሚፈሩና ሀብታም ከነበሩ ከማርያምና ከአርስጦብሎስ ሰሜን አፍሪካ በጥንታዊቷ ፔንዳ ፖሊስ በዛሬይቱ ሊቢያ ውስጥ በነበረች ቀሬና በምትባለው ከተማ ተወለደ:: በዚሁ ሀገር ወላጆቹ ሲኖሩ ሽፍቶች ተደጋጋሚ ዘረፋ ስላደረሱባቸው ወደ ኢየሩሳሌም ተሰደዱ:: ኢየሩሳሌም እያሉ ልጃቸው ማርቆስ ከፍ ያለ ትምህርት እንዲቀስም አድርገዋል:: እርሱም በዘመኑ በእብራይስጥና በአረማይክ ቋንቋ ይሰጡ ከነበሩ ከፍተኛ ትምህርቶች ገብይቷል:: የግሪክና የላቲን ቋንቋዎችንም በሚገባ አጥንቷል:: በጻፈው ወንጌል ውስጥ ይህ በጉልህ ተንፀባርቋል::

የክርስትና ትምህርት የተማረው ከአጐቱ ከበርናባስ ነበር:: ቆላስ. 4÷10:: የቅዱስ ማርቆስ አባት አርስጦብሎስና በርናባስ በእናት የሚገናኙ ወንድማማቾች ናቸው:: የእነርሱን እህት ደግሞ ቅዱስ ጴጥሮስ ስላገባት ቅዱስ ማርቆስ አክስቱን ለመጠየቅ ሲሔድ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ተዋወቀ:: ከዚያ ከ72ቱ አርድዕት አንዱ ሆነ:: ከጌታችን እርገት በኋላ በ60 ዓ.ም. ወደ ሚያውቀውና ወደአደገበት አካባቢ ወደ ሰሜን አፍሪካ መጣ:: በአባይ ዴልታ አድርጐ በዘመኑ የንግድ፣ የባሕል፣ የፖለቲካ ማዕከል ወደ ነበረችው እስክንድርያ ገባ:: በወንጌል ትምህርቱና በገቢረ ተአምራቱ በግብፅ የነበሩትን አብያተ ጣኦታት አፈራረሰ:: በዚያም የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያንን መሠረተ:: በመጨረሻም በ68 ዓ.ም. ሚያዝያ 30 ቀን በሰማዕትነት አረፈ::

በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቬኑስ ነጋዴዎች አፅሙን ሠርቀው ወስደውት ነበር:: በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ መሠረት የካቶሊክ ሊቀ ጳጳስ ጳውሎስ 6ኛ ለእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ለቄርሎስ 6ኛ እንዲሰጥ አደረገ:: ወንጌላዊው ቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

ማርቆስ በሰማዕትነት ያረፈበትን 1ሺ900 ዓመት በዓል የግብፁ
መሪ ናስር፣ የኢትዮጵያው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኦሬንቲያል፣
የግሪክ፣ የካቶሊክ፣ የፕሮቴስታንት የሃይማኖት መሪዎችና ተወ
ካዮች በተገኙበት በ1968 ዓ.ም. በድምቀት ሲከበር የቅዱስ ማር
ቆስ አፅም ወደ ግብፅ ተመልሶ ካይሮ ውስጥ በስሙ በተሠራው
20ሺ ምዕመናን ሊያስተናግድ በሚችለው ታላቁ ካቴድራል
ውስጥ በክብር አርፏል::

በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የአንጾኪያ፣ የኢየሩሳ
ሌም፣ የሮምና የእስክንድርያ ከተሞች የክርስቲያኖች መዲና
ነበሩ:: አሁን ግን መንበሩ በካይሮ ይገኛል::[1] በዲዮቅልጢያኖስ
ዘመን 284 እ.ኤ.አ. የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ
ስደት ደርሶባት ነበር:: ይህን የስደት ዘመን የግብፅ ቤተ ክርስ
ቲያን ሰማዕታትን የምታስብበትና የዘመን መቁጠሪያዋ መጀ
መሪያ ያደረገችበት ዘመን ነው:: በፋርሶች 616 ዓ.ም በዐረቦች
ደግሞ 642 ዓ.ም. ከፍተኛ የሆነ ስደት አድርሰውባቸዋል::
የግብፅ - እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ለምንኩስና ሕይወት
ምንጭ ናት::

ከበረሀ ባሕታውያን መካከል የብሕትውና ጀማሪ የሆነው
ቅዱስ እንጦንስ ለብዙ ክርስቲያኖች እስክንድርያን እንዲጎበኙ
ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ ምክንያት ሆኗል:: የምንኩስና

1. ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩትን ጳጳሳት ለመቆጣጠር እንዲመቻቸው
ግብፅን የሚያስተዳድሩ ሡልጣኖች በእነሱ ተፅእኖ የሊቃነ ጳጳሳቱን መን
በር ከእስክንድርያ ወደ ካይሮ ያዛወሩት ከዚህ የተነሣ ነው:: ይህም የሆነው
በአባ ዘካርያስ የሊቀ ጵጵስና ዘመን ከ996 - 1023 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ነው::
እነዚህ አራቱ ጥንታውያን የክርስትና መዲና ውስጥ የተቋቋሙት መንበ
ሮች ዋናዎቹ ናቸው:: ከ4ቱ ውስጥ ደግሞ የእስክንድርያ መንበር በመላው
ዓለም ለሚኖሩ ክርስቲያኖች የትንሣኤ በዓል በየዓመቱ ሲከበር የሚያበስ
ረው በመንበረ ማርቆስ ላይ የሚቀመጠው ፓትርያርክ ነበር:: ለምሳሌ
በ297 ካርቴጅ ላይ በተደረገው ጉባኤ የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት 27 መሆና
ቸውን ያሳወቀው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ ነው::
ይህንን የገለጸበት አጋጣሚ በዚሁ ዓመት በተከበረው የትንሣኤ በዓል
ምክንያት በማድረግ የእንኳን አደረሳችሁ መልእክቱ ላይ ነበር:: ምክንያ
ቱም ሁልጊዜ የበዓላት መዋያ ቀኖች የሚያውጀው የአስክንድርያ ሊቀጳጳስ
እንዲሆን የሠለስቱ ምዕት ቀኖና ያዛል:: ከዚህ በተጨማሪ ዓለማቀፍ ሦስቱ
ሲኖዶሶች የኒቂያን፣ የቁስጥንጥንያ እና የኤፌሶን ጉባኤዎችን በሊቀ
መንበርነት የመሩት የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት ነበሩ::



ሥርዓትና ደንብ በማውጣት ግብፃዊው ቅዱስ ጳኩሚስ ዋናው
ነው:: ዛሬ በእስክንድርያ 13 ገዳማት ሲኖሩ፤ 600 ወንዶች 250
ሴት መነኮሳይያት አሉ:: እነዚህም መነኮሳት የተማሩ ናቸው::
አሁን ያለው የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቷ የተከፈተው
በ1893 /እ.ኤ.አ/ ሲሆን፤ በዚህም ትጋቷ ቤተ ክርስቲያኒቱ 7
የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች በራሷ ሀገር በግብፅ ሲኖራት፤
ሁለቱ ደግሞ በሰሜን አሜሪካ አንድ ደግሞ በአውስትራሊያ
አላት:: የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ለአዲሱ ትውልድ የሚ
ሆን የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃና የሙያ ትምህርት ቤቶችን
ከፍታለች:: መንፈሳዊ የኅትመት እንቅስቃሴ በስፋት በመጀመር
እና በዚህም ብዙውን ተከታዮቿን /አማኞቿን/ ብሩህ አዕምሮ
እንዲይዙ አንፃቸዋለች:: ዋና የቤተ ክርስቲያኗ መልእክት የሚ
ተላለፍበት «ኤልክራዚ» የተባለ መጽሔታቸው በሳምንት ሁለት
ጊዜ በዐረቢኛ፤ በወር አንድ ጊዜ ደግሞ በእንግሊዝኛ ይታተ
ማል:: ወጣቶችን በተመለከተ «ውታኒ» የሚል መጽሔት በዐረ
ብኛ ታሳትማለች::

ቤተ ክርስቲያኒቱንና በተለይ ደግሞ የብሕትውና ኑሮ
ወደ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ እንዲሸጋገር ያደረገው በብሕት
ውና ሕይወት የታወቀው ታላቁ የጸሎት ሰውና ተአምር አድ
ራጊ በመባል የሚታወቀው ከ1959 - 1971 ፓትርያርክ የነበረው
ቄርሎስ 6ኛ ነው:: ዛሬ በመካከለኛው ምሥራቅ ካሉት ጥንታ
ውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል 10 ሚሊዮን አማኞች ያሏ
ትና በቁጥርም የምትበልጠዋ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን
ናት::

ከስደት ዘመን በኋላ /በ1960 ዓ.ም/ ለመጀመሪያ ጊዜ
በካናዳ ቶሮንቶ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን መስርታለች:: በዩናይ
ትድ ስቴትስ 50 አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሲኖራት፤
በካናዳ 10፤ በአውስትራሊያ 16፤ በምዕራብ አውሮፓ 23 አቋ
ቁማለች:: የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ተልዕኮዋን
ለመወጣት በአፍሪካ ውስጥ ብዙ ሊቢያውያን፤ ሱዳናውያንን
ክርስቲያኖች አድርጋለች:: በተጨማሪ ኬንያ፣ ዛምቢያ፣ ዚምባ
ቡዌ፣ ናሚቢያ እና ደቡብ አፍሪካ በእነዚህ አገሮች የወንጌል
ተልዕኮዋን ተወጥታለች:: የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን እስከ
አሁን ድረስ ሥርዓተ ቅዳሴዋን፣ መዝሙሯን፣ በዐረብኛ ቋንቋ



www.ethiopianorthodox.org

ትገለገላለች። የሥርዓተ ቅዳሴ መጻሕፍቶቿ የምትገለገልባቸው የቅዱስ ጎርጎርዮስ፣ ቅዱስ ቄርሎስ፣ የቅዱስ ባስልዮስ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ያሉት የቤተ ክርስቲያኗ መሪ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ 3ኛ ሲሆኑ 117ኛ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ናቸው።

የግብፅ-እስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክ አሁን እስካሉት ድረስ 117 ፓትርያርኮችን በመንበሯ ላይ የሰየመች ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ ኢትዮጵያን ያዩ (የጐበኙ) ፓትርያርኮች 5 ብቻ ናቸው። ዝርዝር ታሪኩ በክፍል ሁለት ወርቃማ ዘመናት መጽሐፍ ተገልጿል። በዚህ መሠረት ከዚህ በታች በመንበረ ማርቆስ የተቀመጡትን ፓትርያርኮች እንደየዘመን ሢመታቸው እንደ ሚከተለው ተቀምጧል። ዓመተ ምህረቶቹ በጠቅላላው እ.ኤ.አ መሆኑን አስቀድሜ አሳስባለሁ። ያረፉበትን ቀን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስንክሳር ባሠፈረው ቀን የተወሰደ ነው።

| የፓትርያርኮች ስም | ፓትርያርክነቱን የጀመሩበት ዓ.ም. | በሹመት የቆዩበት ዘመን | | ያረፉበት ወር እና ቀን |
|---|---|---|---|---|
| | | ዓመት | ወር | |
| 1. በሮማውያን ጊዜያት ፓጋን ገዥነት ስር የነበሩ | | | | |
| ማርቆስ | 61 | 7 | 8 | ሚያዝያ 30 |
| አንያኖስ | 63 | 20 | - | ኅዳር 20 |
| ሚልዮስ | 83 | 11 | 9 | መስከረም 1 |
| ክርዳኑ | 95 | 10 | 9 | ሰኔ 21 |
| አምብርዮስ | 106 | 12 | 1 | ነሐሴ 3 |
| ዮስጦስ | 118 | 10 | 10 | ሰኔ 12 |
| አውማንዮስ | 129 | 12 | 3 | ጥቅምት 9 |
| መርክያኖስ | 141 | 10 | 2 | ጥር 6 |
| ክላድያኖስ | 152 | 14 | 6 | ሐምሌ 9 |
| አክርጳዮስ | 166 | 11 | 6 | የካቲት 5 |
| ዮልዮስ | 178 | 10 | - | መጋቢት 8 |
| ድሜጥሮስ | 188 | 42 | 7 | ጥቅምት 12 |
| ያሮክላ /ሔራክልስ/ | 230 | 16 | 1 | ታህሳስ 8 |
| ዲዮናስዮስ | 246 | 17 | 2 | መጋቢት 17 |
| መክሲሞስ | 264 | 17 | 5 | ሚያዝያ 14 |
| ቴዎናስ | 282 | 19 | 1 | ጥር 2 |
| ጴጥሮስ /ተፍፃሜተ፤ ሰማዕት/ | 302 | 9 | 10 | ኅዳር 29 |
| አክላስ | 311 | - | 6 | ሰኔ 19 |



## ማስታወሻ

በእነዚህ ፓትርያርኮች ዘመን የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የስደት ዘመናትን አሳልፋለች። ከቅዱስ ማርቆስ እረፍት በፊትና በኋላ የሮም ቄሣሮች ግብፅን ጨምሮ ያስተዳድሩ ነበር። የአሕዛብ የአይሁድ የሮም ቄሣሮች ግብፅን ጨምሮ ... ሊቃውንት መናኸሪያና የእውቀት መፍለቂያ እንዲሁም ለሮማ ግዛት በትልቅነቷ ከሮም ቀጥላ ሁለተኛ ከተማ እስክንድርያ ነበረች። እንግዲህ የሮም ቄሣሮች ግዛት እንደመሆኗ መጠን ነገሥታቶች በክርስቲያኖች ላይ ስደት በየጊዜው አስነስተውባቸው ነበር። ሊጠቀሱ የሚገባቸው የስደት ዘመናት፡- በቄሣር ሤስቲሚያኖስ ከ193 - 211 ዓ.ም.፤ በዳክዮስ 249 - 251 ዓ.ም. እና በዲዮቅልጢያኖስ ዘመነ መንግሥት የተነሳው ስደት 284 - 305 ዋናዎቹ ናቸው። በእነዚህ ፓትርያርኮች ዘመን ክርስቲያኖች የተሰደዱበት፣ አሠቃቂ የሰማዕትነት ጽዋ የተጐነጩበት ዘመን ሲሆን፤ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ይህን ዘመን የሰማዕታት ዘመን በማለት ሁልጊዜ ታስበዋለች፤ መታሰቢያውም እንዳይረሳ በማለት የቀን መቁጠሪያዋን ከዚህ ትጀምራለች።

**ማሳሰቢያ:** ፓትርያርክነት የጀመሩበት ዓ.ም.፤ በሹመት የቆዩበት ዘመን፣ ዓመት፣ ወር ያረፉበት ወር እና ቀን የሚለው የሠንጠረዥ ርዕስ ከዚህ በታች በተቀመጡት ሠንጠረዥ ባዶው ተቀምጧል አንባብያን በላይኛው ሰንጠረዥ መሠረት እንድትመለከቱት አሳስባለሁ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2. በክርስቲያን ዘመን በቢዛንቲን ጊዜያት የነበሩ | | | | |
| እለስክንድሮስ | 312 | 15 | 9 | ሚያዝያ 24 |
| አትናቴዎስ | 328 | 45 | | ግንቦት 7 |
| ጴጥሮስ 2ኛ | 373 | 5 | 9 | የካቲት 20 |
| ጢሞቴዎስ | 379 | 6 | 4 | ነሐሴ 26 |
| ቴዎፍሎስ | 385 | 27 | 2 | ጥቅምት 18 |
| ቄርሎስ | 412 | 31 | 8 | ሐምሌ 13 |
| ዲዮስቆሮስ | 444 | 10 | 1 | መስከረም 1 |

## ማስታወሻ

ቢዛንቲን የሚባለው በቁስጥንጥንያ የአንድ መንደር ስም ነው። ነገሥታት የሚወለዱበት መንደር ስለሆነ መላው የታናሽ እስያ መንግሥት ቪዛንታይን እየተባለ ይጠራ ነበር። በዚህ ዘመን የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ከላይ የጠቀስኳቸውን ሊቃነ ጳጳሳት በመንበሯ ላይ ሰይማለች። ከእነዚህ ውስጥ ቅዱስ እለእስክንድሮስ፤ ቅዱስ አትናቴዎስ፤ ቅዱስ ጢሞቴዎስና ቅዱስ ቄርሎስን ላቲኖችና ግሪኮች በእምነታቸው ጠንካሮችና ኃይለኞች ናቸው ይሏቸዋል።



www.ethiopianorthodox.org

ከእነዚህ 4ቱ ሊቃነ ጳጳሳት መካከል ለብዙ ዘመናት ከመንበሩ ሲሰደድ፣ ሲመለስ የኖረው በተለይ ተረፈ አርዮሳውያን ያንገላቱት ቅዱስ አትናቴዎስን ነው:: ይህ አባት ለ45 ዓመታት በፓትርያርክነት የቆየ ሲሆን 15ቱን ዓመታት ያሳለፈው በግዞትና በስደት ነው:: ትምህርቱና ተጋድሎው ቀዳማውያን አበው ሐዋርያትን ስለሚመስል «አትናቴዎስ ሐዋርያዊ» ይባላል:: ለእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን 20ኛ ፓትርያርክ ነው:: ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አባ ሰላማን ሹሞ የላከልንም እሱ ነው:: ከላይ የጠቀስኳቸው ከ4ቱ ሦስቱ ታላላቅ አባቶች ሦስቱን ዓለማቀፍ ጉባኤ በሊቀ መንበርነት መርተውታል:: ይህም:-

አርዮስ የተወገዘበትን የኒቂያ ጉባኤን ቅዱስ እለእስክንድሮስ በ325 ዓ.ም.፣ መቅዶንዮስና ትምህርቱ የወገዙበትን የቁስጥንጥንያ ጉባኤን ቅዱስ ጢሞቴዎስ በ381 ዓ.ም.፣ በመጨረሻም የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ንስጥሮስ የተወገዘበት የኤፌሶን ጉባኤ ቅዱስ ቄርሎስ በ431 ዓ.ም. ሊቀ መንበርነት የመሩት የእስክንድርያ ፓትርያርኮች ናቸው::

| 3. ከቤተ ክርስቲያን መለያየት በኋላ የነበሩ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጢሞቴዎስ 2ኛ | 455 | 21 | 10 | ነሐሴ 7 |
| ጴጥሮስ 3ኛ | 477 | 12 | 2 | ኅዳር 2 |
| አትናቴዎስ 2ኛ | 489 | 6 | 9 | መስከረም 20 |
| ዮሐንስ | 496 | 8 | 7 | ግንቦት 4 |
| ዮሐንስ 2ኛ | 505 | 11 | - | ግንቦት 12 |
| ዲዮስቆሮስ 2ኛ | 516 | 2 | 4 | ጥቅምት 17 |
| ጢሞቴዎስ 3ኛ | 518 | 17 | 3 | የካቲት 13 |
| ቴዎዶስዮስ | 536 | 31 | 4 | ሰኔ 28 |
| ጴጥሮስ 4ኛ | 567 | 2 | - | ሰኔ 25 |
| ድምያኖስ | 569 | 35 | 11 | ሰኔ 18 |
| አንስጣስዮስ | 321 | 11 | 6 | ታህሳስ 23 |
| አንድራኒቆስ | 332 | 6 | - | ጥር 8 |
| ብንያሚን | 339 | 39 | - | ጥር 8 |

## ማስታወሻ

ከኤፌሶን ጉባኤ በኋላ በ481 ዓ.ም. የሃይማኖት፣ የሥልጣን፣ የዘር ችግርን ያስተናገደው የኬልቄዶን ጉባኤ ሲሆን፣ አንዲቷ ቤተ ክርስቲያን ይህን ጉባኤ አትቀበለውም:: በሠንጠረዥ ውስጥ ከቤተ ክርስቲያን መለያየት በኋላ ብለን የጠቀስነው ይህን ነበር:: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳን እንደ ሦስቱ ዓለማቀፍ ጉባኤዎች ይህኛው ጉባኤ አንድ መሠረታዊ ነገር ያልተገኘበት ሲሆን፣ እነ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ከቤተ ክርስቲያን ክብር ይልቅ ለቤተ መንግሥት ሰዎች ክብር በቆሙ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ጥርሱ



የረገፈበት፣ የተዋሕዶ ትምህርት ጠበቆች እምነቱ ባለበት እንዲቀጥል የተጋደሉ የእስክንድርያ አባቶች የተነሡበት ዘመን ነው:: እንግዲህ ከቤተ ክርስቲያን መለያየት በኋላ ከተነሡ አባቶች መካከል ዋነኛው 25ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ነው::

| 4. በእስላሞች ከሊፎች ገዥነት ስር የነበሩ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ያጋቱ /አጋቶን/ | 662 | 18 | 9 | ኅዳር 16 |
| ዮሐንስ 3ኛ | 680 | 9 | - | ታህሳስ 10 |
| ይስሐቅ | 690 | 2 | 10 | ኅዳር 9 |
| ስምኦን | 692 | 7 | 7 | ሐምሌ 24 |
| እለስክንድሮስ 2ኛ | 704 | 24 | 9 | የካቲት 2 |
| ቆዝሞስ | 729 | 1 | 3 | ሰኔ 30 |
| ቴዎድሮስ | 730 | 11 | 7 | የካቲት 7 |
| ካኤል /ሚካኤል/ | 743 | 23 | 6 | መጋቢት 6 |
| ሚናስ | 767 | 8 | 10 | ጥር 30 |
| ዮሐንስ 4ኛ | 777 | 22 | - | ጥር 16 |
| ማርቆስ 2ኛ | 799 | 20 | 2 | ግንቦት 22 |
| ያዕቆብ | 819 | 10 | 9 | የካቲት 14 |
| ስምኦን 2ኛ | 830 | - | 7 | ጥቅምት 3 |
| ዮሳብ /ዮሴፍ/ | 831 | 17 | 11 | ጥቅምት 23 |
| ካኤል 2ኛ /ሚካኤል/ | 849 | 1 | 5 | ግንቦት 22 |
| ቆዝሞስ 2ኛ | 851 | 7 | 4 | ኅዳር 21 |

## ማስታወሻ:

በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዐረቦች ግብፅን ወርረው ነበር:: ይህቺን የመሰለች በአፍሪካ ውስጥ የክርስቲያኖች መዲና የነበረችው የግብፅን ቤተ ክርስቲያን እንዳልነበረች በማድረግ ብዙ ጥፋቶችን አድርሰውባቸዋል:: በሠንጠረዥ ውስጥ እንዳየነው በእስላም ከሊፎች ገዥነት ስር የነበሩ የእስክንድርያ ፓትርያርኮች 16 ናቸው:: እነዚህም ያለ ፈተና በቀላሉ በመንበራቸው ላይ የተቀመጡ አይደሉም:: የገዥዎች የግብር ጫና ያንገላታቸው ነበር:: መታሠር መሰደድም እጣቸው የሆነበት ዘመን ነበር::

| 5. በቱሊኒደስ ገዥነት ስር የነበሩ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ስንትዮ | 859 | 21 | 3 | መጋቢት 14 |
| ሚካኤል | 880 | 27 | - | መጋቢት 20 |



www.ethiopianorthodox.org

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6. በአክሸዲስ ገዥነት ስር የነበሩ | | | | |
| ገብርኤል | 909 | 10 | 9 | መጋቢት 20 |
| ቆዝሞስ 2ኛ | 921 | 12 | - | መጋቢት 3 |
| መቃርስ /መቃርዮስ/ | 932 | 20 | - | ሰኔ 24 |
| ታውፋኒዎስ | 952 | 4 | 4 | መጋቢት 4 |
| ሚናስ 2ኛ | 956 | 17 | 11 | ታህሳስ 3 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 7. በቤተ ፋጡማ ገዥነት ስር የነበሩ | | | | |
| አብርሃም | 975 | 3 | 7 | ታህሳስ 6 |
| ፊላታዎስ | 979 | 24 | 7 | ኅዳር 12 |
| ዘካርያስ | 1004 | 27 | 11 | ኅዳር 13 |
| ስንትዮ 2ኛ | 1032 | 14 | 7 | ኅዳር 12 |
| ክርስቶዶሉ /ገብረ ክርስቶስ/ | 1046 | 31 | - | ታህሳስ 24 |
| ቄርሎስ 2ኛ /ጌርሉስ/ | 1078 | 14 | 2 | ሰኔ 12 |
| ሚካኤል 2ኛ | 1092 | .9 | 7 | ግንቦት 30 |
| መቃርዮስ 2ኛ /መቃርስ/ | 1102 | 26 | 1 | መስከረም 4 |
| ገብርኤል 2ኛ | 1131 | 14 | 2 | ሚያዝያ 10 |
| ሚካኤል 3ኛ | 1145 | - | 8 | ሚያዝያ 3 |
| ዮሐንስ 5ኛ | 1147 | 18 | 8 | ግንቦት 14 |
| ማርቆስ 3ኛ | 1166 | 22 | 6 | ጥር 6 |
| 8. በቤተ አዩቢዴስ ገዥነት ስር የነበሩ | | | | |
| ዮሐንስ 6ኛ | 1189 | 26 | 11 | ጥር 11 |
| ቄርሎስ 3ኛ | 1235 | 7 | 9 | መጋቢት 14 |
| አትናቴዎስ 3ኛ | 1250 | 11 | 2 | ታህሳስ 1 |

ማስታወሻ:

ከእነዚህ ፓትርያርኮች ዘመን ግብፅን ይገዙ የነበሩ የፋቲሚድ /የፋጡማ/ ዳይናስቲ ዘሮችና የሺአት እስልምና እምነት ተከታዮች ነበሩ:: እነዚህ የፋቲሚድ ዘሮች በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚሠሩ ክርስቲያኖችን ክርስቲያን ስለሆኑ ብቻ ከሥራቸው ያባርሯቸው ነበር:: የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳን በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው የእስራት ስቃይ፤ ሁልጊዜ ከእስላሞች በሚሰነዘረው ውንጀላ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ ከፍተኛ ምቀኝነትና ቅናት ከሰፈነባቸው የኮፕት መነኮሳትና ጳጳሳት ለገዥዎች በሚያቀርቡት የሀሰት ውንጀላ ጭምር ነበር: ለምሳሌ:- የማዕርግ እድገት የተከለከለ ኮሎቶስ የተባለ መነኩሴ በፓትርያርኩ በአቡነ ክርስቶዶሉስ /ገብረ ክርስቶስ/ ላይ 1046 - 1077 ዓ.ም. ባቀረበው የሀሰት ክስ ምክንያት ባለሥልጣኖቹ የክሱን ይዘት በሚገባ ሳያጣሩ ፓትርያርኩን አስረው የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብት የወሰዱበት ጊዜ ነበር:: የፋጡማ



ዳይናስቲ ዘሮች ምንም እንኳ በግብፅ ክርስቲያኖች ላይ ከባድ ስቃይ የማድረስ ፍላጐት ባይኖራቸውም፤ ነገር ግን ከፍተኛ ግብር፣ በመጠየቅ፤ ክርስቲያኖችን ከሥራ በማባረርና ከመዝረፍ አልተቆጠቡም::

ሌላው በቤተ ፋጡማ ገዥነት ስር የነበሩ ፓትርያርኮች የጐላ ችግራቸው አንድ ፓትርያርክ ሞቶ ሌላውን ለመተካት ከገዥዎች ፈቃድ ሲጠየቁ፤ ገዥዎች ደግሞ ገንዘብ ይጠይቁ ነበር:: ፓትርያርክ መቃርዮስ 2ኛ በ1128 ዓ.ም. ሲሞቱ አዲስ ፓትርያርክ ለመሾም የሲኖዶስ አባሎች ፈቃድ ሲጠይቁ በቅድሚያ 6ሺ ያህል ዲናር ክፈሉ ተብለው ነበር:: ክርስቲያኖች ግን ከታክስ፣ ከግብር የሚወሰድባቸው ብዙ ገንዘብ ሌላ ይህን ያህል ገንዘብ የለንም ብለው ተውት:: በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ነገር አመላላሽ ክርስቲያኖች ከምእመናን የሚሰበስቡትን ገንዘብ ለጠላቶቻችን ለፍራንኮች ይሰጣሉ ብለው ወሬ ተናገሩ:: ገዥዎችም ሳያጣሩ ቤተ ክርስቲያኒቱ ያላትን ሀብት ሙጥጥ አድርገው ወሰዱ:: ፓትርያርክ መርጦ የመሾም ዓላማቸው ተገትቶ ከቆየ በኋላ በ1131 ዓ.ም. ዳግማዊ ገብርኤል የተባሉ ፓትርያርክ በብዙ ደጅ ጥናት ገንዘብ ከፍለው ሾሙ::

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 9. በቤተ ባሕሪት ማምሉክስ ገዥነት ስር የነበሩ | | | | |
| ገብርኤል 3ኛ | 1268 | 2 | | ሚያዝያ 26 |
| ዮሐንስ 7ኛ: የፓትርያርክነቱ መንበር 2ኛ ጊዜ የያዙ ናቸው:: መጀመሪያ ከ1262-1268ዓ.ም. ቀጥሎም ከ1271- 1293 ዓ.ም. ፓትርያርክ ነበሩ:: | 1263 | 29 | | ሰኔ 4 |
| ታውዳስዮስ 2ኛ | 1294 | 5 | 6 | ጥር 6 |
| ዮሐንስ 8ኛ | 1300 | 20 | 3 | ሚያዝያ 2 |
| ዮሐንስ 9ኛ | 1320 | 6 | 6 | |
| ብንያሚን 2ኛ | 1327 | 11 | 8 | ጥር 11 |
| ጴጥሮስ 5ኛ | 1340 | 8 | 6 | ጥቅምት 4 |
| ማርቆስ 4ኛ | 1348 | 14 | 5 | የካቲት 6 |
| ዮሐንስ 10ኛ | 1363 | 6 | 2 | ሐምሌ 1 |
| ገብርኤል 4ኛ | 1370 | 8 | 4 | ግንቦት 2 |
| ማቴዎስ | 1378 | 30 | 5 | ጥር 5 |

ማስታወሻ:

በቱርክ ማምሉክ ገዥነት ስር የነበሩ የእስክንድርያ ፓትርያርኮች በሠንጠረዥ ውስጥ እንዳየነው 11 ናቸው:: በቱርክ ገዥነት ዘመን የመስቀል ጦርነት በመካከለኛው ምሥራቅ የተቀጣጠለበት ጊዜ ነው:: ይህ ዘመን የግብፅ ክርስቲያኖች መከራ እየጨመረ የሔደበት ነው:: ቱርኮች በዐረብ ተወላጆች ይገዛ የነበረውን የግብፅን መንግሥት ገልብጠው ይገዙ የነበሩት መምሉኮች ክርስቲያኖችን ማሰቃየት ጀመሩ:: እንዲያውም እናንተን መሰል



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኖች ናቸው በመስቀል ጦርነት ጉዳት የሚያደርሱብን በማለት፤ በእነሱ ገዥነት ስር የነበሩ በተለይ በፓትርያርክ ማርቆስ 4ኛ 1348 - 1363 ዓ.ም. እና በፓትርያርክ ዮሐንስ 10ኛ ከ1364 -1369 ዓ.ም. በተከታታይ በተሾሙት በእነዚህ ሊቃነ ጳጳሳት ዘመን በክርስቲያኖች ላይ ግድያ፣ እስራት የመሳሰሉት ስቃዮች አድርሰዋል። አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማትን አፈራርሰዋል።

በዚህ ጊዜ ነበር ከግብፅ ግዛት ውጭ የነበሩ 4 ሀገሮች ይህን ሕገ ወጥ ተግባራቸውን የሚተውበት የምልጃና የማስፈራራት ደብዳቤዎች የላኩት። እነዚህም ሀገሮች:- የቁስጥንጥንያ፣ የአርጉን፣ የኑብያና የኢትዮጵያ መንግሥታት ነበሩ። ከሦስቱ ሀገሮች ጥያቄ ከበድ የሚለው የኢትዮጵያው ንጉሥ የላከው መልእክት ነው። ምክንያቱም በተዋሕዶ እምነት መሰሎቹ በሆኑት ክርስቲያኖች ላይና በቤተ ክርስቲያናቸው ላይ የግብፅ ገዥዎች የሚያደርሱትን ግፍ በደል አሳዝኖታል። ነገር ግን ይህን ካላቆሙ የአባይን ወንዝ አቅጣጫ በመለወጥ የሚበቀል መሆኑን አስጠንቅቆ ልኮላቸዋል። ይህ ንጉሥ ዳዊት 1ኛ ሳይሆን አይቀርም።

| 10. በቱርካውያን ማምሉክ ገዥነት ስር የነበሩ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ገብርኤል 5ኛ | 1409 | 17 | 8 | ጥር 8 |
| ዮሐንስ 11ኛ | 1427 | 25 | - | ግንቦት 9 |
| ማቴዎስ 2ኛ | 1452 | 13 | - | መስከረም 13 |
| ገብርኤል 6ኛ | 1466 | 8 | 10 | ታህሳስ 19 |
| ሚካኤል 4ኛ | 1477 | 1 | - | የካቲት 16 |
| ዮሐንስ 12ኛ | 1480 | 3 | 4 | መስከረም 7 |

| 11. በቱርኮች ገዥነት ስር የነበሩ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዮሐንስ 13ኛ | 1484 | 40 | - | ጥቅምት 29 |
| ገብርኤል 7ኛ | 1525 | 43 | - | |
| ዮሐንስ 14ኛ | 1571 | 15 | 4 | ግንቦት 7 |
| ገብርኤል 8ኛ | 1587 | 16 | 10 | ግንቦት 9 |
| ማርቆስ 5ኛ | 1603 | 17 | - | ግንቦት 9 |
| ዮሐንስ 15ኛ | 1619 | 10 | - | |
| ማቴዎስ 3ኛ | 1631 | 14 | 7 | መስከረም 9 |
| ማርቆስ 6ኛ | 1646 | 10 | - | ሚያዝያ 7 |
| ማቴዎስ 4ኛ | 1660 | 14 | 8 | ነሐሴ 16 |
| ዮሐንስ 16ኛ | 1676 | 42 | 2 | ሰኔ 10 |
| ጴጥሮስ 6ኛ | 1718 | 7 | 7 | መጋቢት 26 |
| ዮሐንስ 17ኛ | 1721 | 18 | 3 | ሚያዝያ 23 |
| ማርቆስ 7ኛ | 1745 | 24 | - | ግንቦት 12 |
| ዮሐንስ 18ኛ | 1769 | 26 | 7 | ሰኔ 2 |
| ማርቆስ 8ኛ | 1796 | 13 | 3 | ታህሳስ 13 |



| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጴጥሮስ 7ኛ | 1809 | 4 | 3 | መጋቢት 28 |
| ቄርሎስ 4ኛ ሜጥሮጶሊስ ሆነው በ1853 ተሾሙ ፓትርያርክ ሆነው በ1854 ተሾሙ | 1853 | 7 | 9 | ጥር 23 |
| ጴጥሮስ 2ኛ | 1862 | 7 | 7 | ጥር 11 |
| ቄርሎስ 5ኛ | 1874 | 52 | 9 | ነሐሴ 1 |

## ማስታወሻ:

በቱርክ ገዥነት ስር የነበሩ የእስክንድርያ ፓትርያርኮች 19 ነበሩ። ያው በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ያለው መከራ የቀጠለበት ዘመን ቢሆንም፤ በአንድ ታላቅ ፓትርያርክ አማካኝነት ቤተ ክርስቲያኒቱ ያንሰራራችበት ዘመንም ነው። ይኸው አባት ፓትርያርክ ቄርሎስ 4ኛ ሲባል፤ 110ኛው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ነው። ያነበረበት ዘመን 1853 - 1862 ዓ.ም ሲሆን ለ7 ዓመታት በመንበረ ማርቆስ ላይ ቆይቷል። ዋነኛ ዓላማ አድርጉ የተነሳው ትምህርትን ማስፋፋት ስለነበር በግብፅ ካህናት ላይ ሰፍኖ የነበረውን የትምህርት ጉድለት በማሻሻል ተግተው እንዲማሩ አድርጓቸዋል።

ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ከፍቶ መንፈሳዊና ዓለማዊ እውቀት የነበራቸውን መምህራን በማስማራት መጻሕፍት በገፍ በማቅረብ:- የቅብጥ፣ የዐረብኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ እና የቱርክ ቋንቋዎችን የተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርቶችን እንዲማሩ ያደረገ አባት ነው። ለካህናት መማሪያና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ መንፈሳዊ ነክ መጻሕፍት በማዘጋጀት የሕትመት መሣሪያ ከአውስትራሊያ በማስመጣት አቋቁሟል። ይህ ማተሚያ ቤት ካይሮ ከነበረው ከመንግሥት ማተሚያ ቤት ቀጥሎ ሁለተኛው ነው። ፓትርያርክ ቄርሎስ 4ኛ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ንጉሡንና የቱርክን እስላም ለመሸምገል፤ በተጨማሪ የማርቆስን ካቴድራል ለማደስ ፈልገው ስለነበር እርዳታ ለመጠየቅ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል።[2] [ዝርዝር ታሪኩን በክፍል ሁለት መጽሐፈ ተገልጧል] በአጠቃላይ በቱርኮች ገዥዎች ስር ከነበሩት የግብፅ ፓትርያርኮች መካከል ጉላ ያለው የዚህ ፓትርያርክ ዘመን ስለሆነ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የለውጥ ዓመታት ነበር ማለት እንችላለን። አቡነ ቄርሎስ 4ኛ ከኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች

2. ይህ አመጣጣቸው ለሁለተኛ ጊዜ ነው። በራስ ዓሊ ዘመነ ምስፍና በ1843 ዓ.ም. በወርኃ ፀደይ ወደ ሀገራችን ቆሞስ በነበሩ ጊዜ መጥተዋል። በዚህ ዘመን የእንጦንስ ገዳም አበምኔት የነበሩ ሲሆን ቆሞስ ዳውድ ይባሉ ነበር። የመጡበት ምክንያት በፓትርያርክ ጴጥሮስ 7ኛ ተልከው ሲሆን በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን የመጡት ግብጻዊ ጳጳስ አቡነ ሰላማ እና የጎንደር ካህናት ስላልተግባቡ ይህን ችግር ለመፍታት ነበር የመጡት። ቆሞስ ዳውድ አንድ ዓመት ያህል በሀገራችን ቆይተው በሐምሌ ወር 1844 ዓ.ም. ወደ ካይሮ ተመልሰው ሄደዋል። ከፓትርያርክ ጴጥሮስ እረፍት በኋላ ቆሞስ ዳውድ ፓትርያርክ ቄርሎስ 4ኛ ተብለው ተሹመዋል። [እድገትና ነጻነት ገጽ 15]



www.ethiopianorthodox.org

ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት በመሻት ከአርመንና ከግሪክ ፓትርያርኮች ጋር ግንኙነት ፈጠረ:: ሆኖም የተጀመረው ግንኙነት በግብፅ መንግሥት ላይ እንደታለመ አመፅ በመቁጠር የግብፁ ገዥ ሰይድ ፓሻ አቡነ ቄርሎስን በእጅ አዙር በመርዝ አስገደለው::

| 12. ነፃነት ከታወጀ በኋላ ያሉ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዮሐንስ 19ኛ | 1928 | 14 | 6 | |
| መቃርዮስ 3ኛ | 1944 | 1 | 5 | |
| ዮሳብ /ዮሲፍ/ 2ኛ | 1946 | 14 | 6 | |
| ቄርሎስ 6ኛ | 1959 | - | - | |
| ሺኖዳ 3ኛ | 19 | - | - | |

## ማስታወሻ

የግብፅ - እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ነፃነት ካገኘች ጊዜ ጀምሮ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ በመንበሯ ላይ የተቀመጡ ፓትርያርኮች 5 ናቸው:: ይህ የነፃነት ዘመን ቤተ ክርስቲያኒቱ የማሻሻሉ ተግባር በምእመናን በተመረጡ ማዕርገ ክህነት በሌላቸው የሰበካ ጉባኤ አባላት ይካሔድ የጀመረበት ዘመን ነው:: ሆኖም የቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ እንደሚያስረዳን በአዲሱ የነፃነት ዘመን የተከሰተውን በበጐ ሀሳቢነት መንፈስ ቆርጠው በተነሱት ምሁራንና ወግ አጥባቂ ካህናት ጋር ግብግብ የገጠሙበት ዘመንም እንደሆነ እንረዳለን:: ከእነዚህ በነፃነት ዘመን ከተነሡት ፓትርያርኮች መካከል ለ53 ዓመታት በማርቆስ መንበር ላይ የተቀመጡት አቡነ ቄርሎስ 5ኛ ይባላሉ:: በእኚህ ፓትርያርክ ዘመን ምንም እንኳ የመንግሥቱ እምነት እስልምና ቢሆንም ለክርስቲያኖችም ነፃነት የተሰጣቸው በዚያው አመታት ነው::

ሌላው በዚህ የነፃነት ዘመን ከነበሩት ፓትርያርኮች መካከል አቡነ ዮሳብ 2ኛ የተባሉት ለመጀመሪያው የሀገራችን ሊቀ ጳጳስ አባ ባስልዮስ የሊቀ ጵጵስና ማዕርግ የሰጡ ሲሆኑ፣ ከእሳቸው ቀጥሎ የተሾሙት አቡነ ቄርሎስ 6ኛ ደግሞ የአቡነ ባስልዮስን የሊቀ ጵጵስና ማዕርግ ወደ ፓትርያርክነት ማዕርግ ከፍ ያደረጉ እሳቸው ሲሆኑ ይኸውም ኢትዮጵያዊ ቀርቶ የራሳቸው ፓትርያርክ ለመሾም የገዥዎችን ፈቃድ የሚጠይቁ የግብፅ ሲኖዶስ አባላት ያ ሁሉ ተፅእኖ ነፃነታቸውን ሲያገኙ ለእኛ ጨምሮ በዚህ መጽሐፍ በስፋት እንደተመለከትነው መንፈሳዊ ሥልጣኑን ለማጐናፀፍ አስችለውናል::

ለዚህኛው ክፍል የመጻሕፍት ምንጭ

- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ፓትርያርክ በመርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ 1956 ዓ.ም.
- የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሉሌ መልአኩ 1986 ዓ.ም.
- ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ በማኅበረ ቅዱሳን 1988 ዓ.ም.
- የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ በአባ ጎርጎርዮስ 1978 ዓ.ም.
- የዓለም ታሪክ ከበደ ሚካኤል 1948 ዓ.ም.
- ከጣኦት አምልኮ ወደ ክርስትና በተ.፯.መኩሪያ 1941 ዓ.ም.
- መጽሔተ አሚን በአክሊለ ብርሃን ወልደቂርቆስ 1946 ዓ.ም.
- ዋዜማ በኅሩይ ወልደ ሥላሴ 1921
- 5ቱ እህት አብያተ ክርስቲያናት በዲ/ን ሰሎሞን ዮሐንስ ያልታተመ



# ከእስክንድርያ ለኢትዮጵያ ተሹመው የተላኩ ጳጳሳት ስም ዝርዝር

### *ከቅዱስ አባታችን ከአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን እስከ አቡነ ቄርሎስ*

ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት ከግብፅ የመጡ ጳጳሳት በሙሉ አንድ ዓይነት አቋም አልነበራቸውም:: በዚህ መጽሐፍ መግቢያ በመጠኑ እንደተገለጠው የተለያየ ባሕርይ ይንፀባረቅባቸዋል:: የነበራቸው አቋም የምንለካው ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ተሹመው ከመጡ ጊዜ ጀምሮ በሚያሳዩት ፀባይ ነው:: ይህም ትክክለኛ ሐዋርያነት፣ ግድ የለሽነት፣ እና ለጥቅም ተገዥነት ዋነኞች ፀባያቸው ነው:: እዚህ ላይ አጠቃላይ ስማቸውን እንደሚከተለው ሰፍረዋል::

የመጡትን ጳጳሳት ስም ብቻ ከማስፈር በማን ዘመነ መንግሥት እንደመጡ የተወሰኑትን /ያገኘሁትን/ ለማስቀመጥ ሞክሬአለሁ:: ይህም አንዳንድ የሀገራችን ነገሥታት ታሪክ ስመለከት እግረ መንገዴን በእነሱ ዘመን የመጣውን ጳጳስ ማን እንደሆነ የተወሰነውን ለቅሜ ባወጣውም ከመረጃ ማነስ የተነሣ ፍላጐቴ ተሳክቶ ሠንጠረዡን ለማሟላት ስላልተቻለ በአብዛኛው ሠንጠረዥ ክፍት ለመሆን ተገድዷል:: ወደፊት ከዚህ ቀደም ብዬ በእጩ ጌዎቹ ዝርዝር ላይ እንዳየነውና እንዳሳሰብኩት ክፍት የሆነው ቦታ ይሞላል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: እስከዚያው ግን ይህ ተሞክሯል::

| ተ.ቁ | ስም | በዘመኑ የነበረው ንጉሥ |
|---|---|---|
| 1 | ቅዱስ ፍሬምናጦስ | አብርሐ ወአፅብሐ |
| 2 | አቡነ ሚናስ | አብርሐ |
| 3 | አቡነ ጴጥሮስ | |
| 4 | አቡነ ማቴዎስ | |
| 5 | አቡነ ማርቆስ | |
| 6 | አቡነ ዮሐንስ | |
| 7 | አቡነ ገብርኤል | |
| 8 | አቡነ ዮሐንስ 2ኛ | |
| 9 | አቡነ ገብርኤል 2ኛ | |
| 10 | አቡነ ሚናስ 2ኛ | |
| 11 | አቡነ ሚካኤል | |
| 12 | አቡነ ይስሐቅ | |
| 13 | አቡነ ስምኦን | |
| 14 | አቡነ ጴጥሮስ 2ኛ | |
| 15 | አቡነ ሚካኤል 2ኛ | |
| 16 | አቡነ ገብርኤል 3ኛ | |
| 17 | አቡነ ዮሐንስ 3ኛ | |
| 18 | አቡነ ሚካኤል 3ኛ | |
| 19 | አቡነ ሚካኤል 4ኛ | በይምርሀነ ክርስቶስ |
| 20 | አቡነ ስምኦን 2ኛ | |



www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| 21 | አቡነ ዮሐንስ 4ኛ | |
| 22 | አቡነ ማርቆስ 2ኛ | |
| 23 | አቡነ አብርሃም | |
| 24 | አቡነ ቄርሎስ | በቅዱስ ላሊበላና ነአኩቶ ለአብ |
| 25 | አቡነ ዮሐንስ 5ኛ | |
| 26 | አቡነ ሚካኤል 5ኛ | ያግባ ጽዮን |
| 27 | አቡነ ስምኦን 3ኛ | |
| 28 | አቡነ ጴጥሮስ 3ኛ | |
| 29 | አቡነ ማቴዎስ 2ኛ | |
| 30 | አቡነ ያዕቆብ | በአፄ አምደ ጽዮን |
| 31 | አቡነ ፊቅጦር | በአፄ ሠይፈ አርዕድ |
| 32 | አቡነ ቄርሎስ 2ኛ | በአፄ ይኩኖ አምላክ |
| 33 | አቡነ ቆዝሞስ | |
| 34 | አቡነ ዮስጦስ | |
| 35 | አቡነ ሚካኤል 6ኛ | |
| 36 | አቡነ ገብርኤል 4ኛ | |
| 37 | አቡነ ሚካኤል 7ኛ | |
| 38 | አቡነ ማቴዎስ 3ኛ | |
| 39 | አቡነ ዮሳብ | |
| 40 | አቡነ ዮሴፍ | |
| 41 | አቡነ ቆዝሞስ 2ኛ | |
| 42 | አቡነ ፊላታዎስ | |
| 43 | አቡነ ጴጥሮስ 4ኛ | |
| 44 | አቡነ ዮሐንስ 6ኛ | |
| 45 | አቡነ ፊቅጦር 2ኛ | |
| 46 | አቡነ ዮስጦስ 2ኛ | |
| 47 | አቡነ በርምያ | |
| 48 | አቡነ ሚካኤል 8ኛ | |
| 49 | አቡነ ገብርአል 5ኛ | |
| 50 | አቡነ ሚናስ 3ኛ | |
| 51 | አቡነ ዮሐንስ 7ኛ | |
| 52 | አቡነ ዮሐንስ 8ኛ | |
| 53 | አቡነ አብርሃም 2ኛ | |
| 54 | አቡነ ማርቆስ 3ኛ | |
| 55 | አቡነ መቃርስ | |
| 56 | አቡነ ሚካኤል 9ኛ | |
| 57 | አቡነ ማቴዎስ 4ኛ | |
| 58 | አቡነ ሚካኤል 10ኛ | |
| 59 | አቡነ ገብርኤል 6ኛ | |
| 60 | አቡነ ዮሐንስ 9ኛ | |
| 61 | አቡነ ቄርሎስ 3ኛ | |
| 62 | አቡነ ሚናስ 4ኛ | |
| 63 | አቡነ ማትያስ 5ኛ | |
| 64 | አቡነ ሚካኤል 11ኛ | |
| 65 | አቡነ ገብርኤል 7ኛ | |
| 66 | አቡነ ማርቆስ 4ኛ | |



| | | |
|---|---|---|
| 67 | አቡነ ገብርኤል 8ኛ | |
| 68 | አቡነ ማቴዎስ 6ኛ | |
| 69 | አቡነ ዮሐንስ 10ኛ | |
| 70 | አቡነ ሚናስ 5ኛ | |
| 71 | አቡነ ማርቆስ 5ኛ | |
| 72 | አቡነ ክርስቶዶሉስ | |
| 73 | አቡነ ዘካርያስ | |
| 74 | አቡነ ፊላታዎስ 2ኛ | |
| 75 | አቡነ ሱንትዮስ | |
| 76 | አቡነ ገብርኤል 9ኛ | |
| 77 | አቡነ ዮሐንስ 11ኛ | |
| 78 | አቡነ ሚካኤል 12ኛ | በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ |
| 79 | አቡነ ገብርኤል 10ኛ | በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ |
| 80 | አቡነ በርተሎሜዎስ | በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ |
| 81 | አቡነ ማቴዎስ 7ኛ | በአፄ በዕደ ማርያም |
| 82 | አቡነ ዮሐንስ 12ኛ | |
| 83 | አቡነ ማርቆስ 6ኛ | |
| 84 | አቡነ ይስሐቅ 2ኛ | |
| 85 | አቡነ ክላድያኑ | |
| 86 | አቡነ ጴጥሮስ 5ኛ | በአፄ ናኦድ |
| 87 | አቡነ ማቴዎስ 5ኛ | በአፄ ልብነ ድንግል |
| 88 | አቡነ ስምኦን 4ኛ | |
| 89 | አቡነ ዮሳብ 2ኛ | በአፄ ገላውዴዎስ |
| 90 | አቡነ ሚካኤል 13ኛ | |
| 91 | አቡነ ማቴዎስ 9ኛ | |
| 92 | አቡነ ማርቆስ 7ኛ | |
| 93 | አቡነ ጴጥሮስ 6ኛ | በአፄ ያዕቆብ<br>በአፄ ዘድንግል |
| 94 | አቡነ ስምኦን 5ኛ | በአፄ ሱስንዮስ |
| 95 | አቡነ ማርቆስ 8ኛ | በአፄ ፋሲል |
| 96 | አቡነ ሚካኤል 14ኛ | በአፄ ፋሲል |
| 97 | አቡነ ዮሐንስ 13ኛ | በአፄ ፋሲል ወንድሙ ያስመጣው |
| 98 | አቡነ ክርስቶዶሉስ 2ኛ | በአፄ ዮሐንስ 1ኛ |
| 99 | አቡነ ሲኖዳ | በአፄ ዮሐንስ 1ኛ |
| 100 | አቡነ ማርቆስ 9ኛ | በአፄ ኢያሱ አድያምሰገድ |
| 101 | አቡነ ክርስቶዶሉስ 3ኛ | በአፄ ዳዊት 3ኛ |
| 102 | አቡነ ዮሐንስ 14ኛ | በአፄ ሕዝቅያስ |
| 103 | አቡነ ዮሳብ 3ኛ | |
| 104 | አቡነ መቃርዮስ 2ኛ | ጎንደር ሳይደርስ የሞተ |
| 105 | አቡነ ቄርሎስ 4ኛ | በዘመነ መሳፍንት |
| 106 | አቡነ ሰላማ 2ኛ | በአፄ ቴዎድሮስ |
| 107 | አቡነ አትናቴዎስ | በአፄ ዮሐንስ |
| 108 | አቡነ ጴጥሮስ 7ኛ | በአፄ ዮሐንስ |
| 109 | አቡነ ማትያስ 10ኛ | በአፄ ምኒልክና በንግሥት ዘውዲቱ |
| 110 | አቡነ ቄርሎስ 5ኛ | በአፄ ኃ/ሥላሴ |



www.ethiopianorthodox.org

# ዋቢ መጽሐፍት


1. አባ ጳውሎስ (ዶ/ር) ፓትርያርክ <u>የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አጭር የሕይወት ታሪክ ከምዕራብ ሀገሮች ጉብኝት በፊትና በኋላ</u>፣ 1987 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
2. መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ (ብላታ)፣ <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ፓትርያርክ</u>፣ 1956 ዓ.ም. ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
3. አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ (ሊቀ ጠበብት)፣ <u>መጽሔተ አሚን</u> 1946 ዓ.ም. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።
4. ኅሩይ ወልደ ሥላሴ (ብላቴን ጌታ) <u>ዋዜማ</u>፣ በማግሥቱ የኢትዮጵያን ነገሥታት በዓል ለማክበር 1921 ዓ.ም. ጎሕ ጽባሕ ማተሚያ ቤት።
5. ከበደ ተሠማ (ደጃዝማች) <u>የታሪክ ማስታወሻ</u>። 1962 ዓ.ም
6. ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (ብላቴን ጌታ) <u>ዝክረ ነገር</u> 1962 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
7. ደስታ ተክለ ወልድ (አለቃ) <u>ገበታ ዋሪያ የንባብ መማሪያ</u> በቅዱስ አልአዛር ማተሚያ ቤት 1928 ዓ.ም. ድሬዳዋ።
8. ሐዲስ የሻነው (ዶክተር) <u>ፍንጭ ፍተሻ</u> 1998 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
9. ከበደ ሚካኤል <u>የዓለም ታሪክ</u> 1948 አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
10. አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ) M.A. <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ</u> 1978ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
11. አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ) M.A. <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u> 1991 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
12. ሰሎሞን ዮሐንስ (ዲያቆን) <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት</u> 1ኛ መጽሐፍ 1995 ዓ.ም. እሌኒ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
13. መርሻ አለኸኝ (ዲያቆን) <u>ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን</u> 1997 ዓ.ም. ኢትዮ ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
14. ጳውሎስ ኞኞ <u>ዐፄ ቴዎድሮስ</u> 1983 ዓ.ም. ቦሌ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
15. አሥራት ገብረ ማርያም <u>መርሐ ሕይወት</u>፣ ሁለተኛ መጽሐፍ 1992 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
16. ትንሣኤዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ <u>መዘክረ ምግባር መንፈሳዊ ዘቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>፣ ጥቅምት 14 ቀን 1948 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
17. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ <u>አዲሲቱ ኢትዮጵያ</u>፣ 1945 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
18. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ <u>ዜና ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ</u>፣ ሰኔ 10 ቀን 1950 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
19. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት፣ <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትና ዛሬ</u>፣ 1990 ዓ.ም. አማርኛና እንግሊዝኛ፣ በንግድ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
20. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ <u>ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከመምህርነት እስከ ፓትርያርክነት</u>፣ ግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
21. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ፣ <u>ዜና መዋዕል ዘብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ</u>፣ 1ኛ መጽሐፈ ሐምሌ 5 ቀን 1989 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
22. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የተዘጋጀ፣ <u>ዝክረ አበው</u>፣ 1996 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
23. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት፣ <u>ታሪካዊው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር</u>፣ 1996 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
24. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የቀብር ሥነ ሥርዓት አስፈጻሚ ኮሚቴ የታሪክ ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ <u>ሰማዕቱ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ</u> 1984 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
25. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፍልሰተ አዕም 5ኛ ዓመት ለመታሰቢያቸው የተሠራው ቤተ መዘክርና ሐውልት የተመረቀበት፣ <u>ዝክረ ቴዎፍሎስ ሁለተኛው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ</u>፣ ለዚሁ በዓል ዝግጅት የተቋቋመ ኮሚቴ ሐምሌ 4 ቀን 1989 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
26. <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እድገትና ነፃነት</u>፣ ለ21ኛው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል መታሰቢያ የጋዜጣና ማስታወቂያ መሥሪያ ቤት አሳትሞ ያበረከተው ጥቅምት 15 ቀን 1944 ዓ.ም. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ።
27. ሉሌ መልአኩ፣ <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u>፣ ለሦስተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የወጣ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1996 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
28. <u>ሐዲስ ሕይወት</u> ቁጥር 1 1964 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
29. <u>ሐዲስ ሕይወት</u> ቁጥር 2 80ኛ ዓመት የልደት በዓል መታሰቢያ አዲስ አበባ።
30. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ <u>ዜና ቤተ ክርስቲያን ልዩ እትም</u> ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ 1ኛ ዓመት በዓለ ሢመት፣ ግንቦት 1 ቀን 1964 ዓ.ም. አዲስ አበባ።






www.ethiopianorthodox.org

## ከዚህ ቀደም የታተሙ

1. የኢትዮጵያ የቤተክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት 1ኛ መፅሐፍ
2. ድል ለነሳው
3. ይኸው የፓትርያርክነቱ መንበር እንዴት ተገኘ?

## ወደፊት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተዘጋጁ

1. የኢትዮጵያ የቤተክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት 2ኛ መፅሐፍ
2. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የችግር ዘመናት
3. የጋብቻ ሕይወት በቤተክርስቲያን
4. የአዲስ ኪዳኑ መፅሐፍ ቅዱስ ጥናት
5. አምስቱ እህት አብያተክርስቲያናት

"…. የማይቀጠርና የማይሰፈር በእኛ ላይ የታወቀ የቸርነቱን ብዛት እንናገር፤ እርጉም በሆነ ከይሲ ምክር ትዕዛዝን ባፈረስን ጊዜ ከተድላ ገነት ወደ ጥፋት ከህይወት ወደ ሞት ከነፃነት ወደ መገዛት ወጣን፤ ለህጢያት ቀንበር ተገዛን። እርሱ ግን ፍጥረቶቹን አልተወንም ቸልም አላለንም። እርሱን እንደበደልነው መጠን ፈጽመን እንጠፋ ዘንድ በህጢያታችን አልተቀየመንም ወደደን እንጂ፤ ኀበኛንም ማረን ይቅርም አለን፤ ከሚገዛን እጅ አዳነን። አዳኝ መድኃኒት የምክሩ አበጋዝ፤ ለአባቱ ቀኝ እጁ፤ ክንዱ ሀይሉና ጥበቡ የሚሆን ልጁን ላከልን። በእርሱም ከዚህ ዓለም ወገን የወደደውን ሁሉ አደረገ የመረጣቸውን እነርሱን ጠራቸው የጠራቸውን እነርሱንም ወደዳቸው የወደዳቸውን እነርሱን አከበራቸው ያከበራቸውን እነርሱን እውነተኞች አደረገ። እውነተኞች ያደረጋቸውን እነርሱን አከናወና የልጁ ጌጥ ይሆኑ ዘንድ …"

(ከዮሐንስ አፈወርቅ ቅዳሴ በከፊል የተወሰደ)

www.ethiopianorthodox.org